# አሥራ ሁለቱ

# ነቢያትና

# መልእክታቸው

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጆች የነቢያትን መልእክት እነርሱ ከተናገሩበት ታሪካዊ መሠረት አንጻር መገንዘብ እንዲችሉ ለመርዳት ነው። ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ ስታጠኑ ምንጊዜም ከነገሥት ወይም ከዜና መዋዕል የተጠቀሱትን ክፍሎች በሚገባ አንብቡአቸው። በተጨማሪም ይህንን መጽሐፍና መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ጎን ለጎን አድርጋችሁ ተጠቀሙባቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ጥቅሶች በፍፁም ሳትዘሉ በሙሉ አንብቡአቸው መምህራን ከሆናችሁ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ እና በዚህ መጽሐፍ ላይ ሌላ ተጨማሪ የሆነ የራሳችሁ ማስታወሻ ደብተር ይኑራችሁ፤ በጥናታችሁ ወቅት ልባችሁን የሚነካውን ነጥብ በዚህ ደብተራችሁ ውስጥ አስፍሩት። ተማሪዎች ከሆናችሁ ከዚህ መጽሐፍ ጋር አያይዛችሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ጥቅሶች ዘወትር አንብቡ።

የአሥራ ሁለቱ ነቢያት ጽሑፎች ደራሲ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አትዘንጉ። መንፈስ ቅዱስ ዘወትር ቃሉን ሊመግበን ይፈልጋል። ስለዚህ በጸሎት መንፈስ ማንበብ እና ማጥናት ይገባናል፤ ለተማርነውም ቃል ታዛዥ መሆን ይኖርብናል።

በምታጠኑበት ወቅት መልስ ያላገኛችሁለት ጥያቄ ቢገጥማችሁ ወይም አስተያየት ቢኖራችሁ፡-

ለአዘጋጁ ክፍል

የመ.ሣ.ቁ. 127

አዲስ አበባ

ብላችሁ ጻፉልኝ።

ታርሞና ተሻሽሎ በ1982 ዓ.ም. ለ3ኛ ጊዜ የቀረበ ዕትም

እንደገና ለ4ኛ ጊዜ በ1984 ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ


ገጽ

1. ክፍል አንድ .................. 6

- ትምህርት አንድ .............................. 6
- ትምህርት ሁለት .............................. 14
- ትምህርት ሦስት .............................. 22
- ትምህርት አራት .............................. 28

2. ክፍል ሁለት .................. 37

- ትምህርት አምስት .............................. 37
- ትምህርት ስድስት .............................. 47

3. ክፍል ሦስት .................. 56

- ትምህርት ሰባት .............................. 57
- ትምህርት ስምንት .............................. 65
- ትምህርት ዘጠኝ .............................. 72

4. ክፍል አራት .................. 80

- ትምህርት አሥር .............................. 81

5. መልሶች .................. 91-99

# ጠቅላላ መግቢያ

ይህ መጽሐፍ በብሉይ ኪዳን መጨረሻ ላይ የምናገኘውን 12 የትንቢት መጻሕፍት ለማጥናት እንድትችሉ ይረዳችኋል። እንግዲህ የመጽሐፉ ዓላማ ከላይ የተጠቀሰው ስለሆነ ዘወትር ይህን መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ጋር አስተባብራችሁ ማጥናት ይኖርባችኋል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ካነሳሳችሁ የተጠበቀበትን ግብ መትቷል ማለት ነው። ምን ጊዜም የተማርነውን ትምህርት ጠቃሚነት መገምገም ይኖርብናል። ስለዚህ የመጽሐፉን ጥቅም በሚከተሉት ሁለት እርምጃዎች መገምገም ይቻላል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ትምህርት ደህና አድርጋችሁ አጥኑት፤ ቀጥሉም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ክፍል አንብቡ። የንባብ ክፍሉን በሚገባ መረዳት ከቻላችሁ መጽሐፉ የተጠበቀበትን ተግባር ከግብ አድርሷል ማለት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኩንና ትምህርቱን ሁለቱንም በአንድነት አቀነባብረን ለማቅረብ ሞክረናል። እነዚህ 12 የነቢያት መጻሕፍት በውስጣቸው ብዙ ታሪክ የላቸውም፤ ስለዚህ ታሪካቸውን ከሌሎች ሥፍራዎች ቀድተን በማምጣት ማቅረብ ይኖርብናል። እንደ ምንም ብለን በተቻለን ዘዴ ታሪኩን ካልሰበሰብን በስተቀር የነቢያትን መጻሕፍት ለመረዳት በጣም ያዳግተናል። እነዚህ ነቢያት ስለየትኛው ሕዝብ እንደተናገሩ በደንብ ማስታወስ ከቻላችሁ ትምህርታቸውን ለመረዳት በጣም ይጠቅማችኋል፤ ትምህርታቸውን ከተያያዝነው ዘመን ጋር ለማዛመድ ይረዳናል። እነዚህ 12 ሰዎች መቼ፥ የትና ለምን እንደሰበኩ ለማስታወስ ስትሞክሩ አስቸጋሪ መስሎ ይታያችሁ ይሆናል። ነገር ግን የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ መገንዘብ ከቻላችሁ ጠቅላላ ትምህርቱን ለማስታወስ እጅግ በጣም ይረዳችኋል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በርከት ያለ ትምህርት ለማከል ሞክረናል። ሁሉን በአንድ ጊዜ ለመማር አትሞክሩ። መምህራን ከሆናችሁ ተማሪዎቻችሁ ይህንን መጽሐፍ እንዲገዙ ገፋፉዋቸው፤ ምክንያቱም ደጋግመው ሊያጠኑት ስለሚያስፈልጋቸው ነው። ተማሪ ከሆንህ ለፈተና ዝግጅት ብቻ ብለህ ይህንን መጽሐፍ አታጥና፤ ነገር ግን ዘወትር ልታጠናው እንድትችል በደህና ሥፍራ አስቀምጠው። ፈተና በማይኖርብህ ጊዜ ቀስ በቀስ የመጽሐፉ ሃሳብ ለአዕምሮህ ግልጽ እየሆነ እስኪመጣ ድረስ ማንበብ ይኖርብሃል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አራት ክፍሎች ይገኛሉ። እነርሱም:-

1. የእስራኤል ነቢያት
2. የይሁዳ ነቢያት
3. የኢየሩሳሌም ነቢያትና
4. ለአሕዛብ የተላኩ ነቢያት ናቸው።

እነዚህ መጻሕፍት እንዴት እንደተያያዙ ለመረዳት ጥቂት ጊዜ ብታጠፉ እያንዳንዳቸው የተናገሩትን መልእክት አንብባችሁ መተርጎም እንድትችሉ ይረዳችኋል። ታሪኩንና ትምህርቱን በአንድ ላይ ለማጥናት እንዲያመቸን በአራት መደብ ከፍለን አቅርበናቸዋል።

እያንዳንዱ ትምህርት ስድስት ክፍሎች ይኖሩታል። እንግዲህ ነጣጥላችሁ እጥኑዋቸው። ትምህርቶቹ በሙሉ ቀስ በቀስ እርስ በርሳቸው ይያያዛሉ። ስድስቱ ክፍሎችም የሚከተሉት ናቸው፦

1. አጠቃላይ የመጽሐፉ ታሪካዊ አቀማመጥ ይህም ቀስ በቀስ ከመጽሐፉ አጠቃላይ ትምህርት ጋር ስለሚያያዝ በአንድ ጊዜ የመማር ሙከራ ማድረግና በመጀመሪያውም ጥናታችሁ ወቅት እያንዳንዱን ነጥብ ማወቅ አያስፈልጋችሁም።
2. የነቢዩ ሸክም ወይም መልእክት
   ይህም ነቢዩ ለሕዝቡ ምን ተናገረ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል።
3. ማብራሪያ
   ይህ ክፍል አጭር ስለሆነ ስለ ክፍለ ምንባቡ ያሉአችሁን ጥያቄዎች በሙሉ አይመልስም! ስለዚህ በቅርብ ጊዜ በዝርዝር የሚያስረዳችሁ አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ የተባለ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ ይቀርባል። እስከዚያ እንግዲህ የመጽሐፍ ቅዱሱን የምንባብ ክፍልና እነዚህን አጫጭር አስተያየቶች ደግማችሁ አንብቡ።
4. ነቢዩ የተለየ ትኩረት ያደረገባቸው ነጥቦች
   እነዚህን ነጥቦች ለማወቅ ጥረት አድርጉ። ይህንን ካደረጋችሁ አንዱን የነቢይ መጽሐፍ ከሌላው መለየት እንደትችሉ ይረዳችኋል። ገና ማጥናት ስትጀምሩ እያንዳንዱ የነቢይ መልእክት በጣም ልዩ መሆኑ ባይሰማችሁም እንኳ በእውነት እያንዳንዱ መጽሐፍ ለየት ያለ መልእክት ያቀርባል።
5. ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና ይህም «ትምህርቱ እንዴት ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ሊያያዝ ይችላል?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል። የነቢያት ትምህርት ለእኛ ምንም ፍቺ አይኖረውም ብለን ማሰብ በፍጹም አይገባንም።
6. ጥያቄዎች
   መምህርም ሆነ ተማሪው ምንም ጠቃሚ የሆነ ነጥብ እንዳያመልጣቸው እነዚህ ጥያቄዎች ይረዷቸዋል። መልሶቹ በሙሉ በትምህርቱ ውስጥ ይገኛሉ። ደግሞም በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ተሰጥተዋል።

በተጨማሪም ጥያቄዎቹ የውይይት ርዕሶች ስለሆኑ ለውይይት ተጠቀሙባቸው። ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍለው መወያየት እና ከመምህሩ ጋር ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ በጣም ጠቃሚ ነው። ውይይት አዳዲስ ነጥቦችን ፈልፍሎ ለማውጣትና ግልጽ ያልሆኑ ነገሮችን ግልጽ እንዲሆኑ ለማድረግ ይረዳል።

መጽሐፍ ቅዱስን በምታነቡበት በማንኛውም ወቅት የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አስታውሱ! ራሳችሁንም ያለማቋረጥ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ፦ ይህ መጽሐፍ ለእኔና በአሁኑ ዘመን ለሚገኙት ክርስቲያኖች ምን ይናገራል?

# ማስታወሻ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ «ዓ.ዓ.» ማለት <u>ዓመተ ዓለም</u> ማለት ሲሆን ይህም ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ዓመት የሚያመለክት ነው።

ለአጠቃቀሙ የሚከተለውን ንድፍ በገጽ 5 ውስጥ ይመልከቱ።

<u>ዓ.ዓ.</u> የክርስቶስ ልደት <u>ዓ.ም.</u>




የንድፉ አጭር ማብራሪያ፡- በመስቀሉ ግራና ቀኝ ዜሮን የሚጠቁም ምልክት ይታያል። ከዜሮ ወደ ግራ ስንቆጥር መደመር ይኖርብናል! ከዜሮ ጀምረን ወደ ቀኝ ስንቆጥርም እየደመርን እንሄዳለን። አቆጣጠሩ ትንሽ ለየት ያለ በመሆኑ ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ብቻ እንደምሳሌ ወስደን እንመልከተው። ለምሳሌ ከጠርዙ ላይ ጀምረን ዜሮ ወደሚገኝበት ወደ መሐሉ አቅጣጫ ከቆጠርን ዜሮ ላይ እስክንደርስ እየቀነስን እንመጣለን ወይም ደግሞ በሌላ አነጋገር ከዜሮ ጀምረን ወደ ጠርዙ አቅጣጫ ከቆጠርን ጠርዙ ላይ እስክንደርስ እየደመርን እንሄዳለን ማለት ነው። ይህንን ከዚህ በላይ የተሰጠው ማብራሪያ ደጋግማችሁ ካነበባችሁት አቆጣጠሩ ግልፅ ሊሆንላችሁ ይችላል።

# ክፍል አንድ

## ትምህርት አንድ

### የእስራኤል ነቢያት

በእስራኤል ስለተናገሩ ነቢያት በምናስብበት ወቅት በእስራኤል ሁለት ዓይነት ነቢያት እንደነበሩ ማስተዋል ይኖርብናል። የመጀመሪያዎቹ ጽሑፍ አልጻፉም፤ ከእነርሱም መካከል በጣም የታወቁት ኤልያስና ኤልሳዕ ናቸው።

**ቀደምት ነቢያት** | **የእስራኤል ነገሥታት**




የኤልያስ ታሪክ ከ1ኛ ነገ.17 - 2ኛ ነገ.2 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ይገኛል። የኤልሳዕ ሞት በ2ኛ ነገ. 13፡14-21 ውስጥ ተመዝግቧል። ሌሎቹ የእስራኤል ነቢያት ትንቢታቸውን በጽሑፍ ያሰፈሩት ናቸው። እነርሱም ሆሴዕ፣ አሞፅና ኢዮኤል ናቸው። እስራኤል ከይሁዳ እንዴት እንደተገነጠለች የሚያስረዳትን 1ኛ ነገ.12ን ደግማችሁ አጥኑት። ምክንያቱም ይህ ምዕራፍ ለሆሴዕ፣ ለአሞፅና ለኢዮኤል ጥናት መልካም መሠረት ይጥላል።

እግዚአብሔር ሆሴዕን፥ አሞፅንና ኢዮኤልን ለአገልግሎት በጠራቸው ዘመን እስራኤል የነበራትን መንፈሳዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ስለሚነግረን የኤልያስንና የኤልሳዕን ታሪክ የያዘውን ክፍለ ምንባብ ከልሱት።

# ሆሴዕ

## ታሪካዊ አቀማመጥ

ከዚህ በታች የሚገኘው ካርታ ከንጉሥ ሰሎሞን ዘመን በኋላ ምድሪቱ እስራኤልና ይሁዳ በመባል እንዴት እንደተከፋፈለች ያሳየናል።




ይበልጡ መሬት የተያዘው በአሥሩ የእስራኤል ነገዶች ነበር። የነዚህን አሥር ነገዶች ስም ታስታውሳላችሁ? ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶስ የነበሩት ስንት ነበሩ?

የእስራኤል ዋና ከተማ ሰማሪያ ነበረች። የይሁዳ ዋና ከተማ ደግሞ ኢየሩሳሌም ነበረች። የቅድስቲቱን አገር ካርታ መንደፍና ሁለቱን ከተሞች በትክክለኛ ሥፍራቸው ላይ ማስቀመጥ መቻል ይኖርባችኋል።

የእስራኤልን ነቢያት በምናጠናበት ወቅት «722 ዓ.ዓ» በጣም ጠቃሚ ዘመን ስለሆነ በሚገባ በቃላችን ልናውቀው ይገባናል። የዘመናት ቁጥር ልክ እንደ ክፍተኛ ሥፍራ ነው፤ ይህንን ዘመን በደንብ ከተገነዘብነው ከእርሱ ወደኋላና ወደፊት ያለ ችግር ተመልሰን ልንመለከት እንችላለን።

አስታውሱ! ኤልሳዕ የሞተው በ800 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር። ሰማርያ በአሶር የተያዘችው በ722 ዓ.ዓ. ነበር። እንግዲህ በክፍል አንድ ውስጥ የምናጠናው ከ800-722 ዓ.ዓ. ድረስ ያሉትን ዘመናት ነው።




ሆሴዕ ለእስራኤል የሰበከው መቼ ነበር? ሆሴ.1፡2 ተመልከቱ።




| አዝያን | | ዳግማዊ ኢዮርብዓም |
|---|---|---|
| 2ኛ ነገ.15፡1-7 | 2ኛ ዜና 26፡1-23 | 2ኛ ነገ.14፡23-29 |

/ዓዛርያስ/ /ዖዝያን/

ሆሴዕ መቼ መስበክ እንደጀመረ በትክክል አናውቅም። ዳግማዊ ኢዮርብዓም በጣም ክፉ ንጉሥ ቢሆንም እጅግ ብርቱ ነበረ፣ 2ኛ ነገ. 14:25። የእስራኤል 4ኛ ንጉሥ በነበረው በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን በትክክል ባልታወቀ ወቅት ሆሴዕ መስበክ ጀመረ። ሆሴዕ ታሪካቸው በ2ኛ ነገ.15-16 ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኘው ከዳግማዊ ኢዮርብዓም በኋላ የነገሡትን የእስራኤል ነገሥታት አልጠቀሳቸውም። በእነርሱ ፈንታ በሆሴዕ 1:2 የይሁዳ ነገሥታት ስሞች ተጠቅሰው ይገኛሉ። 2ኛ ነገ. 15ና 16 ሆሴዕ ስላገለገለበት ዘመን ብዙ መረጃ ስለሚሰጡ እነርሱን በሚገባ ማንበብ ይጠቅማል።

## የነቢዩ ሸክም

እያንዳንዱ ነቢይ በተለያየ መንገድ ለሕዝቡ ተናግሯል። የነቢዩን ስሜት መረዳት የምትችሉ ከሆነ መልዕክቱን እንድታስተውሉ ይረዳችኋል። ነቢያት የእግዚአብሔር ባሕርይ የማይለወጥ መሆኑን በሚገባ ተረድተው ነበር። እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን ስለ ራሱ የተናገረው ነገር ዛሬም ዕውነት ነው። ነቢያት በሙሉ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ቅጣት እንደሚያስከትል ያውቁ ነበር። እያንዳንዱ ነቢይ ይህንን መልእክት የሚያቀርብበት የተለያየ መንገድ አለው።

እስራኤላውያን ለ400 ዓመታት በግብፅ ከተቀመጡ በኋላ እግዚአብሔር ከዚያ አወጧቸዋል፣ ዘፀ. 12 ተመልከቱ። እግዚአብሔር በበረሃ ውስጥ እስከ ሲና ተራራ ድረስ ሕዝቡን በመምራት ለእነርሱ የነበረውን እንክብካቤ አስመስክሯል። በዚያ ስፍራም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የስምምነት ውል ተዋውሏል፣ ዘፀ.20። ይህ ውል ከጋብቻ ውል ጋር የቀረበ ተመሳሳይነት አለው። እግዚአብሔር ይህንን ሕዝብ በግድ ምረጠኝ ብሎ አላስጨነቀውም። ራሱን ገለፀላቸው፤ እነርሱም እርሱን መረጡ እንጂ ሌላን አልመረጡም። የእርሱ መሆናቸውን እንዳይዘነጉ የተለያዩ ምልክቶችን ለምሳሌ ካህናት፣ ሰንበት፣ መሥዋዕቶች፣ ግዝረት፣ ታቦት ወዘተ ሰጧቸዋል።

ከ800-722 ዓ.ዓ. ድረስ ለእስራኤል መልካም ዘመን እንደነበረ 2ኛ ነገ.14-16 ያሳየናል። እስራኤላውያን በውስጣቸው ከሚገኘው ከጠማማው ልባቸው በስተቀር የተቀሩትን ጠላቶቻቸው በሙሉ ድል እንዲያደርጉ ዳግማዊ ኢዮርብዓም አበረታትቷቸዋል። በዚያ ዘመን ሕዝቡ ብዙ የሚታረሱ መሬቶችና የሚሸጡ ነገሮች ስለነበሩአቸው ባለጠጎች ሆነው ነበር። ከዚያ በኋላስ ምን ሆነ? እግዚአብሔር ከቀደሙት አባቶቻቸው ጋር የተዋዋለውን ስምምነት ረሱ።

ሆሴዕ ብዙ የተለያዩ ምሳሌዎችን እየተጠቀመ ጊዜው ሳያልፍባቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ይለማመጣቸው ነበር። አሥሩ ነገዶች ግን የሆሴዕን መልእክት መረዳት አልቻሉም።

ከ722 ዓ.ዓ. በኋላ ሆሴዕ በእስራኤል ወይም በይሁዳ ከሁለቱ በአንዱ ሥፍራ እንደነበረ ሆሴዕ 1:1 ያመለክተናል። እርሱ ራሱም የትንቢቱን ፍጻሜ ተመልክቷል። ሆሴዕ የሰበከው ስብከት እውነተኛ መሆኑን ስለሚያረጋግጥልን ከዚህ መጽሐፍ ጥናት ጋር 2ኛ ነገ. 17ን

በማስተዋል ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው። የእስራኤል ሕዝብ በሆሴዕ በኩል የመጣላቸውን መልእክት ለመቀበል እምቢ ስላሉ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ መፍረድ ነበረበት።

# ሆሴዕ 1-7

## ማብራሪያ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በርከት ያሉ አጫጭር ስብከቶችን እናገኛለን። ታሪኩም እርስ በእርሱ የተያያዘ ሆኖ እናገኘውም፤ ነገር ግን ለመረዳት የሚያዳግት መጽሐፍ አይደለም።

ምዕ. 1-3፡- የሆሴዕ የግል ታሪክ
ምዕ. 4-5 ጣዖት አምልኮ
ምዕ. 6-7፡- ግብዝነት

የመጀመሪያዎቹ 3 ምዕራፎች የሆሴዕን ቤተሰብ ታሪክ ያዘሉ ናቸው፤ በተጨማሪ የእስራኤል ምሳሌ ናቸው። ጎሜር የጋብቻ ውል አፍርሳ ነበር፤ ስለዚህ ሆሴዕ እርሷን በድንጋይ ወግሮ መግደል ሲኖርበት በዚህ ፈንታ እርሷን ፍለጋ ሄደ። እርሷም የማንም ሰው ሚስት ሳትሆን ሴትኛ አዳሪ ሆና ነበር። ሆሴዕ እርሷን ከተዋዋለችው ውል ለማስለቀቅ ገንዘቡን እንኳ ከፍሏል። የጎሜርን ታሪክ መጨረሻ አናውቅም። እስራኤል ምን እንደደረሰባት ግን እናውቃለን፥ 2ኛ ነገ. 17፡6፥ 14-18 ተመልከቱ።

የሆሴዕን ቤተሰብ ታሪክ በተረዳነውና በምናውቀው የእስራኤል ታሪክ መሠረት መተርጎም ይኖርብናል። ስለ ሆሴዕ ታሪክ ሌሎች ትርጉሞች ቀርበው ነበር። ነገር ግን ከእስራኤል ታሪክ ጋር አይስማሙም። እስራኤል በዘፀ. 20 ላይ የተሰጣትን ቃል ኪዳን በመጣስና ከጠላቶችዋ ከአሶርና ከግብፅ ጋር ሌሎች ውሎችን በመዋዋል አመንዝራለች።

ዳግማዊ ኢዮርብዓም 40 ዓመታት ነገሠ። (783-743 ዓ.ዓ.)። ከእርሱ ሞት በኋላ እስከ ሰማርያ ውድቀት ድረስ 20 ዓመታት አልፈዋል። በእነዚህ 20 ዓመታት ውስጥ 6 ነገሥታት ነግሠዋል። ነገር ግን 2ኛ ነገ.14፡23-29 ስለ ሕዝቡ መንፈሳዊ አቋም ምንም ነገር አይነግረንም።

ምዕ. 4-5 እስራኤል ምን ያህል ከትክክለኛው ሃይማኖት እንደራቀች ይነግረናል። በ4፡1-3 ላይ የምናገኘው እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ያቀረበው ክስ ነው። የሕዝቡ መልካም መሪዎች መሆን የነበረባቸው ካህናት የከፋ ሥራ መሪዎች ሆነዋል፥ 4፡4-10፤ 5፡1-3። ሕዝቡ እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ ጣዖት አምላኪ ሆኗል፥ 4፡11-19፤ 5፡4-7። በዚህ ዘመን ይሁዳና እስራኤል ጦርነት እያደረጉ ነበር፥ 5፡8-15።

ሕዝቡ የነቢያትን ቃል የሚሰሙ በማስመሰል ይጓዙ ነበር። ነገር ግን ልባቸው አልተለወጠም ነበር፥ 6፡1-11። በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አድማ ይካሄድ ነበር፥ 7፡3-7። ይህ ድርጊት ከ743-722 ዓ.ዓ. ድረስ ይመሩ በነበሩት በስድስቱ ነገሥታት ዘመን በግልፅ ሲደረግ ነበር። እስራኤል በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ ወደ አሶርና ግብፅ ለመጠጋት ፈርጥጣ ነበር፥ 7፡8-18። ይህ እስራኤል ያደረገችው የእርዳታ ስምምነት ምን ያህል

የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደጣሰችና የሌሎች ባዕዳን ጣዖታት እንደተደገፈች ያመለክታል። ግብዝነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊፈጽሙት ከሚችሉ ኃጢአቶች መካከል እጅግ በጣም መጥፎ ኃጢአት ነው። ሞኞች እጅግ የሚማረኩለት ኃጢአት ነው።

# ሆሴዕ 1-7

## ልዩ ልዩ ነጥቦች

1. ጎሜር ሴትኛ አዳሪ የሆነችው ሆሴዕ ካገባት በኋላ እንጂ ሳያገባት በፊት እንዳልሆነ ግልፅ ይመስላል። ከእስራኤልም ጋር የነበረው ሁኔታ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። የሆሴዕ ቤተሰብ ታሪክ በቅደም ተከተል አልተጻፈም ብለን መጨነቅ አይኖርብንም። አጠቃላይ ትርጉም ግን ግልፅ ነው። በገዛ ጥፋቷ የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውን አፍርሳ ነበር፤ ነገር ግን ሆሴዕ እርሷን ሳያጥላላ ሄዶ እንዲፈልጋት ጌታ አዞታል። ከእስራኤል ታሪክ ጋር ሊስማማ የሚችለው ትርጉም ይህ ብቻ ነው፤ 1:2-8፤ 2:2-13።
2. የዳነው ቅሬታ የተሰኘው ርእስ በብዙዎች የነቢያት መጻሕፍት ይገኛል። ጳውሎስ ከሮሜ 9-11 ባለው ክፍል ውስጥ ስለዚህ ቅሬታ ሕዝብ ያስተምራል፥ በተለይም 9:4-5፥ 25-26፤ 10:21ና 11:1-5 ተመልከቱ። ሕዝቡ በአጠቃላይ በክሕደት ውስጥ የሚመላለስ ቢሆንም እንኳ በማንኛውም ወቅት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የሚቆሙ አነስተኛ ሰዎች ይኖራሉ፥ 1:10-2:1። ነቢያትም በሕዝቡ መካከል ለሚገኙ ለእነዚህ ጥቂት ታማኝ ሰዎች የማጽናናት ቃል ይናገሩ ነበር።
3. በዕብራይስጥ ምዕ. 2:19-23 የተጻፈው በጣም መልክ ነው። የሆሴዕን ሚስት ታሪክ ትርጉም ያሳያሉ። በተጨማሪ እስራኤል ምንም እንኳ ለእግዚአብሔር ታማኝ ባትሆንም እግዚአብሔር ለእርሷ ያለውን ዓላማ ያመለክታሉ። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ በ2:14-18 ላይ ይገኛል። አሳዛኝ የሆነው የሆሴዕ ቤተሰብ ታሪክ ለእስራኤል ከልቡ እንዲማልድ መሠረት ሆኖታል።
4. የምዕ. 4:1-3 ሃሳብ ከኢሳ.1 ጋር ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን የሚከሳት በምን ላይ ተመርኩዞ ነው? ዘፀ.20ን መሠረት በማድረግ ነው፤ ማለት በቃል ኪዳኑ ነው።
5. <u>መጥፎ ሥነ ምግባር ዘወትር ወደ ጣዖት አምልኮ ይመራል</u>፥ 4:11-5:7። የእስራኤል ሰዎች በፈጣሪ ፈንታ ለራሳቸው ጣዖታትን መሥራት ጀምረዋል። በዘፀ. 20:4-6 ላይ እግዚአብሔር ምን እንደተናገራቸው ተመልከቱ። ማንኛውም ሕዝብ እግዚአብሔርን ማየት በሚሳነው ወቅት ሥራው ሁሉ የተገላቢጦሽ ይሆናል፥ ሮሜ 1።
6. 5:8-15 ምናልባት በኢሳ.7:1-9 ካለው ሃሳብ ጋር ይመሳሰላል። በዚህ ዘመን ይሁዳና እስራኤል ሁለቱም ብርቱ ነገሥታት እንደነበራቸው አስታውሱ፤ እነርሱም ዖዝያንና ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነበሩ፥ 2ኛ ነገ.13:12 ተመልከቱ። በነበረው ታሪካዊ ሁኔታ ላይ ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል ተናግረዋል።
7. የእስራኤላውያን ሞኝነት እግዚአብሔር ልባቸውን እንደማያየው አድርገው በመቁጠር መመላለሳቸው ነበር። እግዚአብሔር አንድ ነገር ብቻ ይፈልጋል፤ ይኸውም እውነተኛ ንስሐ ነው። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ከኃጢአታቸው ሳይላቀቁ እንዳሉ ሆነው

የቤተመቅደስ ሥርዓት ያካሄዳሉ፥ 6፡1-7፡2። የቤተ መቅደስ ሥርዓት ጠቃሚ የሚሆነው አስቀድሞ ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።

8. እግዚአብሔርን አልታዘዙም በማለታቸው በሁሉ በኩል ግራ ተጋብተዋል። እርዳታ ለማግኘት ወዲት መሄድ እንደሚገባቸው አያውቁም። ከሚጎዳቸው ጠላቶች ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ይሞክራሉ፥ 2ኛ ቆሮ.6፡14-18። አካዝ አሶራውያን እንዲረዱት ሲጠይቅ የእነርሱ ሃይማኖት ተከታይ ሆኗል፥ 2ኛ ነገ. 16፡7-9፤ 2ኛ ዜና 28፡16-21። በእግዚአብሔር ላይ ከመታመን ይልቅ ብርቱ ጦር ያላቸውን መንግሥታት ተጠግተዋል፥ 7፡8-16 ተመልከቱ። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጎ ስለነበር አካዝ ከአሶር ጋር የተዋዋለው ውልና ተመሳሳይ ውሎች ሁሉ በጌታ ዘንድ አመንዝራነት ናቸው።

# ሆሴዕ 1-7

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. እግዚአብሔር ከአይሁድ ሕዝብ ጋር አድርጎ የነበረው የቀድሞ ቃል ኪዳን ፍጻሜ አግኝቷል፥ ማቴ. 5፡17-20። በእርሱ ምትክ እግዚአብሔር አዲስ ቃል ኪዳን መስርቷል፥ ማቴ.26፡26-30። የዕብራውያን መጽሐፍ ስለ አዲሱ ቃል ኪዳን በሰፊው ያስረዳናል። የአዲሱ ኪዳን ተሳታፊዎች የምንሆነው ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን ተቀብለን በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች ለመሆን ስንለወጥ ብቻ ነው።
2. የእግዚአብሔር ፍቅር የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ አይደለም፥ ሆሴዕ 2፡14-18 አንብቡ። የእግዚአብሔር ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው? ከሁሉ በላይ እጅግ የተሻለውን ነገር ይመኝልናል ማለት ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር ለማስረዳት ሆሴዕ ብዙ ምሳሌዎች አቅርቧል። እኛም ዘወትር እግዚአብሔር ምን እንደሠራልን ማስታወስ ይኖርብናል።
3. በማንኛውም ጊዜ ፍርድ የሚሰጠው ከሥልጣን አንጻር ነው፥ ሆሴዕ 4፡4-10 ተመልከቱ። በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ካህናት እነማን ናቸው? አማኞች በሙሉ የእግዚአብሔር ካህናት የሆኑት ለምንድነው? በእግዚአብሔርና በማታምነዋ ዓለም መካከል የሚገኙ በመሆናቸው ነው። እግዚአብሔር የሃላፊነት ሸክም በማይሰማው የአመራር ክፍል ላይ የሚያመጣው ፍርድ በሕዝቡ ላይ ከሚያደርሰው የባሰ ነው። እግዚአብሔር የእርሱ ቤተሰብ አባላት ለሆኑት ሁሉ ሌሎችን እንዲንከባከቡ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። እያንዳንዳችን አንዳችን የሌላውን ሸክም ልንሸከም ይገባናል፥ ገላ.6፡1-2።
4. ውጤቱ ካልታየ እውነተኛ ንሥሐ አልተደረገም። የሠሩትን ኃጢአት መዘርዘርና ኃዘን መግለጥ ብቻ በቂ አይደለም፥ ሆሴዕ 6፡1-7፡2 ደግማችሁ ተመልከቱ። አንድ አማኝ ንስሐ መግባቱን እንዴት ያረጋግጣል? ንሥሐ ማለት አቅጣጫን መለወጥ ማለት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ንሥሐ የሚመለከተው የአዕምሮን አቋም ነው፥ በተሳሳተ መንገድ ላይ የምንጓዝ መሆናችንን ተገንዝበን በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ይዘነው የነበረውን አቅጣጫ ትተን ወደ ጌታ መመለስ ማለት ነው። ይህን አቅጣጫ ቀይሮ መመለስ ግልፅ

እና ተመልካቾች ሁሉ ሊያዩት የሚችሉት ነገር ነው። ተግባራችን ያው እንደቀድሞው ከሆነ ግን የልብ ለውጥ አላደረግንም ማለት ነው።

5. እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም ሰዎች ተገልለን እንድንኖር አይፈልግም፤ ነገር ግን ከአስተሳሰባቸው እንድንርቅ ይፈልጋል፥ 1ኛ ቆሮ. 5:9-11፤ ዮሐ.17:15። እግዚአብሔር መልካሙን የምሥራች እንዲያበሥሩላቸው ዮናስንና ናሆምን ወደ አሶር እንደሰደዳቸው እናውቃለን፤ ሆኖም እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ዕርዳታ ይልቅ የአሶራውያንን ለማግኘት ብለው ከእነርሱ ጋር በተወዳጁበት ወቅት ጌታ ተቆጥቶ ነበር። እግዚአብሔር ሙሴን በግብፅ እንዲመሰክር ልኮታል፤ ሆኖም እስራኤል በአሶር በተወረረችበት ወቅት በግብፅ ዕርዳታ እንድትታመን የጌታ ፈቃድ አልነበረም። ክርስቲያን ለማታምነዋ ዓለም የሚኖረው አቋም ምን መሆን አለበት? ከእግዚአብሔር አቋም ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት! ልባችን ሲስተካከል ተግባራችንም የተስተካከለ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ከሚለዩን ነገሮች ጋር አንቀሳቀልም፤ እነርሱም ከሚገኙባትም ዓለም ደግሞ ፈርጥጠን አንሸሽም።

# ሆሴዕ 1-7

## ጥያቄዎች

1. ለእስራኤል የተናገሩት ሁለት ዓይነት ነቢያት የትኞቹ ናቸው?
2. ኤልያስና ኤልሳዕ የታዩበት ዘመን የትኛው ነው?
3. የኤልያስ ታሪክ ተመዝግቦ የሚገኘው የት ነው?
4. ለእስራኤል የጻፉት 3 ነቢያት እነማን ናቸው?
5. የእስራኤል ምድር የመከረል ታሪክ የምናገኘው የት ነው?
6. የሆሴዕን መጽሐፍ ለማጥናት የኤልያስና የኤልሳዕ ታሪክ ለምን ይጠቅማል?
7. የእስራኤል ዋና ከተማ ማን ነበረች?
8. በ722 ዓ.ዓ. ምን ተፈፀመ?
9. ኤልሳዕ የሞተው በስንት ዐመተ ዓለም ገደማ ነው?
10. ሆሴዕ አሞፅና ኢዮኤል ለእስራኤል የሰበኩት መቼ ነበር?
11. የዳግማዊ ኢዮርብዓምን ታሪክ የምናገኘው የት ነው?
12. የመጨረሻዎቹ 6 የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ የሚገኘው የት ነው?
13. ለነቢያት ጥናት ዘፀ.20 ለምን ጠቃሚ ሆነ?
14. 2ኛ ነገ.14-16 የሚያሳየን ምንድነው?
15. የሆሴዕን ትንቢት እውነተኛነት የሚያሳየው የ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ የትኛው ነው?
16. ሆሴዕ ምዕ.1-3 በውስጡ ያዘለው ምንድነው?
17. ሆሴዕ የራሱን አሳዛኝ ታሪክ የሚተርከው ለምንድነው?
18. ዳግማዊ ኢዮርብዓም የነገሠው ለስንት ዓመታት ነው?
19. ከዳግማዊ ኢዮርብዓም ሞት እስከ ሰማርያ ውድቀት ድረስ ያለው ዘመን ርቀት ምን ያህል ነው?
20. ሆሴዕ 4-5 የሚናገረው ስለ ምንድነው?
21. ሆሴዕ የእስራኤልን ግብዝነት የገሠፀው በየትኞቹ ምዕራፎች ውስጥ ነው?

22. ትማር ሴትኛ አዳሪ የሆነችው መቼ ነው?
23. ሕዝቡ በአጠቃላይ ኃጢአተኛ ነበር?
24. ዳግማዊ ኢዮርብዓም እስራኤልን በሚያስተዳድርበት ወቅት የይሁዳ ንጉሥ ማን ነበር?
25. አዲሱን ቃል ኪዳን የሚነግረን የትኛው ምንባብ ነው?
26. የንስሐ ማረጋገጫ ምንድነው?
27. ለዓለም ያለን አቋም ምን ዓይነት መሆን አለበት?

# ትምህርት ሁለት

## መግቢያ

እስራኤል ለብቻዋ ተገንጥላ መኖር የጀመረችው ንጉሥ ሰሎሞን በ931 ዓ.ዓ. ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ታሪኳ የሚያከትመው በ722 ዓ.ዓ. በሰማሪያ ውድቀት ነው። ይኸውም 209 ዓመታት አልፎታል። ታምኒን ከእስራኤል ነገሥታት ጋር ከቆጠርነው እስራኤል 20 ነገሥታት ሲኖሩዋት ይሁዳም እንዲሁ 20 ይኖሩዋታል፣ 1ኛ ነገ.16፡21-22።

ከኤልያስና ከኤልሳዕ በፊትም እንኳ በእስራኤል ሌሎች ነቢያት ነበሩ፤ ለምሳሌ ሳሙኤልና አብርሃምም ነቢያት ተብለዋል። እንግዲህ ነቢይ ምንድነው? እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ተቀብሎ የሚናገር ነው። የሚናገረው ስለ አሁን ጊዜ ወይም ስለ ወደፊት ሁኔታ ሊሆን ይችላል።

ዳግማዊ ኢዮርብዓም ምንም እንኳ በአካሄዱ እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ መሪ ቢሆንም እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶችዋ ለማዳን ተጠቅሞበታል፣ 2ኛ ነገ. 14፡23-29 ደግማችሁ አንብቡ። ዮናስ ስለ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ተናግሯል። ሆኖም ዮናስ ስለ ዳግማዊ ኢዮርብዓም የተናገረውን ትንቢት በጽሑፍ ሰፍሮ አናገኘውም።

ከዳግማዊ ኢዮርብዓም በኋላ እስከ ሰማርያ ውድቀት ድረስ በእስራኤል 6 ነገሥታት ነግሠዋል። ሆኖም ስማቸው በሆሴዕም ሆነ በአሞፅ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሶ አይገኝም። 1ኛና2ኛ ዜና ስለ ይሁዳ እንጂ ስለ እስራኤል ምንም ነገር አይናገርም። እስራኤልን በሚመለከት በማንኛውም ጥናት 2ኛ ነገ.17 በጣም ጠቃሚ ምዕራፍ ነው። ይህ ክፍል የሆሴዕ፣ የአሞፅና የኢዮኤል ትንቢቶች እንዴት ፍጻሜ እንዳገኙ ይገልጻል። በ722 ዓ.ዓ. ስለ ሆነው የሰማሪያ ውድቀት ያለን መረጃ ይህ ክፍል ብቻ ነው።

# ሆሴዕ 8-14

## ታሪካዊ አቀማመጥ

1ኛ ነገ. 16፡21-28 በጥቂቱ ስለ ንጉሥ ዘንበሪ ይነግረናል። እርሱም ከ885-874 ዓ.ዓ. ለአሥራ አንድ ዓመታት ነግሦአል። ዘንበሪ በጣም ከታወቁት የእስራኤል ነገሥታት መካከል አንዱ ነበር። ሰማርያ አዲሲቱ የእስራኤል ዋና ከተማ እንድትሆን አድርጓታል። የአሶራውያን ግሪክ እንደሚያስረዳን ከእስራኤል ነገሥታት መካከል መጀመሪያ ለአሶር ታክስ የከፈለ ንጉሥ ዘንበሪ ነው። ከ800 ዓ.ዓ. እንሥቶ ለሚቀጥሉት 150 ዓመታት አሶር ከዕለት ወደ ዕለት ብርታት እየጨመረች መጣች።

885 - 875 ንጉሥ ዘንበሪ 1 ነገ.16፡21-28

አሞፅ
ሆሴዕ
ኢዮኤል

—— አሶር ብርቱ መንግሥት ሆነች

722 ዓ.ዓ. የሰማርያ መፍረስ 2 ነገ. 17

አሶር ከሰሜናዊው የእስራኤል ክፍል አንዳንድ ሥፍራዎችን የያዘችው ከኦዚያን ሞት ከ740 ዓ.ዓ. በኋላ መሆኑን እንረዳለን፣ ኢሳ. 8፡21-9፡1። ሆሴዕ፣ አሞፅና ኢዮኤል በእስራኤል ይሰብኩ በነበረበት ወቅት ኢሳይያስ በኢየሩሳሌም ይሰብክ ነበር፣ ኢሳ.10፡5-19፤ 28፡1-6። በኢሳ.36-39 የሚገኘው ታሪክ የተፈፀመው ከሰማሪያ መፍረስ በኋላ ነው።

ዳግማዊ ኢዮርብዓም አሶራውያን እንዳይደርሱበት ማድረግ ችሎ እንደነበረ 2ኛ ነገ.14፡25 ይነግረናል። ሆኖም እርሱ በ743 ዓ.ዓ. ሞቷል። ከዚህ በኋላ እስራኤል በጣም ተበላሽታለች። እግዚአብሔር 3 ነቢያት ቢልክላቸውም ሕዝቡ ንስሐ አልገቡም።

1ኛ ነገ.18-2ኛ ነገ.13 ከሚያሳየን ይዘት እንደምንረዳው እግዚአብሔር ነቢያቱን የላካቸው እንዲናገሩ ብቻ አልነበረም። ሕዝቡ በሰብአዊ ዓይናቸው የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲመለከቱ ብዙ አስደናቂ ነገሮችንም አድርገዋል። ሆሴዕ ተመሳሳይ ምንም ድንቆችን ባይጽፍም እግዚአብሔር በኤልያስና በኤልሳ ዘመን እንዳደረገው በዚህ ዘመንም ያደርግ ነበር ብለን መገመት እንችላለን።

እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ በአንድ ጊዜ ፍፁም ይሆናሉ ብሎ አይጠብቅም። በቤቴልና በዳን ተተክለው የነበሩት መሠዊያዎች ትክክል አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ እርሱ የማይወዳቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች እስከሚያስወግዱ ድረስ በፍጹም አልቀበላችሁም ብሎ አልነገራቸውም። በሆሴዕ፥ በአሞፅ እና በኢዮኤል አማካይነት ጥቂት ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመለሱ ጥሪ ያደርግላቸው ነበር። እነርሱም ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ አሻፈረን ባሉበት ወቅት ያላቸው ነገር ሁሉ ጠፍቶባቸዋል።

# ሆሴዕ 8-14

## የነቢዩ ሸክም

እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ውል ያላቸው በመሆናቸው ከተቀሩት የዓለም ሕዝቦች የተለዩ ነበሩ፥ ዘፀ.20፥ በተጨማሪ ዘፍ.15፡1-21 አንብቡ። እግዚአብሔር ቃሉን ማጠፍ ስለማይችል የሰጠውን ተስፋ ይፈጽማል። ሆኖም የአፈጻጸሙ መንገድ የተለያየ ሊሆን ይችላል። እስራኤላውያን በሙሉ መሲሁን አንቀበልም በሚሉበት ጊዜ እርሱ ከመካከላቸው ጥቂት ሰዎች በማዘጋጀት እንዲቀበሉት ያደርጋል፥ ዮሐ.1፡10-13፤ የሐዋ.2፡5-12።

·በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ·ሕጎች እንዳሉ ሁሉ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጋር የተያያዙ ሕጎች አሉ። እስራኤላውያን እነዚህን ሕጎች በማይታዘዙበት ወቅት ምን ይደርስባቸዋል? እግዚአብሔር ሃሳቡን አይቀይርም። ስለዚህ ለእስራኤላውያን ተዘጋጅተው የነበሩትን በረከቶች ነሥቶ ለሌሎች ማለትም ለሚታዘዙት ይሰጣቸዋል።

ሆሴዕ ስለ ፍርድ ያቀረበው መልእክት አዲስ አልነበረም፥ ዘሌ.26፡1-46 አንብቡ። የሆሴዕ መልእክት አለመታዘዛችሁ የራሳችሁ የነበረውን በረከት እንድታጡ ያደርጋችኋል የሚል ነው። ሆኖም በእነርሱም ቦታ እግዚአብሔር ሌላ ሕዝብ መርጧል ማለቱ እንዳልሆነ አጥብቆ ያሳስባቸዋል።

ሕዝቅኤል የተነበየው ከ597-560 ዓ.ዓ. ባለው ዘመን ነበር። ከዳንኤል ጋር በባቢሎን ይኖር ነበር። ሁለቱም በምርኮ ለተወሰዱት አይሁዶች መምህራን ነበሩ። እግዚአብሔር ከምርኮኞች መካከል ጥቂት የሆኑትን ታማኞች አዘጋጅቶ ተንከባክቧቸዋል። በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ሆሴዕ በሰፊው ስለ ፍርድ የሚናገረው ለምንድነው? ለዚህ ጥያቄ ሦስት መልሶች መስጠት እንችላለን።

1. ፍርድ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የቃሉ ተግባራዊነት ማረጋገጫ ነው። በረከት ከግላችን ጥረት ወይም ከተለያዩ ምንጮች እንደሚመጡ አድርጎ ማሰብ ከባድ ነገር አይደለም።

   ማንኛውም ጣዖትና ሃሰተኛ ነቢይ በጭራሽ ስለ ፍርድ ሰብኮ አያውቅም። ሆሴዕ ፍርድን በማስመልከት ባቀረባቸው መልዕክቶች ውስጥ ፍርድ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነጸብራቅ መሆኑን ያሳየናል።

2. ፍርድ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚጨነቅ ያሳየናል። ሕዝቡ ኃጢአትን ሲያደርጉ አይቶ ዝም ብሎ መመልከት አይችልም። ደግሞም ተመሳሳይ የሆኑ ስሕተቶች

እንዲሠሩ አይሻም። ፍርድ ለማጥፋት ተብሎ የተደረገ ሳይሆን እነርሱን ለማጥራትና እንደገና ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበትን መንገድ ለማዘጋጀት ነው። እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን አስተውሎ ምንም ባያደርግ ለሕዝቡ ጥንቃቄ አላደረገላቸውም ማለት ነው።

3. ፍርድ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለመሥራት ያቀደውን ዓላማ ሕዝቡ እንዲመለከቱ የሚያሳስባቸው መንገድ ነው። እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ በነቢያቱ አማካይነት ነግሯቸዋል። እነዚህም ነገሮች ለምን እንደሚፈፀሙም አብራርቶላቸዋል፣ 2ኛ ነገ.17፡7-23። በተግባር በሚተረጐሙበት ጊዜ ግን አደረገው የሚል ጥርጣሬ አይኖራቸውም ነበር። ሕዝቡ ጥያቄዎቻቸውን ሁሉ ከማቅረባቸውና ከመጠየቃቸው በፊት እግዚአብሔር እንደሚመልስ በነቢያት አማካይነት ተናግሮ ነበር።

# ሆሴዕ 8-14

## ማብራሪያ

ምዕ.8-10 ጣዖት አምልኮ ቅጣት እንደሚያስከትል
ምዕ.11 የእግዚአብሔር ፍቅር በፍፁም እንደማይለወጥ
ምዕ.12-13 ሰማርያ ለምን እንደፈረሰች
ምዕ. 14 የሆሴዕ ጸሎትና የእግዚአብሔር ተስፋ

የእስራኤል ሕዝብ ከሶስት የተለያዩ አገሮች ርዳታ ይፈልግ ነበር። ጌታ ከእነርሱ ጋር አድርጎ የነበረውን የሲናዊውን ቃል ኪዳን ረስተው የከነዓናውያንን ሃይማኖት ተቀብለው በአልን ያመልኩ ነበር፣ 9፡1። ከሕደት ከሚያስከትልባቸው ቅጣት ለመሸሸ ከአሶር እና ከግብፅ ጋር ለመወዳጀት ይፈልጉ ነበር። ይህን ሁሉ ያደረጉት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ደንብ መታዘዝ ችል ስላሉ ነበር።

ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ የከነዓናውያንን አምልኮ መርጠዋል፣ ሆሴዕ 8፡1-14። እግዚአብሔር ባቆመላቸው መሠዊያ ፈንታ የራሳቸውን መሠዊያ ተክለዋል። ነገር ግን በሁለት መሠዊያዎች መሥዋዕት ማቅረብ የማይቻል ነው። የጣዖታትን መሠዊያ ሲያቆሙ ፈጣሪያቸውንና ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን ያደረገውን አምላካቸውን አዋርደውታል።

ሆሴዕ በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት የሰፈሩትን ታሪኮች የእግዚአብሔር ድርጊቶች እንደሆኑ አድርጎ መቀበሉን አስተውሉ። እስራኤላውያን ለ430 ዓመታት በግብፅ ባርነት ቀንበር ሥር ተሰቃይተው ነበር! አሁን ደግሞ እግዚአብሔር እንደገና ወደ ባርነት ሊሰዳቸው እንደቆረጠ እንመለከታለን። በዚህ ጊዜ የሚገዙት እንደ ቀድሞው በግብፅ ሳይሆን በአሦር ነው፣ ሆሴዕ 9፡1-9። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ግብፅ የሚለው ስም ተጠቅሶ የሚገኝ ሲሆን

የተጠቀሰውም የአሶር ምሳሌ ሆኖ ነው፤ የሚደርስባቸው ሥቃይ ተመሳሳይ መሆኑ ሊያሳስባቸው ነው።

እግዚአብሔር እስከታደጋት ጊዜ ድረስ እስራኤል ሃያል አልሆነችም፣ ሆሴዕ 9፡10-14። አሁን ግን በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ሕዝቡ ሀብታምና ብርቱ ሆኗል። ሆኖም እግዚአብሔር ምን እንዳደረገላቸውም ዘንግተዋል። ያለ እግዚአብሔር ርዳታ የራሳቸውንም መንግሥት ማቋቋም እንደሚችሉ መሰሏቸዋል።

ይህ ዓይነት አስተሳሰብ አዲስ ነገር አልነበረም፣ ሆሴዕ 9፡15-16። ጳውሎስ በ2 ቆሮ.3 ውስጥ የቀደመው ውል ሕይወትን ለመለወጥ ምንም ኃይል እንዳልነበረው ያሳያል። ሕዝቡ በሆሴዕ ዘመን ይፈጽሙት የነበረው ድርጊት የዘወትር ተግባራቸው ነበር።

በዳግማዊ ኢዮርብዓም ከ783-743 ዓ.ዓ. ድረስ በገዛበት ረጅም የአገዛዝ ዘመን አበልፅጓቸው ነበር፣ 9፡17-10፡8። የዋና ከተማቸው የሰማርያ መፍረስ ገና 20 ዓመታት ወደፊት የሚሆን ነገር ቢሆንም ሆሴዕ ውድቀቷ የማይቀር አድርጎ ይመለከተዋል፣ 10፡5-8። እስራኤል በቂ ወታደሮችና ገንዘብ ስላለው አሶርን ድል አደርጋለሁ ብሎ አስቧል። ሆኖም የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማምለጥ የሚያስችለው ጽድቅ የለውም፣ 9፡15-16። እንደገና ሆሴዕ በ10፡9-15 ላይ ስለ ሰማርያ ውድቀት ይናገራል።

የሆሴዕ 11፡1-11 ቃላት ልክ እንደ አዲስ ኪዳን መልእክት ናቸው። እግዚአብሔር ለእስራኤል ላደረገው ነገር ሁሉ ያነሳሳው ፍቅር እንደሆነ ያሳየናል። እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ፍርድ ሊያመጣባቸው አይፈልግም። ቢቀጡም እንኳ ቅጣቱን ያስከተለባቸው የራሳቸው ስሕተት ነው እንጂ የእግዚአብሔር ፍላጎት ሆኖ አይደለም።

የእስራኤል ሰዎች ጥፋተኞች መሆናቸውን ሆሴዕ ያሳየናል፣ ምዕ.12-13 ተመልከቱ። ሰማርያ የወደቀችው ከእስራኤል አምላክ ይልቅ የአሶራውያን ጣዖታት ስለበረቱ ነበር? ወይስ አሶር የተሻሉ ወታደሮችና የጦር መሣሪያ ስለነበሩዋት? የውድቀቱ ምክንያት ያልታወቀ ሳይሆን ኃጢአታቸው ያስከተለው ፍርድ ነበር፣ ሆሴዕ 13፡12-16።

ከእነርሱ ኃጢአት የተነሣ የሆሴዕ ልብ አልጠነከረም ነበር። ለብዙ ዓመታት ሰብኮላቸዋል፤ እነርሱም ንስሐ አንገባም ብለዋል፤ ቢሆንም እርሱ ያፈቅራቸው ነበር፣ 14፡1-3።

ሆሴዕ 14፡4-8 ከ1፡10-2፡1 ጋር ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር የሚፈርድባቸውና የፈረደባቸውም ሲሆንም እንኳ እስከመጨረሻው ጨርሶ አይጥላቸውም። ሆሴዕ ፍርዱንና ተስፋውን እንዴት እንደሚቀላቅለው ለአንዳንድ ሰዎች ግልፅ አይደለም። ፍርድ በተበየነበት ወቅት እንኳ ተስፋ የመስጠቱ ዝንባሌ የእግዚአብሔርን ባሕሪይ ያሳየናል።

ኃጢአት ሰዎችን ዕውር፣ ደንቆሮና ስሜት የሌላቸው ያደርጋቸዋል። ይህንን ሁኔታ መለወጥ የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሊሰራ የሚችለው ፈቃደኞች ሲሆኑ ነው። እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት የሚናገረው ለዚህ ነው። ሆሴዕ የሕዝቡን ሃሳብ ለመሰብሰብ ብዙ ጠንካራ ምሳሌዎችን ይጠቀማል። ይህንን የትንቢት መጽሐፍ ረጋ ባለ መንፈስ ደጋግማችሁ ማንበብ ይጠቅማችኋል። ሆሴዕ ምን ያህል የእግዚአብሔር ፍቅር እና የሕዝቡ ዐመፀኛነት ይሰማው እንደነበር ስትገነዘቡ የዚህን መጽሐፍ መልእክት ትወዱታላችሁ።

# ሆሴዕ 8-14

## የተለዩ ነጥቦች

1. ጣዖት አምልኮ ምንድነው? ሆሴዕ 8፡1-14። የእስራኤል ሕዝብ ለራሳቸው ያቆሙዋቸው ጣዖታት ስንት ናቸው? 1ኛ ነገ.12፡28-31። ሰው አምላኪ ፍጡር በመሆኑ እግዚአብሔርን ወይም ራሱ ያበጀውን ጣዖት ያመልካል። በሆሴዕ ዘመን እስራኤላውያን በትክክለኛው ወቅት መልካም ዝናብ ለማግኘት ብለው ለከነዓናውያን ጣዖታት መሥዋዕት ለማቅረብ ተፈትነዋል። በ1ኛ ነገ. 18 የተመዘገበው ጦርነት የተካሄደው ከሆሴዕ ዘመን ጥቂት ቀደም ብሎ ነው።
2. እግዚአብሔር በእርግጥ ሕዝቡን ይቀጣል? አንዳንድ ሰዎች ቅጣት ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ እና የክፉ ሥራ ውጤት ብቻ መሆኑን ይናገራሉ፤ ሆሴዕ 9፡7-9 አንብቡ። እግዚአብሔር በዚህ ዘመን አውቀው ኃጢአት የሚሠሩትን አማኞችን ይቀጣቸዋል? ሆሴዕ 13፡9-16 ተመልከቱ። 2ኛ ነገ.17፡5-23 የዚህን ትንቢት አፈጻጸም ያሳየናል። አንድ ነገር ኃጢአት መሆኑን ተገንዝበ ከዚያ ነገር ለመሸሽ መከራ አለማድረግ በድርጊቱ እንደመሳተፍ ይቆጠራል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት አይቶ ዝም ለማለት አይችልም።
3. ዳግማዊ ኢዮርብዓም ክፉ ንጉሥ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር እስራኤልን ባርኳታል፤ ሆሴዕ 9፡17-10፡2። ነገር ግን እስራኤል ምን አደረገች? የእግዚአብሔር በረከቶች እንቅፋት ሆነውባት ሕዝቧ በትዕቢት እንዲነፋ አደረጉት። እነዚህ በረከቶች በምሥጋና እንዲሞሉ ከማድረግ ይልቅ ጉረኞች አደረጓቸው። እስራኤላውያን በጣም አስቀያሚ የሆነ ኃጢአት ሰርተው ነበር! ይኸውም እግዚአብሔር ላደረገላቸው መልካም ነገር ጣዖቶቻቸውን አመስግነው ነበር።
4. ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ብሉይ ኪዳንን ፍርድና ቅጣት የሞላበት ክፍል አድርገው ሲመለከቱት አዲስ ኪዳን ደግሞ በፍቅር የተሞላ ነው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ብሉይ ኪዳን ስለ ፍቅር በሰፊው ይተርካል፤ ሆሴዕ 11፡1-11 በድጋሚ ተመልከቱ። በዚህ ምንባብ ውስጥ ከአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ጋር የሚስማሙ ስንት ጥቅሶች ይገኛሉ? ትክክለኛው የፍቅር ትርጉም እንክብካቤ ማለት ነው። ፍቅር እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው ስሜት ሳይሆን የሚያደርግላቸው ድርጊት ነው። እግዚአብሔር ሆሴዕን በሕዝቡ መካከል አኑሮ ትንቢት እንዲተነብይ የላከው ለሕዝቡ ካለው ፍቅር የተነሣ ነው።
5. ሆሴዕ 12፡2-6 በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ ምንባቡ ከዘፍጥረት መልዕክቶች ከየትኞቹ ጋር እንደሚስማማ አገናዝቡ፤ ሆሴዕ 12፡12-14 በተጨማሪ ተመልከቱ። 13፡4-11 የእስራኤልን የቀድሞ ዘመናት የሚመለከት ነው። እግዚአብሔር ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ካደረጋቸው ነገሮች መካከል በ750 ዓ.ዓ. አካባቢ ሆሴዕ በርከት ያሉ ምሳሌዎች ቀስም በመጽሐፉ ውስጥ አስፍሮ እንደቀረበ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በፍጹም አይለወጥም! ስለዚህ ከ1000 ዓመታት በፊት የፈፀማቸው ድርጊቶች ያኔ የነበራቸውን ትልቅ ዋጋ ዛሬ አላቀነሱም። የእግዚአብሔር ሥራዎች በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ብቻ የተመሰረቱ አይደሉም። የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ

የሚመነጩት ከባሕሪው ነው። ስለዚህ እርሱ ግን እንደሆነ ከሚያደርጋቸው ነገሮች እንረዳለን። ሆሴዕን በምታነቡበትና በምትማሩበት ጊዜ ትምህርቱንና ታሪኩን በአንድነት እያይዙት። ምክንያቱም የአንድ ድርጊት አካል ናቸው።

# ሆሴዕ 8-14

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

በዚህ ዓለም በምንኖርበት ዘመን ውስጥ ሁሉ ሰይጣን አይናችንን ከእግዚአብሔር ላይ አንሥተን ወደ ጣዖታት እንድንመለከት ለማድረግ ያልተቋረጠ ጥረት ያደርጋል። ጣዖት ማለት ገንዘብ፥ ዕድገት፥ ዕውቀት፥ ንብረትና ወዘተ ይኸውም በሕይወታችን ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ የወሰደ ማንኛውም ነገር ማለት ነው። በውስጣችን ጣዖታት እንዳሉ እንዴት ማወቅ እንችላለን? የናንተ የሆኑትን ነገሮች በሙሉ በዘረጋችሁት እጃችሁ ላይ በማስቀመጥ ወደ እግዚአብሔር አቅርቡ! ጌታ ሆይ ከፈቀድህ እነዚህን ሁሉ እንድትወስደብኝ እፈቅዳለሁ ብላችሁ ለመጸለይ ፈቃደኞች ናችሁ? ጥያቄው በግለሰብ ደረጃ ቢቀርብ ባሉህ ነገሮች ላይ እንደዚህ ዓይነት ዕርምጃ መውሰድ ትፈቅዳለህ?

ዕብራውያን 12 ስለ ቅጣት በሰፊው ያስተምረናል። ማንም ሰው ቅጣት አይወድም። ካልተቀጣን ከእርሱ ይበልጥ የከፋ የኃጢአት ውጤቶችን እናተርፍ ይሆናል። በፍርድ፥ በቅጣትና በኃጢአት ውጤቶች መካከል ልዩነት አለ። እግዚአብሔር የሚቀጣው ማንን ነው? ቢቃሉ እና በመንፈስ ቅዱሱ አማካይነት ንስሐ እንዲገቡ ሲያስጠነቅቃቸው ንስሐ የማይገቡትን ሰዎች ነው። ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምናልባት ስለዚህ ነገር በሚገባ አያስተምሩም ይሆናል። ስለዚህ ብዙ ክርስቲያኖች ኃጢአትን ማድረግ አይፈሩም። የእግዚአብሔርንም ቅጣት አይፈሩም። መፍራት ግን ይገባቸዋል!

እግዚአብሔር ኑሮአችንን ሲባርክ ምን እናደርጋለን? ባገኘናቸው ነገሮች መኩራራት እንጀምራለን? በረከት ካላገኙ ሰዎች የተሻልን አድርገን ራሳችንን እንቆጥራለን? ትሑት እንድንሆን ያደርገናል ወይስ ኩሩ? እግዚአብሔር ሕዝቡን መባረክ ይፈልጋል! ለእርሱ አገልግሎት የሚጠቀሙበት ከሆነ በተቻለ መጠን መልካም የሆኑ ነገሮችን ለልጆቹ አትረፍርፎ ሊሰጣቸው ይፈልጋል። ልባችን ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ቅን ካልሆነ ግን የእርሱን በጎ ስጦታዎች ለጥፋታችን እናደርጋቸዋለን።

ጌታችን ኢየሱስ ለእኛ ሲል ባደረገው ሥራ የእግዚአብሔርን ፍቅር ከማንኛውም ነገር በላይ ገልጾልናል፥ ዮሐ.3፡16 ተመልከቱ። እግዚአብሔር ቢያንስ ለሁለት ምክንያቶች ለኛ ይጠነቀቃል:-

1. በተቻለ መጠን ለእርሱ የተለየን ሕዝብ እንድንሆን ስለሚፈልግና
2. እንድናገለግለው የሰጠንን መልካም ስጦታ ከሚወስድብንና ከሚጎዱ ኃይሎች ሁሉ ጥበቃ ሊያደርግልን ስለሚፈልግ ነው። ፍቅር የእግዚአብሔር ባሕርይ በመሆኑ እንደሚንከባከበንና እንደሚያስብልን በፍጹም ልንጠራጠር አይገባም።

የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚያቀርቡልንን መንፈሳዊ ትምህርት ብንረዳም ሁለቱም ክፍሎች በታሪክ ላይ የተመረኮዙ መሆናቸውን መዘንጋት አይኖርብንም። ብሉይ ኪዳንን በምናነብበትም ሆነ በምናስተምርበት ጊዜ ታሪኩንና ትንቢቱን በአንድ ላይ እናድርጋቸው። አዲስ ኪዳንን በምናነብበትና በምናስተምርበት ጊዜ የድርጊቱን ታሪካዊ መሠረት ለመረዳት ጥረት እናድርግ፣ ምሳሌ:- ሉቃስ 3፡1-3። የጳውሎስን ታሪክ በምናነብበትና በምናስተምርበት ጊዜ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከሚገኘው ታሪክ ጋር እናዛምደው። እግዚአብሔር በተወሰነ ዘመን፣ ለታወቀ ሕዝብ በተመረጠ ሥፍራ ተናግሯል።

# ሆሴዕ 8-14

## ጥያቄዎች

1. የዘንበሪን ታሪክ የምናገኘው የት ነው?
2. ሰማርያ የእስራኤል ዋና ከተማ እንድትሆን የቀረቀራት ማን ነው?
3. አሦር እስራኤልን በአስጨነቀቻት ዘመን በእስራኤል ይናገሩ የነበሩት ነቢያት እነማን ነበሩ?
4. ዖዝያን የሞተው መቼ ነው?
5. ኢሳ.8፡21-9፡1 የሚያወራው ስለ ምንድነው?
6. ዳግማዊ ኢዮርብዓም የሞተው መቼ ነው?
7. ከ1ኛ ነገ.18-2ኛ ነገ.13 ድረስ የሚገኘው የማን ታሪክ ነው?
8. እግዚአብሔር እስራኤልን እንደጠራት የሚያስረዱን ሁለት ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
9. ከቃል ኪዳኑ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ነገሮች ምንድናቸው?
10. ሆሴዕ ያቀረበው ዓይነት መልዕክት የት እናገኘዋለን?
11. በባቢሎን ምርኮ ወቅት ይናገሩ የነበሩት ሁለት ነቢያት ማን ማን ናቸው?
12. እስራኤል ቃል ኪዳን ለማድረግ የሞከረችው ከማን ጋር ነው?
13. ዳግማዊ ኢዮርብዓም እስራኤል ምን እንድትሆን ረዳት?
14. ሆሴዕ የተነበየው ስለ የትኛይቱ ከተማ ውድቀት ነው?
15. እስራኤላውያን ማምለክ የጀመሩት የማንን ጣኦት ነው?
16. ሆሴዕ 11፡1-11 የሚናገረው ማንን በሚመለከት ነው?
17. ሆሴዕ ብዙ ታሪኮችን የጠቀሰው ለምንድነው?
18. በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ የሚያስተምረው የትኛው ምዕራፍ ነው?
19. ሉቃስ 3፡1-3 ጠቃሚ ምንባብ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
20. ጣዖት ምንድነው?

# ትምህርት ሦስት

## መግቢያ

እግዚአብሔር ሦስት ዓይነት ሠረተኞችን አደራጅቷል። እያንዳንዳቸውም የሚሠሩዋቸው የተለያዩ ሥራዎች አሏቸው። እነርሱም ነቢያት፣ ካህናትና ነገሥታት ነበሩ። ከእነዚህ ከሶስቱ መካከል ማንኛቸውም ቢሆኑ የሚመረጡት በእግዚአብሔር ነበር። የሥራ ድርሻቸውንም የሚመርጡት ራሳቸው አልነበሩም።

1ኛ ነገ. 12 የእስራኤልንና የይሁዳን መከፋፈል ይነግረናል። ከ931-910 ዓ.ዓ. የነገሠው ቀዳማዊ ኢዮርብዓም ሲሆን የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ነበር። እርሱም በቤቴልና በዳን መሠዊያዎችን በመሥራቱ እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄዱ ከልክሏል። የአሮን ቤተሰብ ያልሆኑ ካህናትን መርጦ አዘጋጅቷል። ንጉሥ ቢሆን እንኳ ቀዳማዊ ኢዮርብዓም የዳዊት ዘር አልነበረም።

1ኛ ነገ.13 በእስራኤል ወደምትገኘው ቤቴል ሄዶ ስለነበረ ነቢይ ይነግረናል። በሰሜን የነበሩት ነቢያት እንኳ ብላሽ ነበሩ። እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ ሌሎች ነቢያትን እየላከ ምን እንደሚመጣ ያሳስባቸውና ይነግራቸው ነበር።

የኢዮኤልና የዕንባቆም መልዕክቶች ተመሳሳይነት አላቸው። ኢዮኤል የአሶርን መምጣት ሲመለከት ዕንባቆም ደግሞ የባቢሎንን ይመለከታል።

የአሶር ዋና ከተማ ነነዌ ነበረች። ሁለት ነቢያት ዮናስና ቀጥሎም ናሆም ለአሶር ተናግረዋል። ነነዌ ከሰማሪያ ውድቀት ከ110 ዓመታት በኋላ በ612 ዓ.ዓ. ወደመች። ስለዚህ ለ110 ዓመታት የይሁዳ ቅርብ ጎረቤት አሶር ነበረች።

## ኢዮኤል

### ታሪካዊ አቀማመጥ

መጽሐፉ መቼ እንደተጻፈ ምንም ፍንጭ አይሰጠንም። ሆኖም የመጽሐፉ መልዕክት በጊዜ ላይ የተመረኮዘ ባለመሆኑ መቼ እንደተጻፈ ማወቅ ምንም ጥቅም አይሰጠንም።

አንዳንድ ምሁራን ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በፋርስ ዘመነ መንግሥት ነው ብለው ይገምታሉ፤ ይኸውም ከ538-333 ዓ.ዓ. መካከል ነበር። ነገር ግን ይህ ግምት ትክክል አይደለም።



743 - ዳግማዊ ኢዮርብዓም ሞተ።

አሞፅ

ሆሴዕ ሁሉም የሰበኩት በዚህ ዘመን ነው።

ኢዮኤል

722 - የሰማሪያ ውድቀት

612 - የነነዌ መፍረስ

ዘንበሪ የተባለው የእስራኤል 6ኛ ንጉሥ ከ885-874 ዓ.ዓ. በንጉሥነት ቆይቷል። አሶር እስከ 606 ዓ.ዓ. ድረስ ሙሉ ለሙሉ በባቢሎን አልተረታችም ነበር። ይኸውም አሶር ለ280 ዓመታት ያህል የእስራኤልና የይሁዳ ቀንደኛ ጠላት ነበረች።

ኢዮኤል የሰበከው ለእስራኤል ነው የምንለው ለምንድነው? የኢዮኤል መጽሐፍ ከአሞፅና ሆሴዕ ጋር ዘወትር የሚያያዝ በመሆኑ ነው። ኢዮኤልን በሌላ ሥፍራ እንድናስቀምጠው የሚያስችለን ምክንያት አይኖረንም። በትንቢቱ ውስጥ የይሁዳ ስም አልፎ አልፎ ተጠቅሶ ይገኛል! እንዲሁም የቤተ መቅደሱ ሥርዓት ተጠቅሷል። በሆሴዕና በአሞፅም ውስጥ ደግሞ ተመሳሳይ ሁኔታ እናገኛለን።

የኢዮኤል መልዕክት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የሚስማማው ከዚህ ዘመን ጋር ብቻ ነው። ምናልባት በመጀመሪያ አሞፅ ቀጥሎ ሆሴዕ በመጨረሻ ኢዮኤል በቅደም ተከተል ሰብከው ይሆናል። ኢዮኤል የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዲሸሹ የመጨረሻ ዕድል ሰጥቷቸው ነበር። እነርሱ ግን አልተቀበሉትም። 2ኛ ነገ.17 ምን እንደደረሰባቸው ይነግረናል። 2ኛ ነገ. 17 ከአዲስ ኪዳን ታሪክ ጋር ብዙ የሚዛመዱ ነጥቦች ስላሉት በጥንቃቄ መገንዘብ ጠቃሚ ነው።

እስራኤላውያን ከግብፅ ጋር ተባብረው በአሶር ላይ ለመነሣት መከራ አድርገው ነበር፣ 2ኛ ነገ.17፡1-4። ስለ ከተማይቱ ማለት ስለ ሰማሪያ መያዝ በሰፊው ተዘርዝሮ አልቀረበልንም፣ ድርጊቱን ግን በ2ኛ ነገ. 17፡5-6 በአጭሩ ተጠቅሷል። ከ7-23 የሚገኙት ጥቅሶች ሰማሪያ በምን ምክንያት እንደወደቀች በሚገባ ስለሚያስረዱን በጥንቃቄ ብናስተውላቸው በጣም ይጠቅሙናል። ይህ ሁኔታ በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ውስጥ አስገራሚ ገጽታ ነው። ለሚደረጉት ነገሮች ሁሉ ምክንያት ይኖራቸዋል። የሰማሪያ ውድቀትና የአሰሩ ነገዶች መማረክ ከሥነ ምግባር ጋር የተያያዘ ምክንያት አለው። በዕዝራ መጽሐፍ ውስጥ ሰፍሮ የሚገኘው

ከባቢሎን ምርኮ በሚመለሱትና በምድሪቱ ይኖሩ በነበሩት ሰዎች መካከል የነበረው ጠላትነት መሠረት ምን እንደነበረ ከቁ.24-41 ያሉት ጥቅሶች ያሳዩናል። በዮሐንስ 4 ውስጥም ተመሳሳይ ነገር እንመለከታለን።

ኢዮኤል የተመለከታቸው አንበጦች የአሶር ወታደሮች ሆነው ተገኝተዋል። የኢዮኤል ትንቢት ይበልጡ ተፈጽሟል፥ ኢዮኤል ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠው ማስጠንቀቂያ እውነተኛነት 2ኛ ነገ.17 ያረጋግጣል። ኢዮኤል ለእስራኤል የተላከ በእግዚአብሔር መሆኑን የሚያረጋግጠው የተናገረው ትንቢት መፈጸም ነው።

# ኢዮኤል

## የነቢዩ ሸክም

ነቢያት በሙሉ ከነበራቸው ልምምድ የተነሣ እግዚአብሔርን የሚያውቁት ሰዎች ነበሩ። በኑሮአቸው የእርሱን ኃይል ተገንዝበዋል። ከዚህ ሌላ የእርሱን በረከት የተሳተፉ ሲሆን ቸርነቱንም አውቀዋል።

አንድ ሰው ነቢይ እነዚህ ነገሮች ብቻ አያደርጉትም። እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔር ተግባር በእስራኤል ሕዝብ መካከል ምን እንደሆነ ተረድተዋል። የሙሴን ሕጋጋት አጥንተዋል። የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንና ጌታ ለሕዝቡም የሰጠውን ሕጋጋት አውቀዋል።

ኢዮኤል ስለ እስራኤል ኃጢአት ብዙም አላወራም። በሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ ስሕተታቸውን በጥቂቱ ተመልክተናል። ሆሴዕ የእስራኤልን ሕዝብ መንፈሳዊ ችግር ይነግረናል። አሞፅ የሕዝቡን ሥነ ምግባራዊ ጉድለት ያወራልናል። ሕዝቡ ሁሉ ስግብግቦች ነበሩ፤ እርስ በርሳቸው ይካከሱ ነበር።

ኢዮኤልም የተመለከተው አዲስ ነገር አልነበረም። አንበጦች ዘወትር እስራኤልን ይወሩዋት ነበር። ስለዚህ የእግዚአብሔር መንፈስ የአንበጦቹን ወረራና የሕዝቡን ኃጢአት በአንድነት በእርሱ ልብ ውስጥ አጣምሮታል። ኢዮኤል ለእስራኤል ሕዝብ ማስጠንቀቂያ ለማቅረብ የተጠቀመው በአንበጣ ወረራ ነበር።

በኢዮኤል ትምህርት ውስጥ ሶስት ነገሮች በአንድ ላይ ተሳስረው ይገኛሉ። እነርሱም፡- የአንበጦች ወረራ፥ የአሶር መምጣትና በሐጢአት ላይ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ ናቸው። በኢዮኤል መልዕክት ውስጥ ራሱ እንኳ ያልተረዳቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ፤ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ተጠቅሞ ለወደፊት ትውልዶች ተናግሯል።

ኢዮኤል ምንም እንኳ የሕዝቡ አዕምሮ ስለ ፍርድ እንዲያስብ የአንበጦቹን ወረራ ሊጠቀምበት ቢሻም በዚያው የንስሐ ጥሪ ያስተላልፍላቸዋል፤ እግዚአብሔር ቢፈርድባቸውም እንኳን ቃል ኪዳኑ እንዳልታጠፈ ይነግራቸዋል። እንደገናም ጥቂቶቻቸውን በመጠገን እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ያደርጋል።

በተቀሩት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች አዘውትሮ የማይገኝ ሌላ ትምህርት በኢዮኤል መጽሐፍ ውስጥ እናገኛለን፤ ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ነው። ነቢያት በሙሉ ስለ መንፈስ

ቅዱስ የተለያዩ ትምህርቶች አስተምረዋል። ነገር ግን በሕዝቡ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚወርድ የተነበየው የመጀመሪያ ነቢይ ኢዮኤል ነበረ። በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በአገሪቱ ውስጥ የተለየ ሥራ ይሠሩ ለነበሩ ሰዎች ይሰጥ ነበር፤ ይኸውም ለነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት ነበረ። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከእግዚአብሔር ፈጣሪነት ጋር ተያይዟል፥ መዝ.51፡10።

በብዙ ቦታ የኢዮኤል ቋንቋ ሥዕላዊ መሆኑን አስተውሉ። ስለዚህ ከጥሬ ቃላት አልፎ በመመልከት ኢዮኤል በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች ይናገር የነበረው መልእክት ምን ነበረ? ብላችሁ ሁልጊዜ ጠይቁ።

# ኢዮኤል

## ግብራሪያ

አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን ገበሬዎች ነበሩ። በንግድ ሥራ ላይ እንኳ የተሰማሩ የከተማ ሰዎች ኑሮአቸው በገበሬዎች የተደገፈ ነበር። ምርታቸው ሁሉ በድንገት ወድሟል፥ ኢዮ.1፡1-20። ከእነዚህ ጥቅሶች መካከል የወረራውን ከባድነት የሚጠቁሙትን መርጠህ በማውጣት ጻፉቸው። በ1፡13-14 የታወጀው ጾም ለሕዝቡ ግሳጼ ነበር።

ሕዝቡ አንበጦቹን ብቻ ሲመለከት ነቢይ ኢዮኤል ከእነርሱ አልፎ አሶራውያንን ይመለከት ነበር፥ ኢዮ.2፡1-11። እርሱ የተመለከታቸው አንበጦች ፈረሶች ሆነው አገኟቸዋል። አንበጦቹ ከሰሜን መጥተው የሚወሯቸው ሠራዊቶች ምሳሌ ነበሩ። ይህም ሁኔታ በ722 ዓ.ዓ. ተፈጽሟል። አንበጦቹ እህሉን በአጠቃላይ እንዳበላሹ ሁሉ እንዲሁ አሶራውያን ምድሪቱን ደመሰሱዋት።

ነገር ግን የማምለጫው ጊዜ አላለፈባቸውም ይሆናል፤ ባይዘገዩና ከልባቸው ንሥሐ ቢገቡ ምናልባት እግዚአብሔር ለነነዌ እንዳደረገው ምሕረት ያደርግላቸው ይሆናል። ኢዮኤል ሕዝቡ እውነተኛ ንስሐ እንዲያደርጉ ይጋብዛቸዋል፥ ኢዮ. 2፡12-17። ነገር ግን ንስሐ ለመግባት ፈቃደኞች አልነበሩም። ችግሩ ስለተባባሰባቸው የይስሙላ ንስሐ ገብተዋል። ይሁን እንጂ ይህ ልባዊ ያልሆነ ንስሐ ከአሶራውያን አላዳናቸውም።

እግዚአብሔር ወዲያውኑ በመፍረድ ፈንታ ያደርገላቸው ነገር ምንድነው? ድንጋይ ልባቸውን እንደገና በቸርነቱ ሊያለሰልስ ይሞክራል። እንደገናም መልሶ ይባርካቸዋል፥ ኢዮ. 2፡18-27። ጳውሎስ በሮሜ 2፡4 ላይ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ ሊያቀርባቸው ይገባል ይላል። ይህንን ቸርነት ቢያቃልሉ የሚተርፉቸው ነገር ፍርድ ብቻ ነው።

የኢዮኤል ትምህርት ሶስተኛ ክፍል ስለ መጨረሻው ፍርድ ነው። እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚባርክ ሕዝቡንም ይባርካል፥ ኢዮ.2፡28-32። ነገር ግን ከሐዋ.2፡17-21 እንደምንረዳው የኢዮኤል ትንቢት እርሱ ከተረዳው በላይ እጅግ ፍጻሜ አግኝቷል።

ሌሎቹ ሕዝቦች እንዴት ነበሩ? እግዚአብሔር የእስራኤል ብቻ አምላክ ነው? ኢዮኤል እግዚአብሔር በሌሎች አሕዛብም ላይ እንደሚፈርድ ለእስራኤላውያን ያሳስባቸዋል፥

ኢዮ.3፡1-15። አገላለፁ ሥዕላዊ ይሁን ወይም ቀጥተኛ አባባል ለማወቅ ያስቸግራል፤ ማናቸውም ቢሆን የእግዚአብሔርን ሥራ ያሳየናል።

ቢሆንም የእስራኤል ሕዝብ አልተረሳም። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያስቀመጠው አንድ የተለየ ነገር አለው፥ ኢዮ.3፡16-21 አንብቡ። እነዚያ የእስራኤል ጠላቶች የነበሩት ማምለጫ የላቸውም። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከክፉ ይጠብቃቸዋል። የእግዚአብሔርን ኃይል ከተመለከቱ በኋላ ራሳቸውን ለእርሱ ማስገዛት ያልፈለጉትን ድል ያደርጋቸዋል። በብዙዎቹ የትንቢት መጻሕፍት መጨረሻ ላይ እንደምናገኘው የዚህ መጽሐፍም መደምደሚያ ስለ በረከቶች ነው። ሕዝቡ መጥፎ ቢሆንም ክፋታቸውም ቢባባስ የእግዚአብሔር ዕቅዶች ሊበላሹ አይችሉም፥ ሮሜ 11፡6።

# ኢዮኤል

## የተለዩ ነጥቦች

1. ምንም እንኳን እስራኤልን አንበጦች አዘውትረው የሚያጠቁት ቢሆንም ይኸኛው ወረራ በጣም የከፋ ነበር፥ ኢዮ.1፡2-3 ተመልከቱ። ኢዮኤል ይህን ሁኔታ ሕዝቡን ለመቀስቀሻ ተጠቅሞበታል። ወረራው በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ምንም ሰብል አላስቀረላቸውም ነበር፥ ኢዮ. 1፡11-12፤ 1፡16-20 ተመልከቱ። ይህ ሁሉ ችግር ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ አላደረጋቸውም። ግርፋቱንም ለመቀበል ሽንጣቸውን ገትረዋል።
2. «የጌታ ቀን» መቼ ነው? የመጨረሻውን ፍርድ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ወቅት እግዚአብሔር ኃይሉን በተለየ መንገድ ሲገልፅ ነው፥ ኢዮ.2፡1-11። እግዚአብሔር አሶራውያንን የራሱ መሳሪያ አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል፥ ቁ.11።
3. ልብ ክፉ ነገር ከማድረግ ካልተመለሰ በእግዚአብሔር ፊት ጾም መጾምና ልብስን መቅደድ ምንም አይጠቅምም። ኢዮኤል ይቅርታን ለማግኘት ሥርዓትን መፈጸም በቂ እንዳልሆነ ሊያሳያቸው ሞክሯል፥ ኢዮ.2፡12-17።
4. በምዕ. 3፡1-15 ላይ ኢዮኤል ከጠቀመው የመጨረሻው ፍርድ በፊት እግዚአብሔር ሁለት ምልክቶችን ወይም ማስጠንቀቂያዎችን ለዓለም ይሰጣል። የመጀመሪያው የራሱ ሕዝብ የተለወጠ ኑሮ ነው፥ ኢዮ.2፡28-29። ሁለተኛው ምልክት በምትታየዋ ዓለም ውስጥ የሚደረጉ ለውጦች ነው፥ ኢዮ.2፡30-32። እነዚህ ነገሮች የሚያመለክቱት የመጨረሻዎቹን ዘመናት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በምድር ላይ ከመፍረዱ በፊት የሚያደርገውን ሥራ ነው።
5. በ2ኛ ነገ. 14፡23-29 ላይ እግዚአብሔር በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት እስራኤልን እንደባረካት ተመልክተናል። ይሁዳን ደግሞ በዖዝያን ዘመነ መንግሥት ባርኳታል፥ 2ኛ ዜና 26፡1-23። ሕዝቡ ምን አደረገ? እንዲያውም ከበፊት የበለጠ ኃጢአት ሠርቷል። በኢዮኤል 3፡16-21 ውስጥ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ሕዝቡን በሶስት የተለያዩ መንገዶች ይባርከው ነበር፥ ቁ.16-17፥ ቁ.18፥ ቁ.19-21።

# ኢዮኤል

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. እግዚአብሔር እርሱን እንዳንረሳ ለማድረግ ሁለት የተለያዩ ሥራዎች ይሠራል። ይኸውም:- ይሰጣል፤ መልሶ ይወስዳል። ብዙ ሰዎች ሊያስጠነቅቃቸው ፈልጎ እግዚአብሔር ያላቸውን ሲወስድባቸው ከመጠን በላይ ይተከዛሉ፤ ከአንገት በላይ ከኃጢአታችን ተላቅቀናል ይላሉ፤ ይሁን እንጂ ከሚጥማቸው ኃጢአት ከልብ መላቀቅ አይፈልጉም። እግዚአብሔር ቸርነቱን ለመግለፅ በረከቶች ቢሰጣቸው በትዕቢት ተነፍተው እርሱን ይረሱታል። ኢዮኤል እስራኤላውያንን ስለነዚህ ሁለት ስሕተቶች ያስጠነቅቃቸዋል።
2. እግዚአብሔር ዘወትር ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል። ጆሮአችን ወደ ቃሉ በምናዘነብልበት ጊዜ እነዚህን ማስጠንቀቂያዎች እንረዳቸዋለን። እግዚአብሔር ሰዎችን ምን ሊናገር እንደፈለገ እንገነዘባለን። የእግዚአብሔር ሰዎች ኃጢአት ሲሠሩ ብናያቸው ኢዮኤል በ2፡12-17 ላይ ያደረገውን ማድረግ እንደሚገባን አንርሳ።
3. ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ፍርድ በሚያስጠነቅቅበት ጊዜ ኢዮ. 2፡31ን ተጠቅሟል፥ ማቴ.24፡29፤ ማር.13፡24-25፤ ሉቃ.21፦25፤ በተጨማሪ ራዕይ 6፡12-13 ተመልከቱ። ይህ እግዚአብሔር ከሚሰጣቸው ምልክቶች መካከል አንዱ ነው። ከመጨረሻዎቹ ምልክቶችም ደግሞ አንዱ ነው። ሰዎች ንሥሐ መግባት በጭራሽ እምቢ በሚሉበት ወቅት እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታቸው ምን ማድረግ ይችላል?
4. ኃጢአትና ፍርድ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው፤ እንዲሁም መታዘዝና በረከት አይነጣጠሉም። እግዚአብሔር እርሱን ለማስደሰት ለሚቀኑት ሰዎች የተለየ በረከት ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔርን ማስደሰት ተገቢያችን መሆኑን ስንረዳ ብቻ እንታዘዛለታለን እንጂ በረከቶቹን ስለምንፈልግ አይደለም። እርሱን ማስደሰት ተግባራችን እንደሆነ ስንገነዘብ እኛ ራሳችን ደግሞ በበረከት ተሞልተን እንገኛለን።
5. የእግዚአብሔር ፍቅር መልካም ነገሮችን ብቻ በመስጠት አልተገለፀም። ማስጠንቀቂያዎችም የእርሱ ፍቅር ሌላ ገጽታዎች ናቸው። የኢዮኤል ፍላጎት እስራኤልን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነበረ። በአንዳንድ መንገድ የኢዮኤል መልዕክት ከሆሴዕ ጋር ይመሳሰላል። ሆሴዕ ለሚያደርገው ምልጃ የተጠቀመበት መሠረት የራሱ ቤተሰብ ታሪክ ነው። ኢዮኤል ደግሞ እርሻውን እና የሚያስፈራውን የአንበጦች ወረራ በመጠቀም እስራኤል ለእግዚአብሔር ሕግ ያላትን ተጠሪነት ያሳስባታል።

# ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ያሉት ሶስት ዓይነት ሠራተኞች ማን ማን ናቸው?
2. ለ1ኛ ነገ.12 ርዕስ አውጡለት።
3. ከ931-910 በእስራኤል ይገዛ የነበረው ማን ነበር?
4. ደግማዊ ኢዮርብዓም መሠዊያዎችን ያቆመው የትና የት ነው?

5. ኢዮኤልና ዕንባቆም የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
6. ወደ ነነዌ የተላኩት ማንና ማን ነበሩ?
7. አሶር የይሁዳ ጎረቤት የነበረችው ለስንት ዓመታት ነው?
8. ኢዮኤል የተጻፈው መቼ ነው?
9. ዳግማዊ ኢዮርብዓም የሞተው መቼ ነበር?
10. እስራኤል ለአሶር ማደግደግ የጀመረችው በማን ዘመን ነበር?
11. ኢዮኤልን ከእስራኤል ነቢያት ጋር የምንቆጥረው በምን ምክንያት ነው?
12. ኢዮኤል ነቢይ እንደነበረ የሚያረጋግጠው የ2ኛ ነገ. ክፍል የትኛው ነው?
13. 2ኛ ነገ.17፡7-33 በውስጡ ያዘለው ምንድነው?
14. እስራኤል በማን ተተካች?
15. የአንበጦቹ ትርጉም ምንድነው?
16. በኢዮኤል ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ንግግር ምን ዓይነት ነው?
17. የሐዋ. 2፡ 17-21 የሚያሳየን ምንድነው?
18. ዳግማዊ ኢዮርብዓም እስራኤልን ይመራ በነበረበት ወቅት የይሁዳ ንጉሥ ማን ነበር?
19. መጽሐፉ የሚደመድመው በምንድነው?

# ትምህርት አራት

## መግቢያ

በክፍል አንድ የሚገኙት አራት ትምህርቶች የተፈፀሙት ከ800-700 ዓ.ዓ. መካከል ነው። በዚህ መቶ ዓመታት ውስጥ በእስራኤል ላይ ስምንት ንጉሶች ነግሠዋል፣ እነርሱም፡-

1. ዮአስ 798-783
2. ዳግማዊ ኢዮርብዓም 783-743
3. ዘካሪያ 743
4. ሰሎም 743
5. መናሐም 743-738
6. ፋቂያስ 738-737
7. ፋቁሔ 737-732
8. ሆሴዕ 732-723

የመጨረሻዎቹን ስድስት ነገሥታት ታሪክ ለማግኘት 2ኛ ነገ. 15-16ን ተመልከቱ። በእነዚህ ነገሥታት ዘመን አሶር ከዕለት ወደ ዕለት ብርታት እየጨመረች መጥታለች። አሶር እየበረታች ስትሄድ እስራኤል የሚያስፈራ ደረጃ ላይ እስከምትደርስ ድረስ ኃጢአትዋ ያዳክማት ነበር።

የአሶራውያን ነገሥታት ቅደም ተከተል ከዚህ በታች እንደሰፈረው ነው:-

1. ሳልሣዊ ቴልጌል ቴልፌልሶር 745-727 ዓ.ዓ.
2. ሰልምናሶር - 5ኛ 727-722 ዓ.ዓ.
3. ዳግማዊ ሳርጎን 722-705 ዓ.ዓ.
4. ሰናክሬም 705-681 ዓ.ዓ.
5. አስራዶን 681-669 ዓ.ዓ.
6. አስናፈር 669-627 ዓ.ዓ.

የእነዚህን ነገሥታት ስሞች በሚከተሉት የብሉይ ኪዳን ክፍሉች ውስጥ ማመሳከር እንችላለን።

- ቴልጌል ቴልፌልሶር 3ኛ:- 2ኛ ነገ.15:29፤ 16:7፥ 10፤ 1ኛ ዜና 5:6፤ 5:26፤ 2ኛ ዜና 28:20።
- ሰልምናሶር 5ኛ:- 2ኛ ነገ. 17:3፤ 18:9።
- ሳርጎን:- ኢሳ.20:1።
- ሰናክሬም:- 2ኛ ነገ. 18:13፤ 19:16-20፥ 36፤ 2ኛ ዜና 32:1-2፥ 9-10፥ 22፤ ኢሳ. 36:1፤ 37:17፥ 21፥ 37።
- አስራዶን:- 2ኛ ነገ. 19:37፤ ዕዝ. 4:2፤ ኢሳ.37:38።
- አስናፈር:- ዕዝ.4:10።

# አሞፅ

## ታሪካዊ መግቢያ

ሆሴዕ እና ኢዮኤል የት ይኖሩ እንደነበር የሚያስረዳ ፍንጭ አናገኝም። ምናልባት ያልተጠቀሙበት ምክንያት በእስራኤል ውስጥ በአንዱ አካባቢ ይኖሩ ስለነበር ይሆናል። አሞፅ ግን ትንቢት የተናገረው ለእስራኤል ቢሆንም ተቀማጭነቱ በይሁዳ ነበር። ያደገበት መንደር ቴቁጤ ሲሆን እርሱም ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ 15 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ኢሩኤል ከተባለው በረሃ አፋፍ ላይ ነበር።

የምድር መንቀጥቀጥ የሆነበትን ዘመን አናውቅም፤ ስለዚህ ከዚህ ነጥብ የተነሣ መጽሐፉ የተጻፈበትን ዘመን ለመገመት አንችልም። ኢሳይያስ ለአገልግሎት የተጠራው ንጉሥ ዖዝያን ከሞተበት ዘመን ነበር፥ ኢሳ.6:1። ዳግማዊ ኢዮርብዓም የሞተው ዓርባ ዓመታት በኢየሩሳሌም ከነገሠ በኋላ ከዚህ ጊዜ ሶስት ዓመታት ቀደም ብሎ ማለት በ743 ዓ.ዓ. ነበር። እንደዚህ ከሆነ እንግዲህ አሞፅ ሰማርያ በአሶራውያን ከመያዟ በፊት ቢያንስ በግምት ለ20 ዓመታት ትንቢት ተናግሯል ማለት ነው።

ስለ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት ፍንጭ የሚሰጠን 2ኛ ነገ. 14:23-29 ብቻ ነው። የምናውቃቸው ነገሮች ጥቂትም ቢሆኑ እንኳ መጽሐፉን መተርጎም እንድንችል ይረዱናል። ከ783-743 ዓ. ዓ. ማለት በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት እስራኤል በጣም ሐብታምና ጠንካራ መንግሥት ነበረች። የእግዚአብሔርም ፍርድ ከእስራኤል በጣም

የራቀ መስሎ ይታይ ነበር። ሐብቷና ብርታትዋ በእግዚአብሔር ላይ የተቆጣ መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች አይመስሉም።

አሞፅ በመጽሐፉ ውስጥ አሶራውያንን አለመጥቀሱ በጣም የሚያስገርም ነው። እርሱ በሰሜን ማለትም በእስራኤል እንዳልኖረ እናውቃለን፤ ሆኖም አሶር በ853 ዓ.ዓ. ዝነኛ በሆነው በቃርቃር ጦርነት ደማስቆን እንደወጋች ሳያውቅ አይቀርም፣ 1ኛ ነገ.22፡29-36 ይህን ጦርነት ሳይጠቁም አይቀርም፣ በ843 ዓ.ዓ. እንደገናም በ797 ዓ.ዓ. ደማስቆ ተከባለች። የሶርያ ንጉሥ አዛሄል አሶር ከእርሱ የወሰደቻቸውን ጥቂት መሬት አስመልሶ ነበር። አዛሄል አሶርን የሚደፍር ከመሆኑም በላይ እስራኤልን ደግሞ አልፎ አልፎ ያጠቃ ነበር፣ 2ኛ ነገ.13፡22-25። በዚህ ዘመን ኤልሳዕና ኤልያስ በእስራኤል ትንቢት ይናገሩ ነበር። ዮናስ ደግሞ ወደ አሶር ዋና ከተማ ወደ ነነዌ በእግዚአብሔር የተላከው በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት ነበር።

አሞፅ ከተዘዋወረባቸው ከተማዎች አንዷ ከአብርሃም ጊዜ ጀምሮ ዝነኛ የነበረችው ቤቴል ነበረች፣ ዘፍ.12፡8፤ 33፡1፤ 35፡7። የአሞፅ ተልዕኮ በ1ኛ ነገ.12፡28-13፡32 ላይ ከተገለፀው ከእርሱ ዘመን 200 ዓመታት በፊት ከተፈጸመ ድርጊት ጋር ማወዳደር ይችላል። አሞፅ ስለ ቤቴል የጠቀሰውን ተመልከቱ፣ 4፡4፤ 5፡5-6፤ 7፡13። በአሶራውያን ተልከው ሕዝቡን ሊያስተምሩ የመጡት ካህናት በኋላ ሳምራውያን ተብለው በዚያ ቦታ ሰፍረዋል፣ 2ኛ ነገ.17፡28። በ1ኛ ነገ.12 ላይ የሚገኘው ትንቢት ፍጻሜ ያገኘው ከተነገረ ከ300 ዓመታት ያህል በኋላ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ነበር።

ከ781-740 ዓ.ዓ. የቆየው የዖዝያን ዘመነ መንግሥት ዘገባ በ2ኛ ዜና 26 ውስጥ ሰፍሯል። እርሱም የይሁዳ እንጂ የእስራኤል ንጉሥ አልነበረም። ቢሆንም የእርሱ ዘመነ መንግሥት በዚያ ዘመን ስለነበረው የአይሁዶች ብርታትና ብልፅግና መረጃ ይሰጠናል። በጊዜው ስለነበረው ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ስለሚያስረዱን ከዚህ ቀጥሎ ከሆሴዕ መጽሐፍ የሚቀርቡትን ምንባቦች አንብቡ፣ ሆሴዕ 4፡4-10፤ 5፡4-7፤ 8፡1-14።

# አሞፅ

## የነቢዩ ሸክም

አንድ ሰው በሚያደርገው ሥራ ማንነቱን ያስታውቃል። የሕዝብ ውስጣዊ ሁኔታ በማኅበራዊ ኑሮውና በአስተዳደሩ ይታወቃል።

አሞፅ የእስራኤላውያንን የሃይማኖት አኗኗር ሲመለከት ከአምላካዊው ሥርዓት የራቁትን ልማዶችን አይቷል። እስራኤላውያን በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መቅደስ ባለመሄዳቸው እግዚአብሔር አልተደሰተም። ነገር ግን በዚህ ምክንያት ብቻ እግዚአብሔር አልተቆጣቸውም።

አሞፅ የእስራኤልን ሕዝብ ማኅበራዊ ኑሮ ድካም ይመለከት ነበር፣ 3፡9-4፡3። በግልፅ ይታይ የነበረውም ኑሮአቸው የልባቸውን ዝንባሌ በትክክል ይከሥታል። በሥርዓት አፈጻጸም

ረገድ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እና የሚከተሉ ቢመስሉም እንኳ በማያጠራጥር መንገድ ከእርሱ የራቁ ነበሩ።

ሆሴዕ እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ፍቅር እንዲመለሱ ተማፅኗቸዋል። ኢዮኤል የደረሰባቸው የተፈጥሮ አደጋ ወደ ፊት ለሚደርስባቸው ለከፋ ችግር ምሳሌ እንደሆነ አስተምሯቸዋል። ማኅበራዊ አኗኗራቸው ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያመለክት ስለነበር ለእግዚአብሔር ፍርድ የተዘጋጁ መሆናቸውን አሞፅ ያሳሰባቸው ነበር።

በእስራኤል አገር የነበሩት ባለጠጎችና ኃይለኞች አገሪቱና ሕዝቡ የእነርሱ ንብረት እንደሆኑ ቆጥረውታል። ነገር ግን ሁላቸውም ለእግዚአብሔር መገዛት እንደሚገባቸውና እርሱ እያንዳንዳቸውን ጠርቶ መልስ እንዲሰጡት የሚጠይቃቸው መሆኑን ዘንግተውታል።

እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች በውጭ ለነበሩት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡ መሆናቸውን አስታውሱ! እነዚህም ማስጠንቀቂያዎች የተመረኮዙት በቃል ኪዳኑ ላይ ነው። ሰዎች እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ተስማምተው ነበር፥ ዘፀ. 19፡8። አሁን ግን አውቀው ቃል ኪዳኑን ስለጣሱ የሚጠብቃቸው ፍርድ ብቻ ነው።

በማስጠንቀቂያዎቹ መካከል የንሥሐ ጥሪ እንመለከታለን፥ 5፡1-25። በተጨማሪ ታማኝ ሆነው የሚቆዩትን ጥቂት ሰዎች እግዚአብሔር እንደማይተዋቸው ነቢያቱ ሲያሳስቡዋቸው እንመለከታለን፥ 9፡11-15። ይሁን እንጂ ታማኞቹ ከከፉዎች ጋር ይሰቃያሉ። ሆኖም እግዚአብሔር ታማኞችን አይተውም! በፍጹም አይረሳቸውም። እርሱ በምሕረቱ ይመለስና ያድናቸዋል። አንድ ቀንም ወደ አገራቸው ይመለሳሉ።

አሞፅ አሥሩን የእስራኤል ነገዶች በሚመለከትበት ጊዜ ለመታጨድ የደረሰ ሰብል፥ ለመታለብ የተዘጋጀች ላምና ለመቃጠል የቀረቡ እንጨቶች ይመስሉ ነበር። ከዚህ መዓት የሚያድናቸው የእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ ነው። ነገር ግን ንሥሐ የማይገቡ ከሆነ ያንን ምሕረት ሊያገኙ አይችሉም።

አሞፅ በመጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔርን እንዴት አድርጎ እንደሚያቀርበው አስተውሉ። እያንዳንዱ ሕዝብ ለምሳሌ ፊንቄ፥ ሶሪያ፥ አሞን፥ ሞአብና ኤዶም ሁሉም የራሳቸው ጣኦታት ነበሩአቸው። በተለይ የከነዓናውያን አምላክ በአል ለእስራኤላውያን አደገኛ ነበር። ከዚህ የተነሣ አሞፅ እግዚአብሔርን የሚተካከል ሌላ አምላክ እንደሌለ አጥብቆ ይነግራቸዋል።

# አሞፅ

## ማብራሪያ

አሞፅ 9 ምዕራፎች ቢኖሩትም አጠቃላይ ዕቅዱ በመጠኑ ቀለል ይላል።

የእስራኤል ጎረቤት የሆኑትን፡- ሶሪያ፥ ፍልስጥኤም፥ ጢሮስ፥ ኤዶም፥ አሞን፥ ሞአብንና በመጨረሻም ይሁዳን በመጠቆም ይጀምራል። ነቢዩ ስለ ይሁዳ በምዕ.2፡4-5 ውስጥ ያቀረበው ትንቢት የተፈጸመው ከ200 ዓመታት ያህል በኋላ ነበር። ይህም እግዚአብሔር ይሁዳን ሳይፈርድባት ለ200 ዓመታት ያህል ምሕረቱን እንዳበዛላት ያሳያል።

አሞፅ ስለነዚህ ሰባት መንግሥታት ከተናገረ በኋላ ወዲያው ንግግሩን ወደ እስራኤል ይቀይራል።

እስከ ምዕ. 6 መጨረሻ ድረስ እስራኤላውያንን ይናገራቸዋል። እስራኤል በዚያ ዘመን ሀብታምና ብርቱ እንደነበረች አትዘንጉ። ሕዝቡ ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደሆኑ ተመልከቱ፥ 2፡6-3፡2። በዚህ ምንባብ ውስጥ ስንት ኃጢአት ተጠቅሷል?

አሞፅ ነቢይ መሆን አልፈለገም፤ እግዚአብሔር ስለተናገረውም ዝም ብሎ ለመቀመጥ አልቻለም፥ 3፡3-8። እግዚአብሔር በአፉ ያኖረውን የግድ መናገር ነበረበት።

ንጉሥ ዘምበሪ የቆረቆራት ከተማ ሰማሪያ የእስራኤል መዲና ነበረች። ይህች ከተማ ምን ያህል ሀብታምና ብርቱ እንደነበረች ተመልከቱ፥ 3፡9-4፡3። በዚህ ምንባብ ውስጥ የሰማሪያን ምቾት የሚያመለክቱት የትኞቹ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ናቸው? ሕዝቡ ኃይላቸውንና ገንዘባቸውን ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ለማዋል በመፈለግ ኃጢአትን በኃጢአት ላይ ለመደራረብ ብቻ ያስቡ ነበር።

እግዚአብሔር በመከራና በችግር ሊያስተምራቸው እንዴት እንደሞከረ ኢዮኤል ያሳየናል፤ እነርሱ ግን መማር አልፈለጉም። አሞፅም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፥ 4፡4-13። ችግር እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ አላደረጋቸውም። እግዚአብሔር ቀጥቶአቸዋል፤ እነርሱ ግን መማር አንፈልግም ብለዋል።

ታዲያ አሞፅ ዝም አላቸው? እንዲያውም እስከ መጨረሻው ቀን ማለትም እስከ 722 ዓ.ዓ. ድረስ አብዝቶ ይጠራቸዋል። እስከዚያ ቀን ድረስ ንሥሐ የመግባት ዕድል ነበራቸው፥ 5፡1-2 ተመልከቱ። አሞፅ ኃጢአታቸውን በዝርዝር ስለሚያውቅ ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ብቻ በላያቸው ላይ እንደሚመጣባቸው ይነግራቸዋል።

ኢዮኤል በአንበጦቹ አማካይነት የእግዚአብሔርን ፍርድ ተመልክቷል። አሞፅ በሕዝቡ ኃጢአት አማካይነት የእግዚአብሔርን ቁጣ ተመልክቷል፥ 6፡1-14። 6፡1-14 ፍጻሜ ያገኘው አሞፅ ከተናገረው ከ20 ዓመት በኋላ ሳይሆን አይቀርም፤ ከንቱ ሆኖ ግን አልቀረም። እግዚአብሔር እሠራለሁ ብሎ የተናገረውን አድርጓል።

አሞፅ 8፡4-14 ከ6፡1-14 ጋር በጣም ይመሳሰላል። አሞፅ ለብዙ ዓመታት ሳይሰብክ አልቀረም። ስለዚህ ጎን ለጎን ሰፍረው የሚገኙት ስብከቶቹ በመካከላቸው በግልፅ የብዙ ዘመናት ርቀት ይኖራቸዋል።

በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ታሪካዊ ክፍሉ አንድ ብቻ ነው፥ 7፡10-17። ቤቴል ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን 12 ኪ.ሜ. ብቻ ትርቃለች። በ1 ነገ. 13 የሚገኘውን ታሪክ እንደገና ተመልከቱ። ዳግማዊ ኢዮርብዓም የነገሠው ከ783-743 ዓ.ዓ. ድረስ ነበር፤ ስለዚህ ይህ ታሪክ የተፈጸመው እርሱ ከመሞቱ ከ743 ዓ.ዓ. በፊት መሆን አለበት። ይህም እስራኤል እግዚአብሔርን ለመስማት ፈቃደኛ እንዳልነበረች ያሳየናል።

ትንቢተ አሞፅ አምስት ራዕዮች አሉት:-

1. አንበጦች 7:1-3
2. እሳት 7:4-6
3. ቱምቢ/የውሃ ልክ መለኪያ/ 7:7-9
4. ቅርጫት 8:1-3
5. መሠዊያ 9:1-10

የሁሉም ራዕዮች ትርጉም አንድ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ መሆኑን ያሳያሉ። ፍርዱ ደግሞ የማይቀር ስለሆነ ማንም ሊያመልጥ አይችልም።

ሆኖም የታሪኩ ማከተሚያ ይህ አይደለም፥ ሆሴዕ 13:4-8። በድጋሚ አሞፅ 9:11-15ን እና ኢዮኤል 3:16-21 ተመልከቱ። የእስራኤል ነቢያት እያንዳንዳቸው የሚደመድሙት እግዚአብሔር ገና ወደፊት ለሕዝቡ ምን እንደሚያደርግ በሚያሳይ ተስፋ ነው። ከተናገሯቸውም ትንቢቶች መካከል ጥቂቶቹ ፍጻሜያቸውን እንዳገኙ እናውቃለን። እግዚአብሔር በፍፁም አልረሳቸውም። በ536 ዓ.ዓ. ከባቢሎን ምርኮ አድኗቸዋል። ለብዙ ትውልዶች ዘመናትም ጠብቋቸዋል።

ሕዝቡ ቃል ኪዳኑን ቢተላለፍና እግዚአብሔር ቢቀጣውም ቃሉን ግን አይሰርዝም። አደርግላችኋለሁ ብሎ የሰጣቸውን ተስፋ ያደርግላቸዋል። ቅጣቶቹ እርሱ በእርግጥ የሚጠነቀቅላቸው መሆኑን የሚያሳዩ ዋስትናዎች ናቸው። ሰዎች የተሰጧቸው ቅጣቶች ሲሰጧቸው እግዚአብሔር በእውነት ነቢዩን እንደላከው ይረዳሉ።

# አሞፅ

## የተለዩ ነጥቦች

የብሉይ ኪዳን ካርታችሁን በመጠቀም በ1:3-2:5 የተጠቀሱትን ቦታዎች ትክክለኛ ሥፍራ ለይታችሁ እወቁ። ከእነዚህ አገሮች መካከል ብዙዎቹ በአንድ ወይም በሌላ አቅጣጫ እስራኤልን እንደሚጎራበቷት ተገንዘቡ። የእያንዳንዱን ሕዝብ ታሪክ አስታውሱ። በዚህ ምንባብ ውስጥ ከተጠቀሱት አገሮች ስንቶቹ እስከዛሬ በብሔር ደረጃ ይገኛሉ? ፍልስጥኤም የሚለው ቃል ሁለት የተለያየ ትርጉም ያለው መሆኑን አትርሱ። እግዚአብሔር እያንዳንዳቸውን ደምስሷቸዋል።

እግዚአብሔር እስራኤልን ድል አድራጊ እንድትሆን መርጧታል። እዚህ ላይ ግን የምንመለከተው እስራኤል በየአቅጣጫው ስትሸነፍ ነው፥ 4:4-13፤ 6:1-14፤ 8:4-14። የእግዚአብሔር ዕቅድ አልተጨናገፈም፤ ደግሞም አልተለወጠምም። እስራኤል ግን እግዚአብሔር ሊሰጣት የፈለገውን በረከቶች በራስዋ መንገድ ልታገኛቸው ስለፈለገች አጥታቻቸዋለች።

አሞፅ ወደ አገልግሎቱ የመጠራቱን ሁኔታ ሲዘረዝርልን የጥሪው አቀራረብ ከኢሳይያስና ከኤርምያስ ልዩ መሆኑን ይገልጻል፥ ኤር. 1ንና ኢሳ.6ን ተመልከቱ። ሰስታቸውም እግዚአብሔር ለሥራው እንደጠራቸው እርግጠኞች ናቸው። ለመናገር የተገደዱት

እግዚአብሔር ቃሉን ስለሰጣቸው ነበር። አሞፅ ለምን ያህል ጊዜ እንደተናገረ አይታወቅም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለቃሉ እንደመረጠው እርግጠኛ ነበር፣ 1፡2 ተመልከቱ።

ሰዎች የልባቸውን ሁኔታና ዓላማ እንዲገልጡ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ሰጥቶአቸዋል። በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ የተቀደሱት ሥርዓቶቹ ትልቅ ዋጋና ትርጉም ነበራቸው። ሆኖም 5፡1-27 እንደሚያሳየን ሥርዓቶች ትርጉም የለሽ ሽፋን ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። የተቀደሱት ሥርዓቶች ከሥነ ምግባራዊ ለውጦች ጋር አብረው የማይሄዱ ከሆነ ጥቅመቢስ ሆነው ይገኛሉ። አሞፅ ምዕ.5 የአይሁድን ሥርዓት ሙሉ በሙሉ እንደሚያወግዝ ተደርጎ መቆጠር የለበትም።

የአምስቱ ራዕዮች መሠረታዊ ትርጉም አንድ ዓይነት ነው። የያዙት ትንቢት በ722 ዓ.ዓ. የተፈፀመ መሆኑን እናውቃለን። አሞፅ በእያንዳንዱ ራዕይ ውስጥ ፍርዱ የተቃረበና የማይቀር መሆኑን ያሳስባቸዋል። ሕዝቡ ከእነዚህ ራዕዮች ውስጥ ለራሳቸው የሚያስፈልጓቸውን ትምህርቶች ሳይቀስሙ እንዳልቀሩ እናውቃለን።

በ9፡11-15 ውስጥ የሚገኘው ትንቢት ሶስት ዓይነት የአፈጻጸም ደረጃ ሊኖረው ይችላል። ሕዝቡ በ536 ዓ.ዓ. ከምርኮ ወደ ይሁዳ ተመልሰዋል። የሐዋ.15፡16-18 እንደሚያሳየን እነዚህ ቃሎች አማኞችንም ደግሞ ይመለከታሉ። እግዚአብሔር አሁንም ለሕዝቡ የተሻለ ነገር ለማድረግ በማቀድ ላይ ሊሆን ይችላል። ትንቢቱ ሰፊ በመሆኑ በአንዱ ትርጉም ብቻ ይወሰናል ለማለት አይቻልም። ስለዚህ የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ልብ አድርገን እናስላስላቸው፡-

1. ትንቢቱ አንድ ጊዜ ተፈጽሟል፣ ስለዚህ ሌላ ትርጉም አይኖረውም ብለን እንዳናስብ መጠንቀቅ አለብን።
2. ታሪካዊውን እና ትንቢታዊውን ትርጉም ብቻ በመውሰድ ምንባቡ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ሥራ የሚያስተምረውን ትምህርት እንዳንተወው እንጠንቀቅ። ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ራሳችንን እንዲህ ብለን መጠየቅ ይኖርብናል! ይህ ትንቢት ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረኛል? እግዚአብሔር ስለራሱስ የሚናገረው ምንድነው?

# አሞፅ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

በሰላም ተቀምጠው እግዚአብሔርን የማያስቡትን በርካታ ብሔሮች ስንመለከት እርሱ ረስቷቸዋል ብለን መገመት ቀላል ነገር ነው። የዮሐንስ ራዕይ ለዚህ ችግር የተሟላ መልስ ይሰጠናል። በተጨማሪ የዕንባቆምን ትንቢት ተመልከቱ። የእግዚአብሔር ጊዜ የእኛ ላይሆን ይችላል! ነገር ግን የእርሱን ፍርድ ያላቃለሉትን በፍፁም አይተዋቸውም።

ሮሜ 8 እንደሚያሳየን በአዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን ሕዝቦቹ ለእርሱ ብቻ እንዲገዙ የእግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑን ያሳያል። ሕዝቡ በሙሉ እስራኤል እንዲሆኑ ይፈልጋል! ይኸውም እስከድል አድራጊነት ድረስ የታገሉትን ነው። ኃጢአት ክርስቲያንን ቢያጠቃውም

እግዚአብሔር ዘወትር መውጫ ይሰጠዋል፥ ሮሜ 7 ተመልከቱ። ሰባት ጊዜ እንኳን ልንወድቅ ብንችልም ሰባት ጊዜ ተነሥተን ጉዞአችንን እንቀጥላለን።

ኢየሱስ 12 ሐዋርያት እንዲከተሉትና እንዲያገለግሉት መርጧል። ወደ ሌሎች የዓለም ክፍሎች ሄደው ወንጌልን እንዲሰብኩ የጥንቲቷ ቤተ ክርስቲያን ሰባክያንን መርጣለች፥ የሐዋ.13። እነዚህ አንድ ቡድን ብቻ ናቸው። ነገር ግን ሌሎች ክርስቲያኖችም ልክ አሞፅ እንዳደረገው የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው እርሱ በመደባቸው ሥፍራዎች ተገኝተው ሊያገለግሉት ይችላሉ። እንደ አሞፅ ለልዩ አገልግሎት የተለየ ጥሪ የተቀበሉ ሰዎች ለየት ያለ ጥሪ ያልተቀበሉት ሰዎች በቤታቸውና በመሥሪያ ቤታቸው የሚሰጡትን አገልግሎት አይሻሙአቸውም።

እንደ መዘመር፥ ጸሎት፥ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ወዘተ የመሳሰሉት ውጫዊ ምልክቶች የልባችንን የውስጥ ስሜቶች ለማሳየት ስለሚያስችሉን አስፈላጊያችን ናቸው። ሆኖም ልባችን ንጹሕ ካልሆነና እግዚአብሔር ያዘዘንን ለማድረግ ዝግጁ ካልሆንን እነዚህ ነገሮች በሙሉ ጥቅም አይሰጡንም። ሆኖም ግንኛውም ውጫዊ ድርጊት የውስጣችንን ስሜትና ዓላማ የግድ ያሳያል፤ ስለዚህ እንጠንቀቅ፤

የእግዚአብሔርን መልዕክት እንድንረዳ ማስተዋል የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። የእስራኤል ሕዝብ አምስቱን ራዕዮች አዳምጠዋል። ነገር ግን ምንም ለውጥ አላሳዩም፤ ንስሐም አልገቡም። ስለዚህ በ722 ዓ.ዓ. በአሶራውያን ተማርከዋል። ዘወትር ቃሉን ስንሰማ እግዚአብሔር ትርጉሙን ለልባችን ግልፅ እንዲያደርግልን እንጸልይ። እግዚአብሔር በመልዕክቶቹ አማካይነት ምን እንደሚል ማስተዋል ያሻናል።

እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይለወጥ ቃሉም አይለወጥም። ቃሉ ዘወትር አዲስ ስለሆነ ትርጉሙን በምናነብበት ወቅት ሁሉ አዲስ ነው። በአሞፅ ትንቢት ውስጥ የተጠቀሱት ተስፋዎች በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ለኖሩት ሰዎች ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ዛሬም ለምንገኘው ለእያንዳንዳችን ጭምር ነው፥ 1ኛ ጢሞ.1፡12 ተመልከቱ። በማንኛውም ጊዜ ስታነቡ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፡- ጌታ ሆይ ተናገረኝ፤ እኔ ባሪያህም አደምጣለሁ። መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክና የመልክዓ ምድርን አቀማመጥ አያስተምረንም። ነገር ግን እርሱ እንዲያስተምረን ካልጠየቅነው መልዕክቶቹ ልባችንን በፍጹም አይነኩትም።

## ጥያቄዎች

1. በክፍል አንድ የሚገኙ አራት ትምህርቶች የሚያጠቃልሉዋቸው ዘመናት የትኞቹ ናቸው?
2. ዳግማዊ ኢዮርብዓም የነገሠው ምን ያህል ዓመታት ነው? መቼ?
3. ከዳግማዊ ኢዮርብዓም ሞት በኋላ ሰማሪያ በ722 ዓ.ዓ. ከመውደቋ በፊት በእስራኤል ስንት ነገሥታት ነበሩ?
4. የ6 የእስራኤል የመጨረሻ ነገሥታት ታሪክ የምናገኘው የት ነው?
5. ሰማሪያን ለ3 ዓመታት የከበባት የአሶር ንጉሥ ማን ነበር?
6. ሰማሪያን አሸንፍኩት ያለው የአሶር ንጉሥ ማን ነበር?

7. በ702-701 ዓ.ዓ. ይሁዳን ከወረረ በኋላ ኢየሩሳሌምን የያዛት የአሶር ንጉሥ ማን ነበር?
8. የመጨረሻውና ዝነኛው የነበረው የአሶራውያን ንጉሥ ማን ነበር?
9. ቴቁሔ የምትገኘው የት ነው?
10. አዳርያስ የሞተው መቼ ነበር?
11. የዳግማዊ ኢዮርብዓም ታሪክ የሚገኘው የት ነው?
12. በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን እስራኤላውያንን ያኩራሩዋቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
13. በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ወደ ነነዌ የተላከው ማን ነበር?
14. ከአሞፅና ከሆሴዕ በፊት በእስራኤል ያገለገሉት ሁለት ነቢያት እነማን ናቸው?
15. 1ኛ ነገሥት 12ና አሞፅ 7 የሚመሳሰሉት በምንድነው?
16. በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን የይሁዳ ዝነኛ ንጉሥ ማን ነበር?
17. የእስራኤል ማኅበራዊ ኃጢአት የሚጠቁመን ምንድነው?
18. የአሞፅ 2፡4-5 ትንቢት የተፈፀመው መቼ ነበር?
19. ሰማርያ የእስራኤል ዋና ከተማ እንድትሆን የመረጣት ማን ነበር?
20. አሞፅ ከባዱን ፍርድ የጠቆመው በምንድነው?
21. በአሞፅ ውስጥ ስንት ራዕዮች አሉ?
22. እነዚህ ራዕዮች በሙሉ የሚጠቁሙት ምንድነው?
23. ኤር.1፤ ኢሳ.6ና አሞፅ 3 በጋራ የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው?

# ክፍል ሁለት

## ትምህርት አምስት

### የይሁዳ ነቢያት

በትምህርት አምስት እና ስድስት ውስጥ ሶስት መጻሕፍት እናጠናለን። እነርሱም ሚክያስ፥ ሰፎንያስና ዕንባቆም ናቸው። ኢሳይያስና ኤርምያስ ደግሞ ለይሁዳ ተናግረዋል። ይሁዳ የሚይዘው ሁለት ነገዶችን ብቻ ነው። ይሁዳ ትገኝበት የነበረውን አካባቢ ለማወቅ ከዚህ በታች የሚገኘውን ካርታ እዩ።




የይሁዳ ታሪክ ከ931 ዓ.ዓ. ማለት ከሰለሞን ሞት አንሥቶ እስከ 586 ዓ.ዓ. እስከ የኢየሩሳሌም ውድቀት ድረስ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። ከ931 ዓ.ዓ. አንሥቶ እስከ 740 ዓ.ዓ. የአዝያን ሞት ድረስ ማለት ለ200 ዓመታት በይሁዳ ምድር የሚጽፉ ነቢያት አልነበሩም።

ኢሳይያስና ሚክያስ የተናገሩት በተመሳሳይ ዘመን ነበር፤ እነርሱ የመጀመሪያዎቹ ለይሁዳ የተናገሩ ጸሐፊ ነቢያት ነበሩ።

ከኢሳይያስ ሞት ማለትም ከ700 ዓ.ዓ. አንሥቶ እስከ ንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን ማለት ለ75 ዓመታት በይሁዳ ምድር ምንም ነቢያት አልነበሩም። ወዲያው በድንገት ሶፎንያስ ብቅ ብሏል።

ዕንባቆም የተናገረው በኢየሩሳሌም ውድቀት አካባቢ በ586 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር።




በዚህ ዘመን ብዙ ሌላ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ተፈጽመዋል። የሚቀጥሉትን ትምህርቶች በምናጠናበት ጊዜ እነዚህን ነገሮች በአዕምሮአችን መያዝ አለብን።




ከዘንበሪ ዘመነ መንግሥት አንሥቶ 885-874 ዓ.ዓ. እስከ 606 ዓ.ዓ. ድረስ አሶር በዓለም እጅግ ታላቅ ነበረች።




አሶር ከወደመ ከ20 ዓመታት በኋላ ማለት በ586 ዓ.ዓ. የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን አጠፉ። የአሶር መንግሥት ተሸንፎ በባቢሎን እንዴት እንደተተካ መረዳት አስፈላጊ ነው።

# ሚክያስ

## ታሪካዊ አቀማመጥ

ኢሳይያስ መተንበይ የጀመረው አዝያን በሞተበት ዘመን በ740 ዓ.ዓ. ነበር። የአዝያን ልጅ ኢዮአታም ለ16 ዓመታት ነግሷል፥ 2ኛ ዜና 27፡1። የእርሱ ልጅ አካዝ ደግሞ ለ20 ዓመታት ነግሷል። ታሪኩን በኢሳ.7 ውስጥ እናገኘዋለን። የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ ለ29 ዓመታት በኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበር። ስለዚህ ሚክያስ የተናገረው በ740ና 687 ዓ.ዓ. መካከል ማለት ንጉሥ ሕዝቅያስ እስከ ሞተበት ዘመን ድረስ ነው ማለት እንችላለን። ኢሳይያስ የተናገረው በኢየሩሳሌም ከተማ ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ሲሆን ሚክያስ የተናገረው በተለይ በገጠር ለሚገኙት ነበር፥ 2፡1-13፤ 6፡6-16።

2ኛ ነገሥትና 2ኛ ዜና ሁለቱም የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ይነግሩናል። 2ኛ ዜና ጠለቅ አድርጎ ስለሚነግረን ለጊዜው እርሱን እንመልከት።

| | | |
|---|---|---|
| 2 ዜና 26 | አዝያን<br>መልካም ንጉሥ | 781-740 ዓ.ዓ. |
| 2 ዜና 27 | ኢዮአታም<br>መልካም ንጉሥ | 740-736 ዓ.ዓ. |
| 2 ዜና 28 | አካዝ<br>ክፉ ንጉሥ | 736-716 ዓ.ዓ. |
| 2 ዜና 29-31 | ሕዝቅያስ<br>መልካም ንጉሥ | 716-687 ዓ.ዓ. |

ኢዮአታም ከ740-736 ዓ.ዓ. ድረስ ማለት ለአራት ዓመታት በኢየሩሳሌም ከተማ ስፈ ጥገና አድርጓል፥ 2ኛ ዜና 27፡3-4። በተጨማሪ የአሞንን ንጉሥ አሸንፎ ብዙ ትርፍ አግኝቷል፥ 2ኛ ዜና 27፡5-6። ይሁዳም ኃይለኛና ሀብታም ሆናለች። በተጨማሪም ኢዮአታም መልካም ንጉሥ ነበር።

አካዝ ለ20 ዓመታት በኢየሩሳሌም ነግሷል። የአካዝ ትልቅ ስሕተት እስራኤልንና ሶርያውያንን በመፍራት ከአሶር ጋር የቃል ኪዳን ስምምነት ማድረጉ ነበር። የእርሱ መንፈሳዊ ብልሹነት በ2ኛ ዜና 28፡1-4 በዝርዝር ተገልጿል። እስራኤል በይሁዳ ላይ ታላቅ አደጋ አድርሳባት 200000 ሰዎች ማርካባታለች፥ 2ኛ ዜና 28፡5-8 ተመልከቱ። ኦዴድ የተባለው ነቢይ እስራኤላውያን ምርኮኞችን እንዲመለሱ ነግሯቸዋል፥ 2ኛ ዜና 28፡9-15። ኤዶማውያንና ፍልስጤማውያን ይሁዳን ወረዋታል። አሶራውያንም ደግሞ ተነሥተውባቸው አካዝን ከፍተኛ ግብር እንዲከፍል አስገድደውታል፥ 2ኛ ዜና 28፡16-21 አንብቡ። ይህም ድርጊት ወደ ታላቅ መንፈሳዊ ብልሽት አድርሷቸዋል፥ 2ኛ ዜና 28፡22-25።

ሕዝቅያስ መልካም ንጉሥ ስለነበር ለእርሱ ታሪክ 3 ምዕራፎች ተሰጥተዋል። በመጀመሪያ ቤተ መቅደሱን አንፅቷል፥ 2ኛ ዜና 29፡1-17። ቀጥሎም ሕዝቡን ሁሉ ሰብስቦ እንደገና ለእግዚአብሔር አቅርቧቸዋል፥ 2ኛ ዜና 29፡18-36። ሰዎች ለብዙ ዘመናት ፋሲካውን አላከበሩም ነበር። ሕዝቅያስ ያደራጀው የበዓሉ ሥርዓት በ2ኛ ዜና 30፡1-27 ተገልጿል። ከዚህ ቀጥሎ በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ማደስ ችሎ ነበር፥ 2ኛ ዜና 31፡1-19 አንብቡ።

በእነዚህ ላይ በተጠቀሱት በሶስት የይሁዳ ነገሥታት ዘመን ሚክያስ በደቡብ ለሚገኙት ሕዝቦች ሰብኮላቸዋል።

| እስራኤል | ይሁዳ |
|---|---|
| አሞፅ<br>ሆሴዕ<br>ኢዮኤል | ኢሳይያስ<br>ሚክያስ |

# ሚክያስ

## የነቢዩ ሸክም

የአሞፅና የሚክያስ ትንቢቶች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም የሚያተኩሩት ከመሪዎች ይልቅ በሕዝቡ ኃጢአት ላይ ነው። ሚክያስ ስለ መሪዎች ይናገራል። ለምሳሌ ምዕ.3፡1-12 ተመልከቱ። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ያጠፋው በሕዝቡ ኃጢአት ላይ ነው። እርሱ የሚናገረው ለደቡብም ለሰሜንም ክፍል እንደነበር ተጠንቅቃችሁ አስተውሉ፥ 1፡1። እንደዚህ ከሆነ አብዛኛዎቹ እርሱ የተናገራቸው ነገሮች ሰማሪያ ከመደምሰሰዋ ከ722 ዓ.ዓ. በፊት ተፈጽመዋል። ሆኖም ብዙዎቹ የእርሱ ትንቢቶች የተነገሩት ለደቡብ ክፍል ነበረ።

ጠቢዩ አዕምሮ ውስጥ ሶስት ነገሮች በአንድነት ተጣምረዋል። እነርሱም ቃል ኪዳኑ፥ አለመታዘዝና ፍርድ ናቸው። የእስራኤልና የይሁዳ ኃጢአቶች ከባድ የሆነበት ምክንያት ይህ ነው። ሁሉም ሰው ኃጢአት ይሠራል። እግዚአብሔር አስቀድሞ በአሪት ውስጥ ለኃጢአት መፍትሄ ሠጥቶ ነበር። ንሥሐና ይቅርታ በተለያዩ መስዋዕቶች አማካይነት ተገልፀው ነበር። ሆኖም በማወቅ ሆን ተብሎ ለሚሠራ ኃጢአት ምንም መስዋዕት አልነበረም።

እስራኤልና ይሁዳ ሆን ብለው ኃጢአት መሥራታቸው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን መርሳታቸውን ያመለክታል። ይህም ማለት እንግዲህ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ መሠረት ይፈርድባቸዋል። ኃጢአት ማለት ጥፋት ማለት ነው። ነቢያት በተለይም አሞፅና ሚክያስ ይህንን ነገር ግልፅ በሆነ መንገድ ተመልክተውታል። በሚክያስ ከሚገኙት ሰባት ምዕራፎች ውስጥ የሕዝቡን ኃጢአት የሚዘረዝሩትን ምንባቦች በአንድ ላይ ሰብስቡአቸው።

አሞፅ ስለ ተስፋ አንድ ግልፅ የሆነ ምንባብ አለው፥ አሞፅ 9፡11-15። በሚክያስም ውስጥ ቢያንስ 2 ምንባቦች ይገኛሉ። ሚክ.4፡1-4፤ 5፡2-4። በሚክያስ ትንቢት የአሁን ጊዜና የወደፊቱ በአንድ ላይ ተያይዘዋል። ልክ የአንድ ዛፍ ግንድ በዘሩ ውስጥ እንደሚደበቅ የወደፊቱ በአሁኑ ጊዜ ውስጥ ተደብቋል።

ሚክያስ በተጨማሪ ሌላ ነገር ተመልክቷል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ቃሉን፥ ዕቅዱንና አስተሳሰቡን እንደማይለውጥ ነው። ሕዝቡ ሊበታተኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር

ዕቅድ አይሰናከልም። ሊዘገይ ይችላል፤ ይሁን እንጂ ጥቂት ሰዎች መሲሁ በሚመጣበት ወቅት እንዲቀበሉት እርሱ ያዘጋጃል። ስለዚህ በሚክያስ መጽሐፍ ውስጥ ፍርድና ተስፋ ጎን ለጎን ሆነው እናገኛለን።

ሚክያስ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚገልፁ ሁለት ምንባቦች አሉት፥ ሚክ.6፡6-8፤ 7፡18-20። ሆኖም ሕዝቡን በብዙ ለንሥሐ አይጠራቸውም፥ ማለት ሆሴዕ እንዳደረገው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ አይጠራቸውም። በሰማሪያ ላይ በ722 ዓ.ዓ. የሚደርሱትን በኢየሩሳሌም ላይ ደግሞ በ586 ዓ.ዓ. የሚመጡትን ፍርዶች ይመለከት ነበር። ነገር ግን እንደ ኢዮኤል ሥዕላዊ በሆነ መንገድ አላሳያቸውም ነበር።

ሚክያስ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚገባው አሳስቦ ነበር። ሰዎችም የቃል ኪዳኑ ግዳጅ ምን እንደሆነ ተረድተው ነበር። ማንም አላስተማረንም ሊሉ በፍፁም አይችሉም።

# ሚክያስ

## ማብራሪያ

ሚክያስ ትንቢቱን የሚጀምረው ለኢየሩሳሌምና ለሰማሪያ በተለቀሰ የልቅሶ ሙሾ ነው፥ ሚክ. 1፡1-9 ተመልከቱ። ሰማሪያ የባሰች ኃጢአተኛ ናት በማለት ኢየሩሳሌም ታስባለች። ሚክያስ ሁለቱንም በአንድ ሥፍራ ያስቀምጣቸዋል።

ሚክያስ 1፡10-16 ትንቢታዊ ይሁን ወይም ታሪካዊ አናውቅም፤ ከሁለቱ አንዱን ዓይነት ሊሆን ይችላል። በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጣው ፍርድ የማይቀር እንደሆነ ያመለክታል።

ሚክያስ እንደ ኢሳይያስና ኤርምያስ የከተማ ነዋሪ ሳይሆን የገጠር ሰው ነበር። አሞፅ ደግሞ ገበሬ ነበር። በኢዮአታም ዘመን ሕዝቡ ሀብታም ሆኖ ነበር። በሚክ.2፡1-13 ላይ እንደምንመለከተው ሀብታሙ ከድሀው ላይ መሬት ይቀማ ነበር። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደተወ ሊያመለክት ይችላል።

እንደ አካዝ ያሉት መሪዎች፥ እንዲሁም አንዳንድ ነቢያትና ካህናት ከአካዝ አይሻሉም ነበር። እነርሱም ቢሆኑ እንኳ የሚያተኩሩት በግል ጥቅማቸው ላይ ነበር። ዘካሪያስ በ518 ዓ.ዓ. እንደተናገረው ዓይነት መሪዎች ናቸው፥ ዘካ.11 አንብቡ። እግዚአብሔር ለሚክያስ ትክክለኛውን ነገር ለይቶ ማወቅ እንዲችል ብሩህ አዕምሮ ሰጥቶት ነበር። የመሪዎች ስሕተት ሊወስዳቸው የሚችለው ወደ ጥፋት ብቻ ነበር፥ ሚክ.3፡1-12።

ሚክያስ 4፡1-5 ከኢሳ.2፡1 ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም በአንድ ወቅት የሰበኩ መሆናቸውን አስታውሱ። እግዚአብሔር በሁለቱም ውስጥ በተመሳሳይ ዘመን አንድ ዓይነት መልዕክት አስተላልፎባቸዋል። ሚክያስ የሚመለከተው ከእርሱ ዘመን በጣም ተሻግሮ ነው። ያገለገል የነበረው የራሱን ዘመን ሰዎች ሳይሆን ከእርሱ ብዙ መቶ ዓመታት ርቀው የሚገኙት ትውልዶች ነበር። የክርስቶስን መምጣትና የአዲስ ዓይነት መንግሥት መቋቋም ይነግራቸው ነበር።

ከዚያም ሚክያስ አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ መቼ እንደሚመለሱ ይተነብያል። ይኸውም 536 ዓ.ዓ. ነበር፡ ሚክ.4:6-13፤ ዕዝራ 1-6 እንደሚያሳየን ይህ ትንቢት ተፈጽሟል።

ሚክ. 3 እንደሚያሳየን የዘመኑ መሪዎች ተበላሽተው ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር አዲስ መሪ ይሾማል፡ ሚክ. 5:1-5፤ ማቴ.2:6፤ ዮሐ. 7:42 አንብቡ። የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብሔርን ይከዱት ይሆናል፤ ነገር ግን እርሱ አይተዋቸውም። ቃል ኪዳኑንም ይቃወሙ ይሆናል፡ ነገር ግን እርሱ ቃል ኪዳኑን አያፍርም።

ምናልባት ሚክ.5:5-15 በ702 ዓ.ዓ. ከተፈፀመ በኢሳ.36-39 ውስጥ ከሚገኘው ትንቢት ጋር አንድ ይሆን ይሆናል። እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት ተስፋ እንደገባላቸው አሶር ኢየሩሳሌምን በፍጹም አልረታትም። የይሁዳ በአሶር መወረር ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነበር። ነገር ግን እነርሱ አላስተዋሉትም። ስለዚህ በ586 ዓ.ዓ. በባቢሎን ተሸንፈዋል። የምዕ.5:5-15 ሁኔታ በ2ኛ ነገ.17 ከተዘረዘረው ታሪክ ጋር ሳይመሳሰል አይቀርም።

እግዚአብሔር እስራኤልን የሚወነጅላት እንዴት ነው? ሚክ.6:1-5 አንብቡ። ከይሁዳና ከእስራኤል ጋር ውል ስለነበረው ነው። ይህ ምንባብ በኢሳይያስ 1 ውስጥ ይሁዳ ቃል ኪዳኑን ስላሰበረች ጌታ የከሰሳትን ክስ ደግሞ ያስተጋባል።

የሕዝቡ ዝንባሌ በከፋ ኑሮአቸው ተገልጧል፡ 6:9-16ን በማንበብ ምን ያህል አጭበርባሪዎች እንደሆኑ አስተውሉ። አንድ ሥራ የሚሠሩ ያስመስሉ ነበር፤ ነገር ግን የሚያደርጉት የተለየ ነው። ሚክ.6:6-8 ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ሰላም መፍጠር እንደሚችሉ ይነገራቸዋል? ይህ ነገር የተጻፈው በቃል ኪዳኑ ውስጥ ለነበሩት እንደሆኑ አስተውሉ።

ሚክያስ የተመለከተው የትኛውንም አካባቢ ቢሆን ማጭበርበርን ያገኛል። የሕዝቡ ልብ ጠማማ ስለነበር የሚያደርጉት ሁሉ እንደዚሁ ጠማማ ነበር፡ 7:1-7 አንብቡ። ይህም ማርቆስ 7:21-22ን ያስታውሰናል።

ባቢሎናውያን በ586 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን አፍርሰዋታል። እግዚአብሔር ባቢሎንን ባሸነፈው በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ አማካይነት ሕዝቡን አድኗቸዋል። በኋላም ግሪኮች በ333 ዓ.ዓ. ፋርስን አሸንፈዋል። የይሁዳ ጠላቶች እንደሚሸነፉ የሚናገረው በሚክያስ 7:8-9 ላይ የሚገኘውን ትንቢት ዕውነተኛነት የዓለም ታሪክ ያረጋግጣል።

መጽሐፉን በጸሎት የሚደመድም ነቢይ ሚክያስ ብቻ ነው፡ 7:14-20። በተጨማሪ ሚክያስ የይሁዳን ኃጢአት ቢገልጥም እንኳ ስለ እግዚአብሔር ሩህሩህ የሆነ ፍቅር፡ እንክብካቤና ሕዝቡ ወዲያው በእውነተኛ ንስሐ ወደ እርሱ ቢመለሱ ይቅር ሊላቸውሙሉ ፈቃደኛ እንደሆነ ይነገራቸዋል። ሚክያስ 7:18-20 ከወንጌል የተወሰደ ምንባብ ይመስላል። በቃላችን ብናጠናው ይጠቅመናል።

# ሚክያስ

## የተለያዩ ነጥቦች

ሚክያስ ስለ ነቢይነቱ በጥሪው ውስጥ ምንም ባይነግረንም እንኳ የእግዚአብሔር ኃይል ሕይወቱን እንዲለውጥለት ብዙ ነገሮችን ተለማምዷል። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ለማዳንና ይቅር ለማለት ያለውን ምኞትና ዕቅድ አጥብቆ ይነግረናል፥ 6:6-8፤ 7:14-20። የይሁዳ ሕዝብ ይህንን ነገር ተቀብለው ቢሆን ኖር ባቢሎናውያን ባልማረኳቸውም ነበር።

ነቢዩ አሁን ሁኔታውን ሲመለከተው አስደንጋጭ ይሆንበት ይሆናል፤ ነገር ግን የወደፊቱንም የአሁኑንም ሁኔታ ይመለከት ነበር። ሕዝቡ ኃጢአትን እየተለማመዱ ስለነበር ፍርድ ይጠብቃቸዋል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለእነርሱ ሌላ ዕቅድ ደግሞ ነበረው፥ 4:1-5፤ 5:1-5 ከወንጌል ታሪክ እንደምንረዳው ይህ ሁኔታ ተፈጻሚነትን ያገኘ መሆኑን እናውቃለን፤ ሆኖም ሌሎች ፍጻሜአቸውን የሚጠብቁ ትንቢቶች አሁንም አሉ።

ሚክያስ ስለ ፍርድ ይሁዳን ይናገራት የነበረው ነገር ባቢሎን በ586 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን ስትደመስሳት ተፈጽሟል፥ ሚክ. 1:10-16፤ 5:6-15 በተጨማሪ በ2ኛ ነገ. 25ና ኤር. 52 ላይ የሚገኙትን ታሪኮች አንብቡ። እነዚህ ታሪኮች እግዚአብሔር በባሪያው አማካይነት የተናገረው እውነተኛ እንደነበረ ያሳዩናል። ሚክያስ ይህ ድርጊት ከመፈጸሙ ከ150 ዓመታት በፊት እንደተናገረው አስታውሱ።

ሚክያስ የተቃረበውን የኢየሩሳሌምን ውድቀት ይመለከት ስለነበር ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ብዙ ይናገር ነበር፥ 2:1-13፤ 1:2-9፤ 6:9-16። እርሱ ይተነብይ በነበረበት ወቅት ሰማሪያ በአሦራውያን ተደምስሳ ነበር፤ ይኸውም በ722 ዓ.ዓ. ነበር። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ያለ ምንም ምክንያት እንዳልፈረደባት ለማሳየት የእነርሱን ኃጢአት ይጠቅስ ነበር። ይህ ነገር የይሁዳ ሕዝብ ንስሐ በመግባት እንዲድኑ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል።

ሚክያስ ኃጢአትንና ፍርድን ተመልክቷል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ተስፋ እንዳላቸው ደግሞ ያውቃል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በፍጹም አይጥላቸውም፥ 4:6-13፤ 6:8-13። ብዙ ምሁራን አንድ ነቢይ ስለ ፍርድና ተስፋ በአንድነት እንዴት ሊናገር ይችላል ብለው ስለሚያስቡ ይህንን መቀበል ይቸገራሉ። እነዚህ ምሁራን ነቢይ የሚናገረው የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንደሆነ ዘንግተዋል። እነዚህ ዕቅዶች ዘወትር የሚመረኰዙት ከሰው ድርጊት በላይ በሆነ ነገር ላይ ነው።

ክርስትና ታሪካዊ መሠረቶች አሉት። ስለዚህ የተደረጉትን ነገሮች ከትርጉማቸው በስተቀር ከታሪክ ማረጋገጥ ይቻላል። ሚክያስ ደግሞ የሚናገረው በቀድሞ ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን እንዳደረገለት ነው፥ 6:1-5 አንብቡ። የእግዚአብሔር የቀድሞ ዘመን ሥራ አሁንም ለክርስቲያን ጠቃሚ ነው። እርሱ አይለወጥም። ስለዚህ ወደፊት የሚሠራው ሥራ ከቀድሞ ሥራው ጋር የተጣመረ ነው።

# ሚክያስ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

በብሉይ ኪዳን ታትዶ የነበረው ደህንነት በአዲስ ኪዳን ተፈጽሟል። ተፈጽሟል የሚለው ዘይቤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ይገኛል። ይህ የሚያመለክተው ከፍርድ ነጻ መውጣትን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ከማንኛውም የኃጢአት ሁኔታ የማዳን ችርነቱን ጥምር ነው። ሚክያስ የክርስቶስን ሞት በማስመልከት የጠቆመው ደህንነት በአዲስ ኪዳን ዘመን በይበልጥ ተሟልቷል።

በዚህ ዓለም ሊኖረን ስለሚገባው ባሕርይ ትኩረት መስጠት ያስፈልገናል። የተለወጠ ባሕርይ የልብ ተሃድሶ ማረጋገጫ ነው። ሆኖም የወደፊቱን ሁኔታ ችላ ማለት አይገባንም። ሚክያስ እግዚአብሔር ገና ወደፊት ምን እንደሚያደርግ ተናግሯል። እግዚአብሔር ገና ወደፊት የሚሠራውን ለመገመት እንድንችል ብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የወደፊቱን ሁኔታ እንድንመለከት ያደርጉናል። ስብከታችን፥ ትምህርታችንና አኗኗራችን ወደፊት ገና ከሚሆኑት ነገሮች አንጻር የተመጣጠነ መሆን ይኖርበታል።

ጴጥሮስ ፍርድ የሚጀምረው ከእግዚአብሔር ቤተሰብ እንደሆነ ይነግረናል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንኳ ኃጢአት ሲሠራ ጌታ ይፈርድበታል። ፍርድና ፈተና አንድ አይደሉም። ፈተና የሚመጣው በኃጢአት ምክንያት አይደለም። ፍርድ ግን በኃጢአት ምክንያት ነው። ጳውሎስ በኃጢአት ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ሰብኳል። እኛም እንደዚሁ መስበክ ይኖርብናል። አስቀድመን ካላስጠነቀቅናቸው ሰዎችን ወደ ንስሐ መጥራት አንችልም። ኃጢአተኞች የእግዚአብሔርን ፍርድ መፍራት ይገባቸዋል፥ ዕብ.12፡29።

እግዚአብሔር ነቢያቱንና ሐዋርያቱን እንዲነግሩን ስለላካቸው የኃጢአት ትርጉም ምን እንደሆነ እናውቃለን። ሚክያስ ሕዝቡን ፍርድ ስለሚያስከትሉባቸው ነገሮች አስጠንቅቋቸዋል። እንዲሁም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ብዙ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያዎች ሰጥተዋል። ኃጢአት ባለበት ቦታ የእግዚአብሔር በረከት አይገኝም። ኃጢአት የነካው ነገር ሁሉ ንፁህ አይደለም። እግዚአብሔር ደግሞ ንፁህ ያልሆነ ማንኛውንም መሥዋዕት አይቀበልም። እግዚአብሔር እንደሚጠላው ከነገረን ነገር ሁሉ መራቅ ይገባናል።

እግዚአብሔር ቀድሞ የሠራውን ነገር ስንገነዘብ ወደፊት እሠራለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር በእምነት እንድንቀበለው ይረዳናል፤ ሆኖም መቼ እንደሚሠራው አናውቅም። እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ ሳይናወጡ መቆየት ማለት ተስፋ ማለት ነው። መጠራጠር ግን ተስፋ ማድረግ አይደለም። ተስፋ ማድረግ ማለት ወቅቱ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ያደርጋል ብሎ እርግጠኛ መሆን ነው። እግዚአብሔርን ቀድሞ መሄድ ትዕቢት ሲሆን ወደኋላ መቅረት ደግሞ አለመታዘዝ ነው። ሚክያስና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክርስቲያኖች ስላሉት ተስፋ ብዙ ይናገራሉ።

እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን አማካይነት ያቀረበው መገለጥ ታሪክን የተመረኮዘ ነው፥ ሉቃስ 3፡1-3 ተመልከቱ። የአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ ትምህርቶች ጠቃሚ ናቸው። ነገር ግን

ታሪካዊ አመጣጠቸውን መግር ይናርብናል። የጳውሎስ መልዕክቶች እግዚአብሔር በእርሱ፥ በእስያና በገሪክ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አማካይነት የሠራቸው ሥራዎች ውጤት ናቸው። እግዚአብሔር አሁንም በዚህ ዓለም ውስጥ የሚደረጉትን ሥራዎች እየተቆጣጠረ ነው።

# ሚክያስ

## ጥያቄዎች

1. ሶስት አጫጭር መጻሕፍት የጻፉት የይሁዳ ነቢያት ማን ማን ናቸው?
2. ለይሁዳ የተጻፉት ሁለት ትላልቅ መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው?
3. የይሁዳ መንግሥት ዘመን ከስንት እስከ ስንት ነበር?
4. በ931 ዓ.ዓ. ምን ተፈጸመ?
5. በ931-740 ዓ.ዓ. መካከል ስለ ይሁዳ መዘንጋት የሌለበትን አንድ ቁም ነገር ጥቀሱ።
6. ከሚክያስ ጋር በአንድ ዘመን የኖረው ነቢይ ማን ነበር?
7. ኢሳይያስ የሞተው መቼ ነበር?
8. ሰፎንያስ ትንቢት የተናገረው መቼ ነበር?
9. ከ700-620 ዓ.ዓ. ስላሉት ዘመናት የምናውቀው ነገር ምንድነው?
10. ዕንባቆም ትንቢት የተናገው መቼ ነበር?
11. በ609 ዓ.ዓ. ምን ተፈጸመ?
12. በ609 ዓ.ዓ. ጨርሶ የተሸነፈው የትኛው መንግሥት ነው?
13. በገምት ከ606-536 ዓ.ዓ. ታላቅ የነበረው መንግሥት የትኛው ነው?
14. አዝያን የሞተው መቼ ነው?
15. በአሜርያስና በሕዝቅያስ መካከል የነገሡት ሁለት ነገሥታት ማንና ማን ናቸው?
16. የኢዮአታምን ታሪክ የምናገኘው የት ነው?
17. አካዝ የኅብረት ስምምነት ያደረገው ከየትኛው መንግሥት ጋር ነው?
18. የሕዝቅያስን ታሪክ የሚያወሩት የሁለተኛ ዜና ምዕራፎች የትኞቹ ናቸው?
19. ሚክያስ በተነበየበት ዘመን የይሁዳ ነገሥታት ማን ማን ነበሩ?
20. አሞፅና ሚክያስ የሚመሳሰሉት በምን መንገድ ነው?
21. ሚክያስ 4፡1-4ና 5፡2-4 የሚያወሩት ስለምንድነው?
22. የፍርድ ትንቢቶች በሙሉ የተነገሩበት መሠረታዊ መንሥኤ ምንድነው?
23. ሚክያስ ኢየሩሳሌምን የሚያጣምራት ከማን ጋር ነው?
24. በሚክያስ ዘመን የነበረው የኢኮኖሚ ሁኔታ እንዴት ነው?
25. የትኞቹ የኢሳይያስ ምዕራፎችና ቁጥሮች ናቸው ከሚክያስ 4፡1-5 ጋር የሚመሳ ሰሉት?
26. ሚክ.4፡6-13 እንደተፈጸመ የትኞቹ የዕዝራ ምዕራፎች ናቸው የሚያሳዩት?
27. ከየትኞቹ 2 ድርጊቶች ጋር ነው ሚክያስ 5፡5-15 የሚገናዘበው?
28. ሚክያስ 6፡6-8 የተጻፈው ለየትኛው ሕዝብ ነው?
29. ሚክያስ 7፡14-20 ምን ዓይነት ምንባብ ነው?
30. የኢየሩሳሌምን መጥፋት ያቀደው ማን ነው?

31. ይህ ታሪክ ለክርስቲያን ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
32. በእግዚአብሔር ቃል ላይ እምነት እንዲኖረን የሚያደርገው ምንድነው?

# ትምህርት ስድስት

## ሶፎንያስና ዕንባቆም

### ታሪካዊ መግቢያ

እነዚህ 2 ነቢያት የተናገሩት ኢየሩሳሌም ከወደቀችበት ዘመን ከ586 ዓ.ዓ. በፊት ነው።




እነዚህ ሁለት መጻሕፍት እያንዳንዳቸው ሶስት ምዕራፎች አሏቸው። የዕንባቆም መጽሐፍ መቼ እንደተጻፈ አይታወቅም። ከነቢዩ ጥያቄ እንደምንረዳው የጻፈው ስለ ባቢሎን እንደነበር አንጠራጠርም። ባቢሎናውያን ሥልጣን የጨበጡት ነነዌን ከብበው አሶርን ባሸነፉበት ወቅት በ612 ዓ.ዓ. እንደሆነ እናውቃለን።

የፋርስ ንጉሥ ቂርስ በ538 ዓ.ዓ. ገደማ ባቢሎንን እንደያዛት እናውቃለን። ስለዚህ የባቢሎን መንግሥት በሥልጣን ላይ የቆየው ለ70 ዓመታት ያህል ነበር።

የዕንባቆም ጥያቄ በ586 ዓ.ዓ. ከተፈፀመው የኢየሩሳሌም ውድቀት ጋር ስለሚገጥም መጽሐፉን በዚያ ዘመን አካባቢ እንደጻፈው በማያሻማ መንገድ እርግጠኞች ነን። የጠየቃቸው ጥያቄዎችና ያገኛቸው መልሶች ልክ እንደዚያው ዘመን ዛሬም ጠቃሚና እውነት ስለሆኑ የተጻፉበት ትክክለኛ ጊዜ ቢታወቅም ባይታወቅም የትንቢቱን ትርጉም ምንም አይለውጠውም።

በ609 ዓ.ዓ. ኢዮስያስ በግብፅ ንጉሥ ኒካኡ በመጊዶ ተገደለ። ኢዮስያስ የነገሠው በ640 ዓ.ዓ. ጠማማው አባቱ አሞፅ ከሞተ በኋላ ነበር። ከይሁዳ ጠማማ ነገሥታት አንዱ አያቱ ምናሴ ነበር።

አሶራውያን በ702 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን ከወጉዋት በኋላ ኢሳይያስ ምን እንደሆነ አናውቅም። የአይሁዳውያን ታሪክ ምናሴ ገድሎታል ይላል። ሆኖም ይህንን ዘገባ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኘውም። ከኢሳይያስ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሶፎንያስ ዘመን ምንም ነቢይ በይሁዳ አለመኖሩን እናውቃለን።

| | | |
|---|---|---|
| 2ኛ ዜና 33፡1-20 | 2ኛ ነገ.21፡1-18 | የምናሴ ታሪክ |
| 2ኛ ዜና 33፡21-25 | 2ኛ ነገ.21፡19-26 | የአሞፅ ታሪክ |
| 2ኛ ዜና 34-35 | 2ኛ ነገ.22-23 | የኢዮስያስ ታሪክ |

የሶፎንያስ ስም በ2 ነገሥትም ሆነ በ2 ዜና ውስጥ አይገኝም። ኢዮስያስ ካነሣሣው ሃይማኖታዊ ተሃድሶ በኋላ ወይም በፊት ታይቶ ይሆን? ለዚህ ጥያቄ የተሟላ መልስ ለመስጠት አንችልም።

## የኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ሠንጠረዥ



# ሶፎንያስና ዕንባቆም

## የነቢያቱ ሸክም

ሁለቱም ነቢያት የእግዚአብሔር ቅድስናና የኃጢአት ውጤት ተሰምቶአቸዋል። ይህም ለእስራኤል የተሰጣትን መለኮታዊ መገለጥ ከከነዓናውያን ኃይማኖት የተለየ አድርጎት ነበር። ከነዓናውያን ኃጢአት የሚባል ነገር ምን እንደሆነ አያውቁም ነበር። ጣኦቶቻቸውም ከሰዎች ይልቅ የባሰ ኃጢአተኞች ነበሩ።
ዕንባቆም ሁለት ነገሮችን በሚገባ ተረድቷል፦

1. እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ምንም ስሕተት ለማድረግ አለመቻሉንና
2. እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን እንዳደረገ እንዲሁም እነርሱም የእርሱ የተለዩ ሕዝቦች መሆናቸውን ነው።

አሁን ግን የነቢዩ አቢይ ጥያቄ፦ እግዚአብሔር እንዴት ሕዝቡን ይቃወማል? ክፉዎቹን ባቢሎናውያንን እንዴት ሊጠቀምባቸው ይመርጣል? የሚል ነበር። ዕንባቆም የእግዚአብሔር ባሕርይና ቃል ኪዳኑ አሁን በይሁዳ ላይ ከሚሠራው ሥራ ጋር የሚስማማ ሆኖ አላገኘውም።

የእርሱ ጥያቄ ይህ ብቻ አይደለም! ዋናው ግን ይህ ነበር። እግዚአብሔር ክፉ ሕዝብ መርጦ እንዴት መጠቀሚያው ያደርጋል? ይህ ጥያቄ ዛሬም በዚህ ዘመን ለምንገኘው ተገቢ ጥያቄ ነው። ክፉዎች በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ያላቸው ስፍራ ምንድነው? እግዚአብሔር እንደ ባቢሎን ያሉትን ክፉ ሕዝቦች በሚጠቀምበት ጊዜ ጠባያቸውን ደገፈ ማለት ነው? እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ካደረገላቸው ሕዝብ ይልቅ ያንን ሕዝብ አብልጦ ወዶታል ማለት ነው? እግዚአብሔር ባቢሎናውያንን ይቀጣቸዋል ወይስ በአጠቃላይ ከቅጣት ያመልጣሉ?

የሶፎንያስ መልእክት ከዕንባቆም ፍፁም የተለየ ነው። ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች የጌታ ትዕግሥት ወደ ማከተሚያው እንደተቃረበ ሊጠቁማቸው ይሞክራል። «የጌታ ቀን» የሚለው ሐረግ ከማንኛውም የብሉይ ኪዳን ክፍል ይልቅ በሶፎንያስ ውስጥ ተደጋግሞ ይታያል። ለነቢይ ሶፎንያስ ይህም ቀን እግዚአብሔር በኃጢአተኛይቱ ከተማ በኢየሩሳሌም ላይ ፍርድ የሚፈርድበት ቀን ነው።

ሶፎንያስ የተነበየው ምናልባት ኢዮስያስ በ621-22 ካከናወነው ተሃድሶ በኋላ ይሆናል። 2ኛ ነገ. 21-22 እንደሚያመለክተን ኢዮስያስ ብዙ ተግባሮችን ፈጽሟል። ሕዝቡ ከጣኦታት አምልኮ ተመልሶ እንደገና የበዓል ቀናትን ማክበርና በቤተ መቅደስ ውስጥ ማምለክ ጀምሮ ነበር።

ሆኖም የሚያደርጉት ከልባቸው አልነበረም። ንሥሐ የገቡት ለይስሙላ ነበረ። ይህንን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? ጠባያቸው ፈጽሞ አልተለወጠም። ቀድሞ ይሠሩት እንደነበረው አሁንም ተመሳሳይ ኃጢአት መሥራት ተያይዘውት ነበር። በአፋቸው ብቻ እግዚአብሔርን ያመልኩታል! ልባቸው ግን ከእርሱ በጣም የራቀ ነበር።

በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ማለት ከ640-609 ዓ.ዓ. ኤርምያስ ደግሞ በኢየሩሳሌም ይሰብክ ነበር። መልዕክቱም የኢየሩሳሌም ሰዎች ሊያመልጡት የማይችሉትን ፍርድ እንዲቀበሉ ማሳሰብ ነበር። ሶፎንያስ ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ ሕዝቦች ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። በዚያ እንዳልተጠቀሙበት እናውቃለን። ስለዚህ ሶፎንያስ የተነበየው ተንቢት ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን ሲደመስስ በ586 ዓ.ዓ. ተፈጸመ።

# ሶፎንያስ

## ማብራሪያ

ሶፎንያስ ነቢይና የንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመድ ነበረ። ትንቢት ይናገር የነበረው በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ማለት ከ640-609 ዓ.ዓ. ነበረ፣ 1፡1።

ሕዝቡ እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢአት አይጨነቅም የሚል የማይረባ ንግግር ተለማምደዋል፣ 1፡12። እግዚአብሔር እንደሚፈርድባቸው ብቻ ሳይሆን የፍርዱም ጊዜ በጣም ቅርብ መሆኑን ነቢዩ ያሳስባቸዋል፣ 1፡7ና 14። የዚህ አስፈሪ ፍርድ ምክንያት አሁንም በኢየሩሳሌም ከተማ የሚገኘው ኃጢአት ነው፣ 1፡4-9። ሕዝቡ ይሠሯቸው የነበሩትን ኃጢአቶች ዓይነት በዝርዝር ጻፏቸው። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ ተደርገው የተቆጠሩ መሆናቸውን አትርሱ።

የቃል ኪዳኑ ሰዎች በመሆናቸው ሶፎንያስ አስፈሪውን የእግዚአብሔርን የፍርድ ቀን ያመለክታቸዋል፣ 1፡10-18 አንብቡ። ሕዝቡ ጊዜው ሳያልፍ ንሥሐ እንዲገባ ሊያሳስብ ይሞክራል።

ሕዝቡ ንሥሐ እንዲገባ ለመጠየቅ በምዕራፍ 2 ሶስት ጥቅሶችን ይጠቅማል፣ 2፡1-3 አንብቡ። ኢዮስያስ ይህንን ድርጊት አስቀድሞ አድርጎት ስለነበር ብዙ ተስፋ የሚጣልበት አይደለም! ስለዚህ ልመናው አጭር ነው።

ይህ ጣኦትን የሚያመልክ ሕዝብ ምንም አይደርስበትም? ከፍልስጥኤማውያን ከተማ ይጀምራል፣ 2፡4-7። ከዚያም ከጨው ባሕር በስተምሥራቅ ያሉትን ሕዝቦች መናገር ይቀጥላል፣ 2፡8-11። ኢዮስያስ ከሞተ ከ3 ዓመታት በፊት ነነዌ እንደተደመሰሰች እናውቃለን። በምዕ.2፡4-15 ውስጥ የሚገኙት ትንቢቶች በሙሉ ተፈጽመዋል። እነዚህ መንግሥታት በሙሉ ተደምስሰዋል። ሶፎንያስ የሚለው ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ጣኦትን የሚያመልኩት እነዚህ ሕዝቦች የተቀበሉትን ዓይነት ፍርድ ይቀበላሉ ነው።

ኢየሩሳሌም የተለየች ናት፣ 3፡1-13 አንብቡ። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይቀጣታል። ይሁን እንጂ ከተማይቱን እንደገና ያድሳታል። ሕዝቡም በተቀጣበት ወቅት ጣኦታትን ለዘላለም መተው እንዳለበት ይማራል። በኢየሩሳሌም ላይ የደረሰው ቅጣት ኃጢአትን ከመከከላቸው አስወገደ-ል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አይሁድ የጣኦታትን አምልኮ ተቀብለው አያውቁም።

ሶፎንያስ ትንቢቱን የሚደመድመው በደስታ መዝሙር ነው፥ 3፡14-20። ከባቢሎን ምርኮ መመለሳቸውን ሶፎንያስ አይጠቁምም፥ ኢሳ. 40-66። በአጠቃላይም ምርኮውን ፈጽሞ አይጠቅሰውም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን ቢቀጣቸውም መልሶ እንደሚጠግናቸው ያውቅ ነበር።

# ዕንባቆም

## ማብራሪያ

ዕንባቆም ትንቢት መናገር የጀመረው መቼ እንደነበረ አናውቅም። ሆኖም የተናገረው ነገር በሚገባ ግልፅ ነው።

ትንቢቱ ስለ እግዚአብሔር በትክክል አለመፍረድ በማጉረምረም ይጀምራል። እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ኃጢአተኞች በመቅጣት ፈንታ ለምን ይረዳቸዋል? 1፡2-4 አንብቡ። በሶፎ.1፡4-9 ላይ ጥቂቶቹ ኃጢአቶቻቸው ተዘርዝረዋል። እግዚአብሔር ምንም ሲያደርግ አንመለከትም።

በ1፡5-11 ላይ መልሱ ተሰጥቷል። እግዚአብሔር ከሩዎቹን ባቢሎናውያን ሊያመጣባቸው ነው፥ በኤር. 25፡9 ላይ ባቢሎን የእግዚአብሔር አገልጋይ ተብላ ተጠርታለች። 2ኛ ነገ. 24-25 እንደሚያስረዳን ጌታ ባቢሎንን ሶስት ጊዜ ጠርቷት ነበር። በመጀመሪያ በ606 ዓ.ዓ.፥ ከዚያ በ597ና በ586 ዓ.ዓ. ነበር። ዕንባቆም ምናልባት የመጀመሪያዎቹን 2 ወረራዎች ሳይመለከት አልቀረም።

ዕንባቆም እንደገና ያጉረመርማል፥ 1፡12-17። እንዴት ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ኃጢአተኛ የሆነን ሕዝብ መጠቀሚያው ያደርጋል? በሐጌ 2፡10-14 ላይ ያለውን ምሳሌ ተመልከቱ። እግዚአብሔር ኃጢአተኛን ሕዝብ በሚጠቀምበት ጊዜ እርሱ ራሱ ረከሷል? መልሱ አልረከሰም ነው። ይህ ጥያቄ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሌላ መልስ ይዞ ይመለሳል፥ 2፡1-4 አንብቡ። እግዚአብሔር ባቢሎንን አንድ ቀን ይደመስሳታል። በ538 ዓ.ዓ. የሜዶንና ፋርስ ንጉሥ ቂርስ ባቢሎን በወጋበትና በደመሰሰበት ወቅት እግዚአብሔር የተናገረው እንደተፈጸመ ተገንዝበናል። በምዕ.2፡1-4 የተጻፈው ትንቢት በዚያን ጊዜ ፍጻሜ አግኝቷል።

2፡5-20 የሚያመለክተው ማንን ነው? ጥቅሶቹን አንብቡ። አንዳንድ ምሁራን ዕንባቆም የሚናገረው ስለ ባቢሎን ነው በማለት ያስባሉ። እኛ ክፍሉ የሚናገረው ስለ ኢየሩሳሌም ይመስለናል። ይኸውም በኢየሩሳሌም የሚገኙት ሰዎች ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያሳየናል። አምስት ጊዜ ተፈርዶባችኋል ብሎ ለእነዚህ ሰዎች ይነግራቸዋል። በጣም ኃጢአተኛ ከመሆናቸው የተነሣ እግዚአብሔር እነርሱን ከማጥፋት በስተቀር ለማዳን ምንም አማራጭ መንገድ የለውም።

የዕንባቆም ጸሎት በአራት ክፍሎች ይከፈላል። ምዕራፍ 3፡1፥ 3-6፥ 7-15ና 16-19 አንብቡ። በቁ. 3-6 ላይ ነቢዩ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ ስላለው ኃይል ይናገራል። በቁ.7-15 ላይ የሚያመለክተው በታሪክ ውስጥ ያለውን ኃይል ነው። ይህም የብሉይ ኪዳን

ታሪክ ግምገማ ነው። ሆኖም እንደ ዕንባቆም ያሉት ታማኝ ሰዎች ምንም አይፈሩም፥ ቁ.16-19።

# ሶፎንያስ

## የተለዩ ነጥቦች

በአል የከነዓናውያን የልምላሜ አምላክ ነው። እነርሱም ዝናብንና ፀሐይን የሚሰጣቸው እርሱ እንደሆነ ስለሚያምኑ መሥዋዕት ይሰዉለት ነበር። አንዳንድ አይሁዳውያን ባቢሎናውያን እንደሚያደርጉት በፀሐይ፥ በጨረቃና በከዋክብት ያምኑ ነበር። ሚልኮም የሞአባውያን አምላክ ነበር፥ 1፡4-9 አንብቡ። ይህ ሃይማኖታዊ ኃጢአት ሕዝቡን ወደ ሕገ ወጥ ኑሮ እንዲያመራ አድርጎት ነበር።

በእንደዚህ ያለ ወቅት ታማኞቹ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ምን ነበር? 2፡1-3 አንብቡ። እግዚአብሔር ፍርድን በሚያመጣበት ጊዜ እንኳ እነዚህን ታማኞች ሊያድናቸው ይችላል። ሶፎንያስ ሕዝቡን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት አዋርደው ትሑታን እንዲሆኑና ከ586 ዓ.ዓ. ከሚደርስባቸው ፍርድ እንዲያመልጡ ያሳስባቸዋል። እግዚአብሔር ኤርምያስን የመሳሰሉትን ሰዎች እንደዚህ አድርጎ አድኗቸው ነበር።

የኢየሩሳሌም ሰዎች እግዚአብሔርን በዓይናቸው አላዩትም፤ በሚያደርጋቸው ሥራዎች ግን ማንነቱን ገልጾላቸዋል፥ 3፡6-7 አንብቡ። እግዚአብሔር ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች በሙሉ ቢያሳያቸውም ወደ እርሱ መመለስ እምቢ ብለዋል። ምን እንደሚደርስባቸው እግዚአብሔር በሚታይ መንገድ አስታውቋቸዋል ግን ለመማር እምቢ ብለዋል። ስሙ በሶፎንያስ 1፡1 ላይ የተጠቀሰው ንጉሥ ኢዮስያስ ሕዝቡን በብዙ መንገድ ሊረዳቸው ሞክሯል። ኢዮስያስ ከመሞቱ ከ609 ዓ.ዓ. በፊት እንኳ እንደገና ወደ ጣኦት አምልኮ ሳይመለሱ አልቀሩም።

# ዕንባቆም

## የተለዩ ነጥቦች

ዕንባቆምና ሌሎቹም ነቢያት ኃጢአት ምን ጊዜም ፍርድን እንደሚያስከትል ተረድተዋል። እግዚአብሔር በ722 ዓ.ዓ. ሰማሪያን አውድሟታል። ጌታ ይህንን ያደረገው ከዕንባቆም ዘመን 140 ዓመታት ያህል በፊት ነበር። ኢየሩሳሌም ልክ እንደሰማሪያ ኃጢአተኛ ነበረች ታዲያ እግዚአብሔር ለምን ታገሳት? እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ኃጢአት ያልቀጣው ለምንድነው? 1፡2-4 በድጋሚ አንብቡ። ዕንባቆም እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑንና ለእስራኤል የሰጣቸው ሕግጋት ሳይጠበቁ እንደቀሩ ያውቃል። እግዚአብሔር ምንም ነገር የማያደርገው ለምንድነው?

እግዚአብሔር ዝም አላለም ነበር። ዕንባቆም ለጠየቃቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል፥ 1፡5-11፤ 2፡1-4 አንብቡ። እግዚአብሔር <u>ማን</u> መሆኑን ተናገሯል ስለዚህ እግዚአብሔር

ጌጊ እንደሆነ የምናውቅበት መንገድ ይህ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ስለ ገለፀልን እርሱ ምን እንደሚያደርግ፥ ምን እንደሚፈልግና ለምን እንደዚህ እንዳደረገ ተረድተናል። ዕንባቆም ምናልባት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ አልተገነዘበም ይሆናል። ሆኖም ሕዝቡን እንዳልረሳው አውቋል።

ዕንባቆም የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ኃጢአት ተመልክቷል፥ 1:2-5፤ 2:5-20። እግዚአብሔር ፍርዱን በማዘግየቱ ተገርሟል እንጂ እንዲያዝን ወይም አዕምሮውን እንዲስት አላደረገውም። ከእግዚአብሔር መልስ ካገኘ በኋላ ምንም መጥፎ ዜና ቢሆንም እግዚአብሔርን ስለኃይሉ ማመስገን ይችል ነበር። ዕንባቆም እግዚአብሔር ለዚያ ኃጢአተኛ ሕዝብ ምሕረት እንዲያደርግ ይለምናል፥ 3:2። በእግዚአብሔር ቸርነትና ልግስና ላይ የነበረው እምነት አይናወጥም፥ 3:16-19።

# ሶፎንያስ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

አዲስ ኪዳንና ብሉይ ኪዳን ሁለቱም አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ ያሳስቡናል። ሆኖም ብዙ አማልክት አሉ። 2 ቆሮ. 6:14-18 ስለ ሌሎች አማልክት ያወራል። የእግዚአብሔርን ማንነት በሚያስተምረን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናገኘው ትምህርት ላይ ምንም ነገር ልንጨምርበት አንችልም። በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ያደረጉት ይህን ነበረ፥ ሶፎ.1:4-9። እኛ ደግሞ ዛሬ ከጣኦት አምልኮ መሸሽ ይኖርብናል፥ 1ኛ ዮሐ.5:21።

መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን እንዲመራ ልንፈቅድለት ያስፈልጋል። በልባችን ውስጥ ያልተናዘዝነው ኃጢአት ሊኖር አይገባም። ይሁንና በእግዚአብሔር ፊት ያለማቋረጥ ራሳችንን ማዋረድ ይገባናል። ምናልባት አንዳንድ ነገሮችን ሸሽገን ሳለ ስለ ሁሉም ነገር ይቅር እንደተባልን አድርገን እንድናስብ ሰይጣን ሊያታልለን ይችላል።

የእግዚአብሔርን ቃል በምናነብበትና በምናጠናበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ዓይናችንን ከፍቶ ማስተዋልን እንዲሰጠን መጸለይ ያስፈልገናል። እኛም የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች ልንመስል እንችላለን፥ ሶፎ.3:6-7። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ማዳመጥ እንችላለን። በተለያዩ ሥፍራዎች የሚያደርሰውን ፍርድ መመልከት እንችላለን። ነገር ግን ከቀሰምነው ትምህርት ምንም ሳንገነዘብ እንቀር ይሆናል። ጳውሎስ በኤፌ.1:18 ላይ በኤፌሶን ላሉት ክርስቲያኖች አዕምሮአቸው እንዲከፈት ጸልዩላቸዋል። እኛም ተመሳሳይ ጸሎት እንጸልይ።

# ዕንባቆም

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር መረዳት ከተሳነን ዕንባቆም እንደሠራውና እንደጠየቀው እናድርግ! አንዳንዴ ስንጨነቅ እግዚአብሔር እንደረሳንና እንደተለወጠ አድርጎ ማሰብ ቀላል ነገር ነው። ኢየሱስ እንዳለው ከኃጢአት የተነሣ የሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።

ዕንባቆም በኢየሩሳሌም የነበረውን ኃጢአት ልብ አድርጓል፤ የባቢሎናውያንን ኃጢአት ተመልክቷል። ነገር ግን የነበረውን ጥያቄ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት አቅርቧል።

መልሶች የምናገኘው ከየት ነው? እርሱን በምንፈልግበትና ሊሰጠን በሚሻበት ጊዜ ስናዳምጠው እግዚአብሔር ማናቸውንም መልሶች ይሰጠናል። ዕንባቆም መልሶቹን ያገኘው በዚህ ሁኔታ ነው። የማንኛውንም ጥያቄ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት እንችላለን። መልሶቻችንን ሁሉ ከዚያ እንፈልጋቸው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ትክክለኛው ስፍራ መርቶን ማስተዋል እንዲሰጠን እንጸልይ።

ዕንባቆም ጥያቄዎች ነበሩት፤ ነገር ግን እንዲያመሰግን አድርገውታል። እግዚአብሔርን ያመሰገነበት ምክንያት በጥሞና አስተውሉ። ዕንባቆም የኖረበት ዘመን በማንኛውም አቅጣጫ አስቸጋሪ ዘመን ነበር። በኢየሩሳሌም የነበሩት አይሁዶች ከሐዲዎች ነበሩ። ጨካኞቹ ባቢሎናውያን ቤተ መቅደሱን ሊያቃጥሉና ምድሪቱን ሊያጠፉት የተቃረበበት ዘመን ነበር። ዕንባቆም በእነዚህ ነገሮች ሁሉ በፍፁም አልተሸነፈም። እግዚአብሔር የፈለገውን ነገር ቢያደርግም እንኳ የዕንባቆም እምነት የጸና ነበር፥ 2፡4 ተመልከቱ።

## ሶፎንያስና ዕንባቆም

### ጥያቄዎች

1. በኢዮስያስ ዘመን የተናገረው ነቢይ ማን ነበር?
2. ባቢሎን ሥልጣን የጨበጠችው መቼ ነበር?
3. ባቢሎን በሥልጣን ላይ የቆየችው ለምን ያህል ዓመታት ነበር?
4. ዕንባቆም ትንቢቱን የጻፈው መቼ ነበር?
5. ከኢዮስያስ በፊት የነገሡት ሁለት ጠማማ ነገሥታት ማንና ማን ነበሩ?
6. ኢዮስያስ የሞተው የትና መቼ ነበር?
7. በ701-640 ዓ.ዓ. መካከል ምን የታወቀ ነገር ተፈጽሟል?
8. ኢዮስያስ የነገሠው ከስንት እስከ ስንት ዓ.ዓ. ነበር?
9. ኢዮስያስ ያደረገው ተሃድሶ የሚገኘው የት ነው?
10. ይህ ተሃድሶ የተደረገው መቼ ነበር?
11. የዕንባቆም ጥያቄ ምን ነበር?
12. የሶፎንያስ ሸክም ምን ነበር?
13. ሶፎንያስ ትንቢት ይናገር የነበረው ከጥገናዊው ለውጥ በኋላ ወይስ በፊት ነበር?
14. የሶፎንያስ ትንቢት የተፈጸመው መቼ ነበር?
15. ሶፎንያስ በተለይ ይናገር የነበረው ለየትኛይቱ ከተማ ነበር?
16. ሶፎንያስ 3፡14-20 ምንድነው?
17. የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቅጣቶች በኢየሩሳሌም ላይ የደረሱት መቼ ነበር?
18. ዕንባቆም 2፡1-4 የተፈጸመው መቼ ነበር?
19. ዕንባቆም ምዕ. 3 የሚናገረው ስለ ምንድነው?
20. የከነዓናውያን የልምላሜ አምላክ ማን ነበር?
21. በዚህ ዘመን የተናገረው ሌላ ነቢይ ማን ነበር?

22. በኢየሩሳሌምና በሰማሪያ መደምሰስ መካከል የነበሩት ዓመታት ስንት ናቸው?
23. እግዚአብሔር ማንነቱን እንዴት ገለጸ?
24. ሶፎንያስ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ለምንድነው?
25. የዕንባቆምና የሶፎንያስ መጻሕፍት የተመሳሰሉበት አንድ መንገድ ግለፅ።

# ክፍል ሦስት

## ኢየሩሳሌም

### ጠቅላላ መግቢያ

በክፍል ሶስት ከምርኮ በኋላ የተናገሩ የሶስት ነቢያት መጻሕፍት እናጠናለን። ኤርምያስና ሕዝቅኤል እንደተነበዩት ናቡከደነጾር መጥቶ ኢየሩሳሌምን እንደደመሰሳት እናውቃለን፤ 2ኛ ነገ. 25፤ 2ኛ ዜና 26፤ ኤር. 52 አንብቡ። ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን እንዲያጠፉት እግዚአብሔር ተጠቀመበት ማለት የተሻለ ነው። ኢየሩሳሌምን ያጠፉት እግዚአብሔር እንጂ ባቢሎናውያን አልነበሩም። ለምን? ሕዝቡ ንስሐ መግባትና ጣኦቶቻቸውን ለማስወገድ እምቢ ስላሉ ነው።

ኤርምያስ ስለዚህ ቀውጢ ሰዓት የልቅሶ ሙሾዎችን ያዘሉ አምስት ምዕራፎች ጽፏል፤ ሰቆቃው ኤርምያስን አንብቡ። እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ስለ 70ዎቹ የምርኮ ዓመታት ተናግሯል፤ ኤር.25፡11፤ 29፡10።



እስከ መጀመሪያው መመለስ ማለት እስከ 536 ዓ.ዓ. ድረስ በ586 ዓ.ዓ. ከኢየሩሳሌም ከወጡት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ በባቢሎን ሞተዋል። በባቢሎን ስላሳለፉት ጊዜ ብዙ የምናውቀው ነገር የለም፤ ለምሳሌ መዝ.135 አንብቡ። በባቢሎን ሕዝቅኤልና ዳንኤል 2 ነቢያት ነበሩ።

ዳንኤል ስለ አንዳንዶቹ ታማኝ ሰዎች ባሕርይና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን የወደፊት ዕቅድ ይነግረናል። ሕዝቅኤል በባቢሎን ይኖሩ የነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ተስፋ እንዳይረሱ እምነታቸውን ያጠናክር ነበር።

በ538 ዓ.ዓ. ገደማ ቂሮስ የሚባል ንጉሥ በአሻን ተነሥቶ ፋርስን ካሸነፈ በኋላ አዲስ መንግሥት አቋቋሟል። ከዚያም ከጦር ሠራዊቱ ጋር ባቢሎንን ድል አድርጎ ከ538-333 ዓ.ዓ. በሥልጣን ላይ የቆየውን የፋርስን መንግሥት መሠርቷል። በጥቂቱም ቢሆን ስለዚህ መንግሥት የሚነገረን የአስቴር መጽሐፍ ብቻ ነው።

ሕዝቡ ከባቢሎን ወደ አገራቸው የተመለሱት በሶስት ቡድን ነበር። በ536 ዓ.ዓ. የመጀመሪያው ቡድን መሪ ዘሩባቤል ሲሆን በ457 ዓ.ዓ. ሁለተኛው መሪ ዕዝራና በ444 ዓ.ዓ. ሦስተኛው መሪ ነህምያ ነበሩ። የመጀመሪያው መመለስ ዝርዝር ሁኔታ በዕዝራ 1-6 ይገኛል፤ እነዚህን ምዕራፎች አንብቡአቸው።

ሦስት ነቢያት ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰውን ሕዝብ ተናግረዋል። ሐጌና ዘካሪያስ የተናገሩት በተመሳሳይ ዘመን ሲሆን በ520 ዓ.ዓ. አካባቢ ሕዝቡ ከምርኮ ከተመለሱ ከ16 ዓመታት በኋላ ነበር። ሚልክያስ የተናገረው ምናልባት ከጥቂት ዓመታት በኋላ ይሆናል። ትንቢተ ሚልክያስ ስለተጻፈበት ዘመን ምንም ፍንጭ ስለማይሰጠን ነቢዩ የተናገረው መቼ እንደሆነ እርግጠኞች ልንሆን አንችልም። በሚልክያስና በነህምያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ሁኔታዎች የሚናገሩት ተመሳሳይ ስለሆነ ምናልባት ሁለቱም በአንድ ዘመን የተነገሩ ሳይሆኑ አይቀሩም።

# ትምህርት ሰባት

## ዘካሪያስ 1-8

### ታሪካዊ መግቢያ

በዘካርያስ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ከይሁዳ ነገሥታት መካከል የማንኛውም ንጉሥ ስም እንዳልተጠቀሰ ትመለከታላችሁ፤ በእርግጥም ምንም ነገሥታት አልነበሩም። የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በ586 ዓ.ዓ. ወደ ባቢሎን ተወስዶ ነበር። ከዚያ ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ በኢየሩሳሌም ምንም ንጉሥ አልነገሠም።

ብዙ ሕዝብ በ536 ዓ.ዓ. ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል። ለአስራ ስድስት ዓመታት የቤተ መቅደስ ሥራ ብዙ አልሠሩም። ሌሎች ነገሮችን በመሥራት በጣም ተጠምደው ነበር።

በተጨማሪ በአካባቢው መንግሥታትና በውስጥ ባለሥልጣኖች በኩል ትልቅ ተቃውሞ ነበረባቸው። ዘካ.1-8 በምታነቡበት ወቅት በዕዝራ 1-6 ውስጥ ከሚገኙት ዝርዝሮች ጋር አዛምዱት።

እነዚህ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሱበት ወቅት አገሪቱ ነጻ እንዳልነበረች አስታውሱ። ይሁዳ የፋርስ መንግሥት ግዛት ስለነበረች በዚያ የነበሩት ባለሥልጣናት በሙሉ የዚህ መንግሥት ቅጥረኞች ነበሩ። ስለዚህ ታላቁ ሊቀ ካህን ኢያሱም ሆነ የሕዝቡ አስተዳዳሪ ዘሩባቤል ከፋርስ መንግሥት ደመወዝ ይቀበሉ ይሆናል።

ካምቢስስ የተባለው የፋርስ ንጉሥ ሲሞት አይሁድ ያለ ምንም ተቃውሞ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ የመገንባት ሥራቸውን ለማካሄድ ዕድል አግኝተዋል። ልክ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ሁለት ነቢያት ልኮላቸዋል። ሁለቱም በአንድ ዘመን ትንቢት ይናገሩ ነበር። ዘካርያስ የተናገረው በ520 ዓ.ዓ. አካባቢ ነበር። ከመጽሐፉ መከፈቻ ጥቅሶች በስተቀር ትንቢተ ዘካርያስ ሌላ ታሪካዊ መረጃዎችን አይሰጠንም።

ዘካርያስ 1-8 የተናገረው ለአንድ ለተለየ ሕዝብ ነው። ይኸውም ከባቢሎን ተመልሰው በኢየሩሳሌም ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ነበር። አንድ ነገር ማስታወስ ይገባናል! ይኸውም ከጥቂት በዕድሜ ሽምገል ካሉት በስተቀር አብዛኞቹ ሰዎች ቤተ መቅደሱ በናቡከደነጾር ከመፍረሱ በፊት አይተውት አያውቁም ነበር። በባቢሎን የተወለዱት ወጣት ዜጎች ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ቤተ መቅደሱ የሚያውቁት በታሪክ ብቻ ነበር።

ምንም ትክክለኛ መልስ ያላገኘንለት ጥያቄ ቢሆንም የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀን የተለያዩትን አማራጭ ሁኔታዎች ማሰላሰል ያስፈልገናል። እነዚህ ሰዎች በሕዝቅ. 40-48 ላይ በተጻፈው መመሪያ መሠረት ቤተ መቅደሱን እንደገና ለመገንባት ተስፋ በማድረግ ይጠባበቁ ነበር? ሐጌና ዘካሪያስ ይህንን ፈጽሞ አልጠቀሱትም። ስለዚህ ያንን ለመከተል አላሰቡም ይሆናል። ዳንኤልና ሕዝቅኤል በባቢሎን ተወልደው ላደጉ አይሁዶች አስተማሪዎች ነበሩ። ከዳን. 9፡1-3 እንደምንረዳው በ536 ዓ.ዓ. ዳንኤል በሕይወት ነበር።

ዘካርያስ በተናገረበት በ520 ዓ.ዓ. በኢየሩሳሌም የነበሩት ሁለቱ መሪዎች ኢያሱና ዘሩባቤል ነበሩ። ዘካርያስ ከተናገረው ብዙው ክፍል የሚመለከተው እነርሱን ነው። ሕዝቡ በእነርሱ ላይ እምነት ስላልነበረው ዘካርያስ እነዚህ መሪዎች የእግዚአብሔር ወኪሎች መሆናቸውን ያረጋገጥላቸው ነበር።

ዘካ.1-8ን ለማስተዋል እንድንችል ስለሚርዳን በሐጌ 1-2 ላይ የሚገኘውን ሐሳብ በተጨማሪ ማንበብ ይገባናል። በዚያ ዘመን በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች ሁኔታ ከሚያስረዱን ከሐጌ 1-25 ዕዝራ 1-6 በስተቀር ሌላ ምንም ማስረጃ አናገኝም።

# ዘካርያስ 1-8

## ነቢዩ ሸከም

የዘካርያስ 1-8 መልእክት <u>ማበረታቻ</u> በሚል ቃል ሊጠቃለል ይችላል። ዘካርያስ ይናገርበት የነበረው ዓላማ በ520 ዓ.ዓ. የነበሩትን መሪዎችና ሕዝብ ለማበረታታት ነበር። ምክሩንና ራዕዩን በምናነብበት ጊዜ ለማን እንደሚናገር ማስታወስ ይኖርብናል። በተጨማሪ ለምን በዚህ ዓይነት መንገድ ሊናገራቸው እንደተጠራ ማስታወስ ይኖርብናል። በዚህ ወቅት ከተዕዛዝና ከተግሳፅ ይልቅ ማፅናኛ ያስፈልጋቸው ነበር።

በመጀመሪያዎቹ ስምንት ምዕራፎች ውስጥ ዘካርያስ እግዚአብሔር የሰጠውን ስምንት ራዕዮች ያስተላልፋል። የስምንቱ ራዕዮች መሠረታዊ ትርጉም አንድ ነው። ይኸውም እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማበረታታትና እርሱ ከእነርሱ ጋር እንደነበረ ለማሳሰብ ነበር። ራዕዮቹ አንዳንድ ምዕላዊ አገላለፅ አሏቸው፤ ነገር ግን የሁላቸውም ትርጉም ግልፅ ነው። ስለዚህ ምንም ምስጢራዊ ትርጉም መስጠት አያስፈልገም።

ዘካርያስ ሁለቱን መሪዎች የማጽናናት ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። ከተናገረው ምን ያህሉ ክፍል ስለ እነርሱ እንደነበረና አንዳንዱም በቀጥታ ለእነርሱ ለራሳቸው እንደነበረ አጥብቃችሁ አስተውሉ። ሕዝቡ መሪዎቹን መምሰሉ ስለማይቀር እነዚህ ሁለት ሰዎች ዘሩባቤል እና ኢያሱ በዕምነታቸው መጽናታቸው በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። በባቢሎን ከምኩራብ በስተቀር ምንም ቤተ መቅደስ ስላልነበረ የሊቀ ካህናት ሥራ ለብዙዎቻቸው አዲስ ነገር ነበር።

ሕዝቡ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ወዲያው አጥፍቶላቸው እንደ ኢያሱና ዳዊት ዘመን እንደገና ድል የሚጎናፀፉ መስሏቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን እንደዚህ አላደረገም። ፋርስ ዕለት በዕለት እየበረታች ሄደች። አይሁዳውያን መንግሥታቸውን በይሁዳ እንዲያቋቁሙ አልተፈቀደላቸውም ነበር። ይህም ሁኔታ እግዚአብሔር ችላ ብሎ ትቶናል ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸው ነበር። አሁንም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደሆነ ዘካርያስ ያረጋግጥላቸዋል።

በባቢሎን ያደጉት እስራኤላውያን በሙሉ ምናልባት ንግድንና እርሻን የመሳሰሉት ጥሩ ጥሩሙያዎች ሳይኖሩአቸው አይቀሩም። ወደ ይሁዳ ሲመለሱ ለ70 ዓመታት ምንም ያልተሠራበት ሆና አገኙአት። ይበልጡ መሬት ወደ ጫካ ተለውጦ ነበር። በባቢሎን በነበሩበት ጊዜ መቅደስ ስላልነበራቸው ጥቅሙ ምን እንደሆነ አልተረዱም ነበር። ስለዚህ ወደ ይሁዳ በተመለሱበት ወቅት ብዙው ነገር የሚያስከፋ ሆኖ አገኙት።

ዘካርያስ ያፅናናቸዋል። በተጨማሪ አኗኗራቸውን ከእግዚአብሔር ጋር እስካላስተካከሉ ድረስ እርሱ ከእነርሱ ጋር እንደማይሆን ያሳስባቸዋል። እነዚህ ሰዎች ሕግጋቱና ቤተ መቅደሱ ኣላቸው፤ ካህናትና ነቢያት ነበሩአቸው፤ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች የተለወጠ ኑሮ ማስገኘት ነበረባቸው። የእርሱ ሕዝቦች ከሆኑ እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ይኖርባቸዋል። የተቀደሰው ሥርዓትና ሥነ ምግባር እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ካደረገው ቃል ኪዳን ጋር የተያያዘ ነው።

# ዘካርያስ 1-8

## ማብራሪያ

በምዕ. 1፡1-6 ላይ የሚገኙት የነቢዩ ቃላት ለመላው መጽሐፍ የተደረጉ መተዋወቂያ ናቸው። እነዚህ ቃላት በ520 ዓ.ዓ. በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ሰዎች የተነገሩ ነበሩ።

የመጀመሪያው ራዕይ ስለ ፈረሶች ነው፤ 1፡7-17። ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔር ዓለምን እንዲቆጣጠሩ መልእክተኞቹን እንደላከ ነው። ከዳርዮስ በፊት በነበረው በፋርስ ንጉሥ በካምቢቢስ ሞት ምክንያት የተፈጠረው ብጥብጥ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው።

የእስራኤል ጠላቶች በአራት ቀንዶች ተመስለዋል፤ 1፡18-21 አንብቡ። እግዚአብሔር ደግሞ እነርሱን ለማጥፋት መንገድ አዘጋጅቶ ነበር። ጠላቶቻቸው በሙሉ ድል ይደረጋሉ።

ኢየሩሳሌም ከመጠን በላይ ሰፊ ትሆናለች፤ 2፡1-5 ተመልከቱ። ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች እምነት የእግዚአብሔር ዕቅድ እጅግ የላቀ ነበር። ተበትነው የነበሩት ሰዎች አሁንም ወደ ኢየሩሳሌም እየተመለሱ ነው፤ 2፡6-13 አንብቡ።

ሆኖም ሕዝቡ በሊቀ ካህኑ በኢያሱ ተግባር አይደሰትም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ከምርኮው እድፍ ሁሉ እንዳነጻው ያሳያቸዋል፤ 3፡1-10። በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሁሉ በብቃት ሊያገለግላቸው ይችላል። ምንም ነገር መፍራት አይገባቸውም። ይህ ለዘካርያስ የተሰጠ 4ኛ ራዕይ ነበር።

ለእነዚህ ሁለት መሪዎች የተሰጠው ጥበብና ብርታት የተገኘው ከእግዚአብሔር ከራሱ ብቻ ነበር። መቅረዙ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሰዎች ምስክርነት ነው፤ 4፡1-14። ምዕ.3 በአጠቃላይ የሚያወራው ስለ ሊቀ ካህኑ ስለ ኢያሱ ነው። ይህ ምዕራፍ የሚያመለክተው በተለይ በወቅቱ የማሕበሩ መሪ የነበረውን ዘሩባቤልን ነው። እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው ተስፋ በ4፡6-10 ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔር የጀመረውን ይፈጽመዋል! ቃሉንም አያጥፍም።

በምዕ.5፡1-4 ላይ በሚገኘው 6ኛ ራዕይ ውስጥ ዘካርያስ የእግዚአብሔር ቃል በሞላ ምድሪቱ ላይ እንደተሠራጨ ይመለከታል። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነትና ብልጽግና መሠረት ነው። በሚታዘዙበት ጊዜ ይባረካሉ። በማይታዘዙት ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር እርግማን ይደርስባቸዋል።

በምዕ.3 ውስጥ የሊቀ ካህኑ የኢያሱን መንጻት አንብበናል። በ5፡5-11 ላይ ደግሞ የምድሪቱን መንጻት እናነባለን። ይህም ሰባተኛው ራዕይ ነው። በአንዳንድ መንገዶች ይህ ራዕይ ከዘሌዋውያን 16 ጋር ይመሳሰላል። እግዚአብሔር ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ላይ ኃጢአትን ያስወግዳል። ሕዝቡም ሁሉ አዲስ ሕይወት መኖር ይጀምራሉ።

8ኛው ራዕይ የሚመለከተው ማንን ነው? ምናልባት እስከ አሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያልተመለሱትን ነው፤ 6፡1-8 አንብቡ። እግዚአብሔር ወደ አገራቸው ሊመልሳቸው

መልዕክተኞችን ይልካል። በባቢሎን እንዲቀመጡ አይፈልግም። ስለዚህ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ አለባቸው።

በ6፡9-15 ላይ የሚገኘው ታሪክ 2 ነገሮችን ያመለክታል። በመጀመሪያ ወደ መሲሁ ያመለክታል፤ ምክንያቱም ነቢይና ንጉሥ ሁለቱን በአንድ ላይ ሊሆን የሚችል እርሱ ብቻ ነው። ምንም እንኳ ዳዊት በመጠኑም ንጉሥም ነቢይም ቢሆን በአይሁዳውያን አስተዳደር ይህ ነገር የማይቻል ነበረ። በሁለተኛ ደረጃ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ነገር እንደሚመዘን ያስተምረናል። ዘውዶቹ እንደ መታሰቢያ ሆነው በቤተ መቅደስ ተቀምጠው ነበር።

በቤቴል ትንሽ ሰዎች አሁንም ስለ ኢየሩሳሌም ውድቀትና ስለ ሴዴቅያስ ሞት መታሰቢያ የሚሆነውን ጾም ይጾሙ ነበር፥ 7፡1-14 አንብቡ። እግዚአብሔር ምን እንደፈለገ ለሕዝቡ ነገሯቸዋል፥ 7፡8-10። በአባቶቻቸው አለመታዘዝ ምክንያት የባቢሎን ምርኮ ደርሶባቸው ነበር፥ 7፡11-14። ዘካርያስ ጾማቸውን በመደገፍ ፈንታ የሚገሥጻቸው ለዚህ ነው፥ 7፡4-6። ስለ ኢየሩሳሌም ውድቀት ከማዘን ይልቅ ንስሐ መግባትና የቤተ መቅደሱን ግንባታ ሥራ መርዳት ይኖርባቸዋል።

አንዳንድ ምሁራን ከምዕ.8 ውስጥ 10 ተስፋዎችን ያወጣሉ። ይህ ምዕራፍ ከእርሱ የሚቀጥሉት ምዕራፎች በሙሉ ማጠቃለያ ነው። እግዚአብሔር በስምንቱ ራዕዮች የሰጣቸው ተስፋዎች በምዕራፍ ስምንት ተደግመዋል። ይህ የዘካርያስ የመጀመሪያ ስምንት ምዕራፎች አጠቃላይ ዓላማ መሆኑን አስታውሱ። ለሕዝቡ ማበረታቻ ያስፈልጋቸዋል። ከበረከቶቹ ጥቂቶቹን እናተኩርባቸዋለን፡- እግዚአብሔር ወደ ከተማይቱ ይመለሳል - ቁ.3፥ ሕዝቡን ያድናቸዋል - ቁ.7፥ በረከቶችን ይሰጣቸዋል - ቁ.12፥ መልካም ነገር ያቅድላቸዋል - ቁ.15፥ አስከፊ የሆኑት ጊዜያት ወደ ደስታ ይለወጣሉ - ቁ.19። የእግዚአብሔር ዕቅድ ለሕዝቡ ይህ ነው። ይህንን ነገር ለመቀበልም ሆነ ለመቃወም ነጻነት አላቸው።

# ዘካርያስ

## 1-8 የተለዩ ነጥቦች

አይሁዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ እግዚአብሔር ከፈራሳውያን ተፅዕኖ ነጻ የሚያወጣቸው መስሎ ታይቷቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን ይህን አላደረገም። ሆኖም የራሱን ሕዝብ እንደሚቆጣጠር እንዲሁ ፈራሳውያን በእርሱ ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ያሳስባቸዋል፥ 1፡1-21፤ 6፡1-8 በድጋሚ አንብቡ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከፈራሳውያን ሥልጣን ሥር ነጻ አውጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ይመልሳቸዋል፤ ስለዚህ እርሱን ማገልገል ይችላሉ።

ኢየሩሳሌም የቤተ ክርስቲያንና የእኛም ሕይወት ምሳሌ ልትሆን ትችላለች። እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው የመረጣቸውን ሰዎች የተለየ ጥንቃቄ ያደርግላቸዋል። የእርሱ ከተማና ቤተ ክርስቲያን ሊዝኑባቸው የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲያቅፉ ሰፋፊ ሆነው እንዲገኙ ይፈልጋል፥ 2፡1-5። አሁንም ጥቂት አይሁዶች በፋርስ ይኖራሉ። እነዚህም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው የመሲሁን መምጣት እንዲጠባበቁ ይጠራቸዋል፥ 2፡6-13።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሙሉ ጥንቃቄ ያደርጋል፤ ነገር ግን ለሚያገለግሉት የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ካህናት ንፁህ እንዲሆኑ ይፈልጋል፥ 3፡1-10። ንፁህ የሆኑ ሰዎች ብቻ ተቀባይነት ያለው አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ። በተጨማሪ በከተማይቱ ውስጥ ስለሚሠሩት ሌሎች አገልጋዮች ያስባል፥ 6፡9-15። በካህናትና በመሪዎች ላይ የሚያተኩርበት ምክንያት እነርሱ ወደ መሲሁ የሚያመለክቱ የእግዚአብሔር ተወካዮች ስለሆኑ ነው። በምዕ.3፡1-10ና 6፡9-15 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የተነገሩ ትንቢቶች እናገኛለን።

በተጨማሪ እግዚአብሔር ሕዝቡ በሙሉ እንዲያገለግሉት ያዘጋጃል። በ520 ዓ.ዓ. የነበሩት አይሁዶች ነጻ ለመውጣት ኃይል ፈልገው ነበር። በምዕ.4፡1-10 ውስጥ በሚገኘው ራዕይ እግዚአብሔር ለመሪዎችና ለሕዝቡ መንፈሱን የሚሰጣቸው እርሱ እንደሆነ ተስፋዎችን ሰጥቷቸው ነበር። እግዚአብሔር ዘሩባቤልን ስለመረጠው ለአገልግሎት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ያቀርብለታል፥ ምዕ.4፡6 ዘወትር ልናጠናው የሚያስፈልገን ጥቅስ ነው።

ኃጢአት ምድራቸውን ካረከሰው እግዚአብሔር ያቀደላቸው ሁሉ ምንም አይረዳቸውም። ዘሌ. 16 ወደ ቀራንዮ መስቀል እንደሚያመለክት ሁሉ እንዲሁ በተመሳሳይ መንገድ በምዕ.5 የሚገኙት ሁለት ራዕዮችም ያመለክቱታል። ምድሪቱን የሚያረክስ ኃጢአት እግዚአብሔር ራሱ ያስወግዳል። ይህን ከማድረጉ በፊት ሕጎች የማይለወጡ እንደሆኑ ያሳስባቸዋል፥ 5፡1-4። ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ በማይለወጡት ሕግጋቱ መሠረት ይቀጣሉ።

እግዚአብሔር በ536 ዓ.ዓ. አካባቢ ሕዝቡን እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም መልሷቸዋል። ለ16 ዓመታት ማለት እስከ 520 ዓ.ዓ. ድረስ ቤተ መቅደሱን መልሰው አልገነቡም። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ዘካርያስንና ሐጌን በመላክ በእነርሱ አማካይነት የቤተ መቅደሱን አምልኮ ሥርዓት እንዲጀምሩ ረድቷቸዋል። ከይሁዳ አገር ነዋሪዎች አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ ዕውሮች ስለሆኑ እግዚአብሔር የሠራውንና የሚሠራውን ማስተዋል አልቻሉም። ጊዜ ያለፈባቸውን ጾሞች መጾም ፈልገዋል። በ7፡1-14 ላይ የእነርሱ ኃጢአት ተገልጿል። በ586 ዓ.ዓ. የተፈጸመው የከተማይቱና የቤተ መቅደሱ ውድቀት እውነተኛ ምክንያትም ተጠቅሷል።

# ዘካርያስ 1-8

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

በማንኛውም ወቅት እግዚአብሔር ዓለምን መቆጣጠር ትቷል ብሎ ማሰብ ቀላል ነገር ነው። አዲስ ኪዳን ሰይጣንን «የዚህ ዓለም ገዥ» ብሎ ይጠራዋል። ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ ዓለምን የሚቆጣጠር መስሎ ስለሚታየው ነው። ሆኖም ዓለም በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ናት። እግዚአብሔር የክፉውንም ኃይላት እንኳ ለራሱ ፈቃድ መፈጸሚያ ይጠቀምባቸዋል። ጳውሎስ በሮሜ 8 ውስጥ ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንደማይችል ያሳየናል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በእኛ ያልተደሰተ መስሎ ይታየናል። በእንደዚህ ያለ ወቅት እንኳን ሰይጣን ከእርሱ ሊለየን አይችልም።

እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለቤተ ክርስቲያኑ የተለየ ሥፍራ እንዳዘጋጀ የኤፌሶን መልእክት ያሳየናል። ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛ ልደት ያገኙ ሰዎች ሁሉ ኅብረት ናት። እግዚአብሔር

ኢየሩሳሌምን እንደተንከባከባትና የሚያስፈልጋትን ሁሉ እንዳዘጋጀላት በተመሳሳይ መንገድ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሁ ያደርግላታል፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚያስብላቸው መጠን ለሕንጻውና ለአገልግሎቱ አያስብም። እርሱ ለሕዝቡ ስለሚጠነቀቅላቸው በኑሮአቸው የእርሱን ኃይል እንዲያሳዩ ይፈልጋል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በመቅደስ ያገለገሉትን ካህናት መርጧል። ሌዋውያን ካህናትን በአገልግሎት ረድተዋቸዋል። ሽማግሌዎች በአስተዳደር ጉዳይ ኅብረተሰቡን አገልግለዋል። እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ዝግጅት ያደረገው ሕዝቡ በስምምነት በአንድ ላይ በመዋሃድ መኖር እንዲችሉ ነበር። በአዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ዝግጅት አድርጓል። እያንዳንዱ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ለብዙዎች ጥቅም በተለያየ መንገድ ሊያገለግል ይችላል።

እግዚአብሔር አገልጋዮችን እንደጠራ ሁሉ ለአዘጋጀላቸው አገልግሎት ደግሞ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያቀርብላቸዋል። እግዚአብሔር ለኢያሱ፥ ለዘሩባቤልና ከእነርሱም ጋር ላገለገሉት በሙሉ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አቅርቦላቸዋል። በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ለአገልግሎት የሚያስፈልጉንን ነገሮች በሙሉ አዘጋጅቶልናል፥ ፊል.4፡19። የእግዚአብሔር ሥራ ለእኛ በጣም ከባድ ነው፤ ነገር ግን ከተመደበልን ሥራ ይልቅ የሚሰጠን ጉልበት በጣም የላቀ ነው። ፈቃዱን ለማሟላት እንድንችል የሚያስፈልገንን ሁሉ ከትዕዛዙ ጋር አቀናብሮ ይለግሠናል፥ ፊል.4፡19።

ሕዝቦቹ በማይነቀፍ መንገድ ሊያገለግሉት እንዲችሉ እግዚአብሔር እነርሱንና ምድራቸውን ከማንኛውም ርኩሰት ሁሉ እንደሚያጠራ ተስፋ ሰጥቷቸዋል። ዛሬም ለእኛ ተመሳሳይ ነገሮችን ያደርግልናል። ከኃጢአት እድፍ መንጻት እንደምንችል ተስፋ ተሰጥቶናል። ምክንያቱም እኛ ሰዎች በመሆናችን ሰይጣን ሊያታልለንና ኃጢአት ልናደርግ ስለምንችል ነው። ሆኖም ኃጢአት በምንሠራበት በማንኛውም ወቅት ምሕረት ልንቀበል እንችላለን። የማንኛውም ኃጢአት ባሪያ ልንሆን አይገባም። ይህ ይቅርታ ብርታትና ማስተዋል ይለግሰናል።

ሰይጣን የእስራኤላውያንንና በቤቴል ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ዓይን ማሳወር እንደቻለ የእኛንም ዓይን ዘግቶ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር እንዳንረዳ ማድረግ ይችላል። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ዝግጁዎች ስንሆን መንፈስ ቅዱስ የእርሱን ዕቅድ እንድንረዳ አዕምሮአችንን ይከፍትልናል። ይህንን ነገር ሊያደርግ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለዚህ በእኛ ውስጥ ገብቶ እንዲኖር ልባችንን እንክፈትለት።

# ዘካርያስ 1-8

## ጥያቄዎች

1. ከምርኮ በኋላ የተናገሩት ሶስት ነቢያት ማን ማን ናቸው?
2. ስለ 586 ዓ.ዓ. ድንገተኛ አደጋ የሚነገሩን ሶስት ምዕራፎች የትኞቹ ናቸው?
3. ስለ 70ዎቹ ዓመታት ምርኮ የተነበየው ማን ነው?
4. በባቢሎን የተጻፈው መዝሙር የትኛው ነው?

5. በባቢሎን ትንቢት ይናገሩ የነበሩት ሁለት ነቢያት ማንና ማን ነበሩ?
6. የሕዝቅኤል ልዩ ተልእኮ ምን ነበር?
7. የፋርስ መንግሥት በሥልጣን ላይ የቆየው ከስንት እስከ ስንት ዓ.ዓ. ነበር?
8. በፋርስ ግዛት በሱሳ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ታሪክ በመጠኑ የሚነገረን የትኛው መጽሐፍ ነው?
9. በ536 ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ይመራቸው የነበረው ማን ነበር?
10. ዕዝራ 1-6 የሚነገረው ስለ የትኛው ዘመን ነው?
11. ከሚክያስ ጋር የሚመሳሰለው የታሪክ መጽሐፍ የትኛው ነው?
12. የይሁዳ የመጨረሻ ንጉሥ ማን ነበር?
13. ሕዝቡ ከባቢሎን ተመልሰው ከ536-520 ዓ.ዓ. ድረስ ለ16 ዓመታት ምን ይሰሩ ነበር?
14. በዘካርያስ ዘመን ይሁዳን ይመራ የነበረው መንግሥት የትኛው ነበር?
15. ከዳርዮስ በፊት የፋርስ ንጉሥ ማን ነበር? 16. ዘካርያስ የተናገረው በማን ዘመነ መንግሥት ነበር?
17. ዘካርያስ የተናገረው ለማን ነበር?
18. በ536 ዓ.ዓ. ዳንኤል በሕይወት ይኖር እንደነበር የሚያሳየን የትኛው ምዕራፍና ቁጥር ነው?
19. ሕዝቅኤል በምዕ.40-48 ውስጥ የሚናገረው ስለ ምንድነው?
20. ዘካርያስ 1-8ን እንድንገነዘብ የሚረዱን ሁለት አጫጭር ጽሑፎች የትኞቹ ናቸው?
21. የዘካርያስ 1-8 አቢይ ትምህርት ምንድነው?
22. በዘካርያስ 1-8 ውስጥ ስንት ራዕዮች ይገኛሉ?
23. ዘካርያስ የተለየ ማበረታቻ ይሰጥ የነበረው ለማንና ለማን ነበር?
24. የባቢሎን ቤተ መቅደስ በምን ተተክቶ ነበር?
25. በዚህ ዘመን ይሁዳ ትገዛ የነበረው በየትኛው መንግሥት ነበር?
26. የአራቱ ቀንዶች ትርጉም ምንድነው?
27. በምዕ.3 በምሳሌ የተጠቀሰው የማን ባሕርይ ነው?
28. ምዕ.4 የሚያወራው ስለ ማን ነው?
29. በምዕ.5፡5-11 የነጻው ነገር ምንድነው?
30. ወዳልተመለሱት የእስራኤል ሰዎች የሚያመለክተው የትኛው ራዕይ ነው?
31. በምዕራፍ ሰባት የተጠቀሱት ሰዎች ስሕተት ምን ነበር?
32. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን እንክብካቤ የሚያሳየን የአዲስ ኪዳን መልዕክት የትኛው ነው?
33. በአዲሱ ቃል ኪዳን ካህናት እነማን ናቸው?

# ትምህርት ስምንት

## ዘካርያስ 9-14

### ታሪካዊ አቀማመጥ

ዘካርያስና ሐጌ ከዘሩባቤል ጋር ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል። በዚያን ጊዜ ኢያሱ ሊቀ ካህን ነበር። ሕዝቡ የተመለሱት በ536 ዓ.ዓ. ነበር። ሆኖም ምድራቸው ከ586-536 ዓ.ዓ. ለ50 ዓመታት ምንም አይሠራበትም ነበር። በ606 ዓ.ዓ. ኢዮአቄም ከተማረከ በኋላ ብዙዎቹ ሰዎችወደ ባቢሎን ተወስደው ነበር። ይህም ኤር.25፡11፣ 29፡10 ላይ የተነበየው የሰባው ዓመታት ምርኮ ነው። እግዚአብሔር በምሕረቱ ለብዙዎቻቸው ቀኑን ወደ 50 ዓመታት ዝቅ አድርጎታል።

በ536 ዓ.ዓ. ከዘሩባቤል ጋር የተመለሱት ምርኮኞች ጎረቤት አገሮቻቸውን ይፈሩ ነበር። ዕዝ.1-6 በተለያዩ ሥፍራዎች የነበረውን ጭንቀት ይነግረናል። ከ536-520 ዓ.ዓ. ለ16 ዓመታት ቤተ መቅደሱን መሥራት አልጀመሩም ነበር። ዳርዮስ ካምቢሲስን ተክቶ በ520 ዓ.ዓ. የፋርስ ንጉሥ ሆኗል። ልክ በዚያ ወቅት እግዚአብሔር ሁለት ነቢያት ማለት ሐጌንና ዘካርያስን ለአገልግሎት ጠርቷቸዋል።

ዘካርያስ በ1-8 ውስጥ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ተናግሯቸዋል። ማበረታቻ ያስፈልጋቸው ስለነበር ከምዕ. 1-8 ባለው ክፍል ውስጥ ዘካርያስ ከእግዚአብሔር ያገኛቸውን ስምንት ራዕዮች ነግሯቸዋል። በአጠቃላይ ምዕ.1-8 የተነገረው በ520 ዓ.ዓ. በኢየሩሳሌም ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ነበር። በዚህ ምክንያት ከ9-14 ክፍል ጋር ይለያያሉ። ከምዕ. 9-14 ባለው ክፍል ውስጥ የኢያሱንና የዘሩባቤልን ስም አናገኝም፤ ራዕዮችም የሉም።

ሆኖም በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ከፋርስ ወደ ይሁዳ አልተመለሱም ነበር። ኤርምያስ በ29፡4-23 እንደነገራቸው ቤቶች ሠርተው ከፋርስ ኅብረተሰብ ጋር ተቀላቅለዋል። ለይሁዳ እንግዶች ነበሩ። ቤተ መቅደሱን በፍፁም አይተው አያውቁም ነበር። ሕይወታቸውን እንደገና ከዜሮ ጀምረው ለመገንባት አልፈለጉም። በምርኮ ያሉ አይሁዶች ሆነው መኖር ደስ ያሰኛቸው ነበር። ቢሆንም ብሉይ ኪዳን ስለነዚህ ሰዎች ብዙ አይነግረንም።

ዘካርያስ 9-14 የሚመለከተው በፋርስ ያሉትን አይሁዶች ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም የነበሩትንም ጭምር ነው። ዘካርያስ ከ1-8 ውስጥ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት አይሁዶች በሙሉ እግዚአብሔር ዕቅድ እንዳዘጋጀላቸው ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለሆነ መፍራት እንደማይገባቸው ነግሯቸዋል። በምዕ.9-14 ተመሳሳይ ዕውነቶች ሥዕላዊ በሆነ መንገድ ተገልፀው እናገኛለን። በፋርስ የነበሩት ብዙ አይሁዳውያን በዕዝራ ከ1-6 ላይ የተመዘገበውን ዜና ሲሰሙ ተስፋ ቆርጠው ለመመለስም አይፈልጉም ነበር።

በ536 ዓ.ዓ. ብዙዎቹ በዘሩባቤል መሪነት ተመልሰዋል፤ በ457 ዓ.ዓ. ዕዝራ የሌላ ትልቅ ተመላሽ ቡድን መሪ ነበር። በ444 ዓ.ዓ. እንደገና ሌላ ትልቅ ቡድን ከነህምያ ጋር ተመልሷል። በዘሩባቤልና በነህምያ መካከል የነበረው የዘመን ርቀት 100 ዓመታት ያህል እንደነበር ተገንዘቡ። በእነዚህ ዘመናት ውስጥ ደግሞ ምናልባት ብዙ ሌሎች ሰዎች ሳይመለሱ አይቀርም። ከዚህ ጊዜ በኋላ እስከ ጌታችን ኢየሱስ ድረስ ማለት ለ400 ዓመታት ያህል በኢየሩሳሌም የተፈፀሙት ነገሮች በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ በሰፊው ተጽፈዋል።

# ዘካርያስ 9-14

## የነቢዩ ሸክም

እነዚህ ስድስት ምዕራፎች ሶስት የተለያዩ ትርጉሞች አሏቸው። ከእነዚህ ትርጉሞች መካከል አንዱን ብቻ መምረጥ አያስፈልገንም። በአንዱ ላይ ትኩረት ስናደርግ ሌሎቹን ሁለት ትርጉሞች ተውናቸው ማለት አይደለም። ሶስቱ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡-

ታሪካዊ - የአይሁዶችን ታሪክ የሚመለከት፥

ትንቢታዊ - አሁንም ትንቢት፥

ተግባራዊ - ለክርስቲያኖች ምክር።

ከእነዚህ መካከል አንዱን ብቻ ወስዶ ሌሎቹን ሁለት ትርጉሞች ከነጭራሹ መተው ትክክል አይደለም።

ሐጌ 1-2 በዚህ ወቅት የኢየሩሳሌም ሁኔታ እንዴት እንደነበር ይነግረናል። በእርግጥ ሁኔታው ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር። ሕዝቡ በየትኛውም አቅጣጫ ቢመለከቱትም ተሸናፊዎች መሆናቸው ይታያቸዋል። የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር እስከ 444 ዓ.ዓ. እስከ ነህምያ ጊዜ ድረስ አልታደሰም ነበር። የተመለሱት ሕዝቦች እስከ አሁን ምንም ሥራ ካልሠሩ ገና ያልተመለሱት እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው እርግጠኛ መሆን የሚችሉት እንዴት ነው?

ከባቢሎን በ536 ዓ.ዓ. የተመለሱት እስከዚህ ጊዜ ድረስ መቅደሱን መልሰው አልገነቡም። በጣም የሚያማምሩ ቤቶች ለራሳቸው ለመሥራት ገንዘብና ጉልበት አልቸገራቸውም። እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር መመልከት ተስኗቸዋል። ኤርምያስና ሕዝቅኤል፥ በተጨማሪ በኢሳይያስ ምዕ.40-66 ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያወጣውን እቅድ ተናግረዋል። ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ሰዎች እስከ አሁን የእግዚአብሔርን እቅድ አልተረዱም።

ሕዝቡ ሲመለሱ መሠዊያውን መልሰ ሠርቶ መሥዋዕት ማቅረብ ጀምሯል፥ ዕዝ.3፡1-6 እንብቡ። ቤተ መቅደሱን መልሰው መገንባት በጀመሩበት ወቅት ብዙዎቹ ያልጠበቁት ነገር ስለሆነባቸው አልተደሰቱም ነበር፥ ዕዝ.3፡12-13። የሰማርያ ሰዎች በቤተ መቅደሱ ግንባታ ሊተባበሩዋቸው ፈልገው ነበር። ነገር ግን ዘሩባቤል ዕርዳታቸውን አልተቀበለም፥ ዕዝ.4፡1-2። ሌሎች ደግሞ የቤተ መቅደሱን ሥራ ለማደናቀፍ ሞክረው ነበር፥ ዕዝ.4፡6-23።

ሕዝቡ ዓይኑን ወደ እግዚአብሔር እንዲመልስ ማድረግ የነቢያት ሥራ ነበር። ዘካርያስ ከ9-14 ባለው ክፍል ሲሠራ የምንመለከተው ይህንን ተግባር ነው። ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንደገና አድሷል፥ ዕዝ.6፡13-18፤ ሐጌ 2፡15-19። እንደገናም እንደ ፋሲካ ያሉትን የበዓል ቀኖች ማክበር ጀምሯል፥ ዕዝ.6፡19-22። ይህንንም ያደረጉት በ514 ዓ.ዓ. ነበር፥ ዕዝ. 6፡15። ይኸውም ዕዝራ ከተመለሰበት ከ457 ዓ.ዓ. አንሥቶ እስከ 514 ዓ.ዓ. ድረስ 59 ዓመታት አልፈው ነበር።

የእግዚአብሔር ዕቅድ እያደር የሚፈካ ነው። ጌታ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የፈፀመውን ድርጊት ና ወደፊት በበለጠ መንገድ ያደርገዋል። ለእነርሱ ያደረገውን ነገር በሙሉ ለእኛም ደግሞ ያደ ገልናል። የእግዚአብሔር ዕቅድ በብሉይና በአዲስ ለሚገኙት ሕዝቦቹ በሙሉ ነው። ወደፊት ለሁሉም የሚደረጉ ገና ብዙ የቀሩ ነገሮች አሉ። እነዚህን ምዕራፎች በምንመለከትበት ወቅት ለእያንዳንዱ ድርጊት ከአንድ በላይ ትክክለኛ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል እንዘንጋ።

# ዘካርያስ 9-14

## ማብራሪያ

ዘካርያስ ይህንን አዲስ ክፍል የሚጀምረው እግዚአብሔር በእስራኤል ጠላቶች ላይ ድል እንደተጎናፀፈ ለአንባብያኑ በማብሰር ወይም በማሳሰብ ነው፥ 9፡1-8። የተሸናፊዎቹ አገሮች የስም ዝርዝር ከሶሪን ይጀምርና የፍልስጥኤምን ከተሞች ያጠቃልላል። ሕዝቡ ከቀድሞ ንጉሶቹና ከአረመኔዎች ነገሥታት በጣም የሚለይ አዲስ መሪ ይኖረዋል፥ 9፡9-10። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደገና መርዳት ይጀምራል፥ 9፡11-17። ነጻ ያወጣቸዋል፥ 9፡11። ከአደጋ ይጠብቃቸዋል፥ 9፡15። ያጸናቸዋል፥ 9፡16። እግዚአብሔር ለእነርሱ ለማድረግ ከሚያቅድላቸው ዕቅድ የተነሣ ምንም ነገር አይጎድልባቸውም። እንደ ገና መምራት ሲጀምር የሚሹትን ሁሉ ያቀርብላቸዋል።

ምዕ.10 በጠቅላላ ነጻ በመውጣታቸው ትምህርት ላይ ያተኩራል። በምርኮና በቅድስቲቱ አገር በነበሩበት ወቅት በጣኦት አምልኮ መሳተፍ አይከብዳቸውም ነበር። እንደዚህ ያለው ጣኦት አምልኮ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ርቀው ምን ያህል ተቅበዝባዥ እንደሆኑ ያሳያል፥ 10፡1-2። ወደ ከንቱ ሃይማኖት የመሩአቸው የባዕድ ሰዎች ይቀጣሉ፥ 10፡3-5። የዚህ ምዕራፍ የቀረው ክፍል የሚናገረው በተለይ እስከ አሁን በምርኮ ላይ ስላሉት ነው። እግዚአብሔር ሊያድናቸው ይፈልጋል፥ 10፡6፤8። በድጋሚ የራሱ ሕዝብ አድርጎ ይቀበላቸዋል፥ 10፡6-7። ደግሞም የሚገኙት የትም ሲሆን ከያሉበት መሰብሰብ እንዲችሉ ይረዳቸዋል፥ 10፡8-12። በሚያመጣቸው መንገድ ላይ ምንም ዓይነት እንቅፋት ቢኖርም እርሱ ያለምንም ጉዳት ይመልሳቸዋል፥ 10፡11-12።

አንድ የአመራር መንገድ በምዕ.3 ውስጥ ተሰጥቷል። እግዚአብሔር ኢያሱ ለአገልግሎት ብቃት እንዲኖረው የሚያደርግ መሆኑን አሳይቷቸዋል። ስለ መጥፎዎቹ መሪዎችስ? በምዕ. 11፡1-3 በግዙፍ ዛፍ ተመስለዋል። እነርሱም ሊደመሰሱ ነው። ነቢዩ ነገሩን በምሳሌ እንዲያሳይ ተነግሮታል፥ 11፡4-6። ነገር ግን ሁኔታውን በድርጊት በሚያሳይበት ወቅት በጎቹ

ማለት ሕዝቡ መልካም እረኛ የማይፈልጉ መሆኑን ይደርስበታል፤ 11፡7-14 አንብቡ። በዚህ ጊዜ ለመሪዎችና ለሕዝቡ የእነርሱ ተቃውሞ የሚያስከትለው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ፍርድ ብቻ እንደሆነ ይነገራቸዋል። ሆኖም ለእረኛው ካለመታዘዙ የተነሣ እጅግ ከባድ ፍርድ ይደርስበታል፥ 11፡15-17 ተመልከቱ። ተመሳሳይ ሁኔታ በኢየሱስና በአይሁዶች ተገልጿል።

ብዙሃኑ መጥፎዎች ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ቃሉን አያጥፍም። በፍፁም አይተዋቸውም። የማያምኑት መንግሥታት እግዚአብሔር የሚሠራውን ነገር ለማጥፋት ይጥራሉ፥ 12፡1-5 ተመልከቱ። እግዚአብሔር ሕዝቡ መቆም እንዲችል መለኮታዊ ብርታት ይሰጠዋል፥ 12፡6-9። ይህም ሁኔታ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆኑን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። የእርሱ ኃይል መገለፅ በኑሮአቸው ላይ ለውጥ የማምጣት ብርታት አለው። ላደረጉአቸው ኃጢአቶች በሙሉ ያዝናሉ፥ 12፡10-14፤ 11፡9-11 አወዳድሩ። እነዚህ ግድ የለሽ ሰዎች እግዚአብሔር በኃይሉ ሲረዳቸው በሚመለከቱበት ወቅት ንሥሐ ይገባሉ። እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ዛሬም ለእያንዳንዳችን ያገለግላል።

በአንዱ ሥቃይ ብዙዎች የመዳን ዕድል ማግኘታቸው በብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ተጠቅሷል። እነዚህ ትምህርቶች የኢየሱስን ሞት እንድንተረጉም ያዘጋጁናል። ይህ ትምህርት በ13፡7-9 ውስጥ ይገኛል። በማቴ. 26፡31ና በማር. 14፡27 ኢየሱስ እነዚህን ቃላት ለራሱ ጠቅሷቸዋል። በ12፡10-14 ሕዝቡን ወደ ለውጥ ስለሚያደርስ ንሥሐ አንብበናል። ይህንን በሚያደርጉበት ወቅት የኃጢአት ዘር በሙሉ ከከተማይቱና ከሕዝቡ ሕይወት ጨርሶ ይወገዳል። ዘካርያስ በ13፡2-6 የሚያመለክተው ጥሩዎቹን ነቢያት ሳይሆን ቁጥር 2 እንደሚያሳየን ሐሰተኞቹን ነው። በቁ.1ና በቁ.9 ላይ የመንጻት ትምህርት እንዴት እንደተገለፀ አስተውሉ።

ከምንም ነገር ይልቅ የሥቃይ ወቅት የእግዚአብሔርን ለዋጭ ኃይል ጉልህ አድርጎ ያሳያል። እግዚአብሔር ሕዝቡን የመርዳት ፍላጎቱ የቱን ያህል ትልቅ እንደሆነ ለማሳየት ዘወትር ይጠቀምበታል፥ 14፡1-5 አንብቡ። ውጤቱን ተመልከቱ። በምድራቱ ውስጥ አጠቃላይ ለውጥ ሊደረግ ነው። ምዕራፉ ሶስት የተደራረቡ ትርጉሞች ሊኖሩት እንደሚችል አስታውሱ፤ እያንዳንዱ ትርጉም የእግዚአብሔርን ባሕርይና ሥራ በተለያየ መንገድ ይገልጻል። በምትታየዋ ዓለም ውስጥ የሚያደርገው ነገር ሁሉ በመንፈሳዊው ዓለም ሊሆን የሚችለውን ሊያብራራ ይችላል። እግዚአብሔር ይህንን ለውጥ በሚያመጣበት ጊዜ ለእርሱ የሚለዩት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ተራ የሆኑትን የሕይወት ጉዳዮች ሳይነካ አይቀርም፥ ዘካ. 14፡16-19፤ 20-21። ሕዝቡ ይህንን ተረድተው መበርታትና ከፋርስ መመለስ ይኖርባቸዋል።

# ዘካርያስ 9-14

## የተለዩ ነጥቦች

እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን ሲፈጥራቸው ዕቅዱ እርሱን እንዲያመልኩ ከሚያግዷቸው ከማናቸውም ነገሮች ነጻ እንዲሆኑ ነበር። እስከ አሁንም የእግዚአብሔር ዕቅድ

ይህ ነው! የምዕ.9 ርእስም ይህ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች በተለይም ፍልስጥኤማውያን ድል ይደረጋሉ። ከዚያም ሕዝቡ እግዚአብሔርን በነጻነት ማገልገል ይችላል። እጅግ ታላላቅ ጠላቶቻቸው በልባቸው ውስጥ ያሉት ነበሩ እንጂ በውጭ የሚገኙት አልነበሩም።

ብሉይ ኪዳን የተሞላው እግዚአብሔር ሕዝቡን ከክፉ ሁሉ የሚያድን መሆኑን አጉልተው በሚያሳዩ ታሪኮች ነው። ዓለም፥ ሥጋና ሰይጣን ያለማቋረጥ ሕዝቡን ወደ እስራት ይወስዱታል። በምዕ. 10 ውስጥ የዘካርያስ መልዕክት እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው ነው ሆኖም ይህንን ከማድረጉ በፊት ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ይኖርባቸዋል። ለመዳን የማይፈልጉ ከሆነ ምንም ሊረዳቸው አይችልም።

ለራሳቸው ጥቅም ብቻ የሚፈልጉ አንዳንድ እረኞች ማለት መሪዎች ነበሩ። ሕዝቡን ለመርዳት አያስተዳድሩም ነበር። እግዚአብሔር ልባቸውንና ሥራቸውን በሚገባ ያውቃል። ነቢዩ የእግዚአብሔርን መልስ ለመግለፅ በምሳሌ ተናገሯል፥ ዘካ.11 ደግማችሁ ተመልከቱ። አንዳንዶቹ ሰዎች እንደቀድሞው መጥፎዎች ነበሩ! እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ መሪ እንዲሆን አይፈልጉም። ለእረኞችና ለበጎች ትክክለኛ ፍርድ ይፈርድላቸዋል።

የእግዚአብሔር ሕዝብ በውጭ ጠላቶቹ በፍፁም አይሸነፍም። እግዚአብሔር ይከልላቸዋል። ሆኖም እርሱ እንዳዘዛቸው ባይኖሩና ኃጢአትን ባያስወግዱ በውስጣቸው ባሉት ጠላቶች ይሸነፋሉ። ይህ የምዕ. 12 መልዕክት ነው። በኤርምያስ ዘመን የኢየሩሳሌም ሰዎች ኑሮአችን ምንም መጥፎ ቢሆንም እግዚአብሔር ከተማይቱን ይከልላታል ብለው ያስቡ ነበር። እውነት አልነበረም። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጠብቀው ለእርሱ ታማኞች ሲሆኑ በእርሱም ቃል ለመመራት ፈቃደኞች ሆነው መንፈሱ በሕይወታቸው እንዲኖር በሚሹበት ወቅት ነው።

እነርሱ ራሳቸውን ሊያጠፉ አይችሉም። እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ በሁለት መንገድ ያጠራል:- 1/ጣኦታትን በሙሉ ከሕይወታቸውና ከምድራቸው ጠርጎ በማስወገድ፥ 13:1-6። 2/ በተጨማሪም በመከራ፥ 13:7-9። እረኛው ለበጎቹ ሲል ይሰቃያል፥ በጎቹም በተመሳሳይ መንገድ ይሰቃያሉ። የዚህ ሁሉ ነገር ዓላማ ሕዝቡን ለመፈተንና ለማጥራት ነው። የመጨረሻው ውጤት ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለማገልገል ዝግጁ ሆነው መገኘታቸው ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡ ታማኝ ምስክሮቹ እንዲሆኑ በማለት መከራ እንዲደርስባቸው ይፈቅዳል፥ 14:1-5። በኤር.31:15-20 ላይ የተጠቀሰው ዓይነት ሥቃይ የተሰጠው ተቀባዮቹ የእግዚአብሔርን የደኅንነት ዕቅድ ይበልጥ እንዲረዱት ለማስተማር ነው። ሕዝቡና ንብረታቸው ለእግዚአብሔር የተለዩ ናቸው። እነርሱ የእርሱ ናቸው፥ ስለዚህ ያላቸውን ሁሉ ለአገልግሎቱ ያበረክታሉ።

# ዘካርያስ 9-14

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

ኢየሱስ እንደ ሕይወታቸው ጌታ ለተቀበሉት ሁሉ ዘላቂ ነጻነት ሰጥቷቸዋል። ጳውሎስ በሮሜ 5-6 እንደሚያሳየን ይህ በእርግጥ ነጻ የመሆን የመጀመሪያው ደረጃ ነው። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ ይህንን ሕይወት እንዲጠብቅ ፈቃድ ካልተሰጠው ኃጢአት እንደገና ይገባል። ጳውሎስ ይህንን ትምህርት በገላትያ 3 ውስጥ ያስፋፋዋል። ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ክርስቲያን ብቻ እውነተኛ ነፃነት ያገኛል፥ ይኸውም እግዚአብሔር ክርስቲያን የሚጠብቀውን ዓይነት ሕይወት ለመኖር የሚያስችል ነጻነት ነው።

ኃጢአት በብዙ የተለያዩ መንገዶች ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት ይገባና እንደገና ባሪያዎች ያደርጋቸዋል። ይህ በሚሆንበት በማንኛውም ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለንሥሐ ይጠራቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድናቸው አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም። ነገር ግን ምን ጊዜም ከእርሱ ርቀው በሚቅበዘበዙበት ወቅት እንዲመለሱ ይጠራቸውና እነርሱንም ለማዳን እጁን ይዘረጋል። እግዚአብሔር ማንኛውም የእርሱ ቤተሰብ ከእርሱ ፍቅርና እንክብካቤ ተለይቶ እንዲኖር ፈቃዱ አይደለም።

ኢየሱስ ራሱ በዮሐንስ 10 ውስጥ እንዳስተማረን መልካም እረኛ እርሱ ነው። የእርሱ ቤተሰብ እንደበጎች ነው፥ ምክንያቱም ንብረቱ ነው። ዛሬም ደግሞ መጥፎ እረኞችና በጎች አሉ። ኢየሱስ በማቴ. 23፡1-12 እነዚህንና የመሳሰሉትን ጠቀሟል። ራሳቸውን ብቻ ለማርካት የሚያገለግሉትን መሪዎች እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። የእግዚአብሔር ፍርድ ቅን ስለሆነ እነርሱን ከመዋጋት ይልቅ ፍርድን ለእርሱ መተው ይገባናል።

ከሐዋ. ሥራ እንደምንረዳው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጠላቶች ነበሩአት። በብዙ ሥፍራዎች አይሁዶች ራሳቸው ክርስቲያኖችን አሳደዋል። 1ኛ ጴጥሮስ የተጻፈው እንደዚህ ላሉት የክርስቲያን ቡድኖች ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ ደግሞ የተጻፈ ክርስቲያን በመሆናቸው ምክንያት ለተሰደዱ ሰዎች ነው። በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸው እምነት እስካጠነከሩ ድረስ አሸናፊዎች ነበሩ። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ስደት እንዳይደርስ አልተከላከለም! ደግሞም አይከላከልም። ነገር ግን በዚያ ውስጥ እንዲጠነክሩ ያደርጋቸዋል።

ኢየሱስ «ልበ ንፁሐን ብፁአን ናቸው» ብሏል። ልብን ግን ንፁሕ ማድረግ የሚችለው ማን ነው? ወይስ ይህ ነገር የሚቻል ነው? ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር ይቻላል! እርሱ ከማንኛውም ርኩሰት ሊያጠራን ይችላል። በምን ወቅት? እርሱን በምንጠይቅበት በማንኛውም ወቅት ይችላል። 1ኛ ዮሐ. 1 እንደሚያስተምረን ኃጢአት አላደረግንም ማለት አንችልም። ሆኖም ለሠራናቸው ለማናቸውም ኃጢአቶችና ለሁሉም ምሕረት ተቀብለናል ማለት እንችላለን።

አልፎ አልፎ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር አንዳንድ ነገር መስጠት ይፈልጋሉ። ይህን የሚያደርጉት በታላላቅ ስብሰባዎች ጊዜ ነው፤ መልካም ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ይፈልጋል! እግዚአብሔር ያለንን ሁሉ ጥቃቅኑንም እንኳ ሳይቀር በእርሱ ትዕዛዝ ሥር

እንድናደርገው ይፈልጋል። በእርሱ ሥር ያልዋለውን ማንኛውም ነገር ሰይጣን ሊጠቀምበት ይችላል። የሮሜ 12፡1-2 ትምህርት ለሁሉም ክርስቲያን አስፈላጊ ነው።

# የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከሐጌ ጋር በአንድ ዘመን የተናገረው ነቢይ ማን ነበር?
2. በሐጌና በዘካርያስ ዘመን የሕዝቡ አስተዳዳሪ ማን ነበር?
3. በ520 ዓ.ዓ. ሊቀ ካህን ማን ነበር?
4. [illegible]ሁዳ ባዶ የነበረችው ለስንት ዓመታት ነው?
5. ኢዮአቄም የተማረከው መቼ ነበር?
6. ዳርዮስ የፋርስ ንጉሥ የሆነው መቼ ነበር?
7. የ536-520 ዓ.ዓ. ታሪክ ተጽፎ የምናገኘው የት ነው?
8. በዘካ.1-8 ስንት ራዕዮች ይገኛሉ?
9. ዘካርያስ ይናገር የነበረው ስለ የትኞቹ ሕዝብ ነው?
10. የዘካ.9-14 ትንቢት የተነገረው ለማን ነው?
11. ኤርምያስ 29፡4-23 የሚሰጠው ምክር ምንድነው?
12. ብዙ አይሁዶች ከፋርስ ያልተመለሱት ለምንድነው?
13. ዘሩባቤል ብዙ አይሁዶችን ይዞ ከፋርስ ወደ ይሁዳ የተመለሰው መቼ ነበር?
14. ከነህምያ እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ድረስ ያለው ዘመን ስንት ዓመታት ይሆናል?
15. ከሐጌ እስከ ነህምያ ምን ያህል ዓመታት ይሆናል?
16. ከምዕ.9-14 የሚገኘው ክፍል ያለው ሶስት ትርጉም ምን ምንድነው?
17. ቤተ መቅደሱ ተመልሶ የተገነባው በነማን ዘመን ነበር?
18. የከተማይቱ ቅጥር ተመልሶ የተገነባው መቼ ነበር?
19. ኢሳ.40-66 የሚተነብየው ስለ ምንድነው?
20. ዕዝ.3-4 የሚነግረን ስለ ምንድነው?
21. ሕዝቡ እንደገና ፋሲካን ማክበር የጀመረው መቼ ነበር?
22. የምዕ.10 ትምህርት ምንድነው?
23. እግዚአብሔር ሕዝቡን በተለያየ መንገድ እንደሚፈትን የሚናገረው የትኛው ምዕራፍ ነው?
24. ሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ እርግጠኞች መሆን የሚችሉት ምን ጊዜ ነው?
25. በተለይ ስለ ነጻነት የሚናገሩ ሁለት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
26. እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድናቸው በምን ወቅት ነው?
27. የዘካርያስ 13 ትምህርት ምንድነው?
28. የእግዚአብሔር መሆን የሚገባው ምን ያህል ነገር ነው?
29. በስደት ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ያደርጋል?
30. ከዮሐ.10 ጋር ተመሳሳይነት ያለው የዘካርያስ ምዕራፍ የቱ ነው?

# ትምህርት ዘጠኝ

## ሐጌና ሚልክያስ

### ታሪካዊ አቀማመጥ

የአሶር ዋና ከተማ ነነዌ ነበረች። በጣም ሰፊ ከተማ ስትሆን ዮናስ እና ናሆም ለእርሷና ስለ እርሷ ተናግረዋል። አሶር በደከመችበት ወቅት ባቢሎን እርሷን ለመጣል ብዙ አጥቅታታለች። የግብፁ ፈርኦን ኒካኡ ባቢሎንን ስለፈራት በቶሎ ከአሁኑ ለመቅጫት የአሶር አጋር ሆኖ ዘምቷል። ኢዮስያስ ግን አሶርን ይጠላ ስለነበር ባቢሎን ብታሸንፍ መልካም ሳይሆን አይቀርም በሚል ሃሳብ የግብፁን ፈርኦን ወደ አገሩ ለመመለስ ሠራዊቱን አሰልፎ ነበር። ኢዮስያስም ከግብፅ ጦር ጋር በውጊያ ላይ ሳለ በ609 ዓ.ዓ. በመጊዶ ሜዳ ተገድሏል። ነነዌም በ612 ዓ.ዓ. ተደመሰሰች። በ606 ዓ.ዓ. አሶር ጨርሳ ተደምስሳ ባቢሎን የዓለም ኃያል መንግሥት ሆናለች።

የሜዶን ንጉሥ ቂሮስ በ540-39 ዓ.ዓ. ፋርስን መውጋት ጀመረ። ፋርስንም አሸንፎ ራሱን የፋርስ ንጉሥ ብሎ ሰየመ። ከዚያም በ538 ዓ.ዓ. ገደማ ባቢሎንን ወግቶ አሸነፈ። ኢሳይያስ በ700 ዓ.ዓ. ገደማ ስለዚህ ነገር ትንቢት ተናግሮ ነበር፥ ኢሳ.45፡1-4፥ 13፤ 48፡12-13። አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ቂሮስ ፈቅዶላቸዋል። አብዛኛው ሕዝብ ሀብታም ሊሆን በሚችልበት በባቢሎን መቆየት መርጧል።

በ536 ዓ.ዓ. ገደማ ዘሩባቤል 43000 የሚያህሉ አይሁዶችን እየመራ ከፋርስ ገና ነጻነቷን ሙሉ ለሙሉ ወዳልተጎናፀፈችው ወደ ይሁዳ ይዞ ተመለሰ። ዘሩባቤል ምናልባት የፋርስ መንግሥት ቅጥር ሠራተኛ ሳይሆን አይቀርም። ይሁዳ ከ586-536 ዓ.ዓ. ድረስ ለ50 ዓመታት ያህል ተገቢው ጥበቃ ሳይደረግላትና ሳትታረስ ቆይታ ነበር። 70 ዓመታት ምርኮ ብለን የምንናገረው የመጀመሪያው ቡድን የተማረከው በ606 ዓ.ዓ. ስለነበረ ነው፥ ኤር.25፡11፤ 29፡10። ከባቢሎን እስከ ኢየሩሳሌም ሶስት ወር ተጉዘው የተመለሱት አይሁዶች ይሁዳ ሲደርሱ በተመለከቱት ሁኔታ እጅግ ሳይተክዙ አልቀሩም።

ከ79 ዓመታት በኋላ በ457 ዓ.ዓ. ዕዝራ ሌላ ቡድን ይዞ ከባቢሎን ወደ ይሁዳ ተመልሷል፥ ዕዝ.7-10 አንብቡ። የዕዝራ የመጀመሪያ ስድስት ምዕራፎች የሚነገሩን ስለ 536 ዓ.ዓ. እንጂ ስለ 457 ዓ.ዓ. አይደለም። ስለዚህ በም6.6ና 7 መካከል የ79 ዓመታት ርቀት አለ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም ነቢያት አልነበሩም። በዕዝራ 7-10 ላይ ከምናገኘው ዘገባ በስተቀር ስለዚህ ጊዜ የምናውቀው ብዙ ነገር የለም።

ዕዝራ ከሄደ ከ13 ዓመታት በኋላ ነህምያ ሌላ የአይሁድ ቡድን ከፋርስ ሱሳ ወደ ኢየሩሳሌም በ444 ዓ.ዓ. ገደማ እየመራ ይዞ ተመልሷል። ይህ ታሪክ በነህምያ 1-13 ውስጥ ተዘርዝሯል። በነህምያና በሚልክያስ መጽሐፎች ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሣ ሚልኪያስ በዚህ ዘመን ሰብኳል ብለን እንገምታለን። በሚልክያስ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈበትን ወቅት የሚጠቁመን ነገር በፍፁም አናገኝም።

ወደ አሶር በ722 ዓ.ዓ.፣ ወደ ባቢሎን በ606፣ በ597 እና በ586 ዓ.ዓ. ከተወሰዱት አይሁዶች ውስጥ አብዛኞቹ በዓለም ሁሉ ተበታተኑ እንጂ ወደ ይሁዳ አልተመለሱም። ጳውሎስና የጥንት ክርስቲያኖች ወንጌልን መስበክ ሲጀምሩ በማንኛውም ከተማ አይሁዶችን ያገኙ ነበር። በ300 ዓ.ዓ. አካባቢ በእስክንድሪያ ከተማ ውስጥ በጣም ብዙ አይሁዶች ይኖሩ ነበር።

# ሐጌ

## የነቢዩ ሸክም

ሕዝቡ 536 ዓ.ዓ. ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። የፋርስ ንጉሥ ዳርዮስ በ520 ዓ.ዓ. ነገሠ። በ536ና በ520 መካከል በነበሩት 16 ዓመታት ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን መልሶ መገንባት አልጀመሩም። ቤቶችን በመሥራትና ለ50 ዓመታት ታርሶ የማያውቀውን መሬት በማጽዳት ሥራ በጣም ተጠምደው ነበር። የሐጌ መልዕክት ቤተ መቅደሱን ሥሩ የሚል ነው።

በእርሻቸው ላይ ምንም በረከት የላቸውም። ቁጥቋጦውን ይመነጥሩ ነበር አርሰውም ዘርተዋል! ነገር ግን ምርታቸው በጣም ትንሽ ነበር። እግዚአብሔር አይባርካቸውም ነበር። በመካከላቸው የተደበቀ ኃጢአት ነበር። በኢያሱ ምዕ.7 ላይ የሚገኙትን ሰዎች ይመስሉ ነበር። ቤተ መቅደሱን ለመሥራት እግዚአብሔርን አንታዘዝም ብለዋል። የራሳቸውን ሥራ ከእግዚአብሔር አስቀድመዋል።

እግዚአብሔር ትዕዛዝ ብቻ አይሰጣቸውም፤ ነገር ግን እርሱን ለሚያፈቅሩትና ለሚያገለግሉት በረከትን እንደሚሰጣቸው ተስፋ ይሰጣቸዋል። ይህም የመልካም ሥራ ሽልማት ብቻ አልነበረም፣ እግዚአብሔርን ለሚያፈቅሩትም መልስ ነበር። የእግዚአብሔር በረከቶች ተስፋ ወቅታዊ ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር የወደፊቱንም ይመለከታል። እርሱ ለመሥራት እንደሚያቅድ ያውቃል። ለዘሩባቤል የተለዩ ተስፋዎች ይገባለታል። የእርሱ ስም በማቴ.1፡ 12-16 ባለው የስም ዝርዝር ውስጥ ይገኛል። እርሱ መሲሁ የተገኘበት ቤተሰብ ዘር ነው።

# ሚልክያስ

## የነብዩ ሸክም

በሚልክያስ ዘመን የነበሩት አይሁዶች እግዚአብሔር ከባቢሎን ምርኮ ስላዳናቸው የፈለጉትን ሁሉ እንኳ ቢሠሩ የሚባርካቸው ይመስላቸው ነበር። ሚልክያስ እነርሱ ማንኛውም ዓይነት ሰው ቢሆኑ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መንገድ ካልተመላለሱ ሊረዳቸው እንደማይችል ሊያሳስባቸው ያስፈልጋቸው ነበር። እግዚአብሔር የሚያደርጉትን መጥፎ ነገር ስለሚያውቅ ተቆጥቷቸዋል።

እንጠብቃለን ብለው ከእግዚአብሔር ጋር የተዋዋሉትን ቃል ኪዳን ወይም ከእነርሱም ጋር ያደረገውን ስምምነት አፍርሰው ስለ ነበር ኃጢአተኞች ነበሩ። «ቃል ኪዳን» የሚለው ቃል

በሚልክያስ ውስጥ ተደጋግሞ ይታያል። ይህንን ነገር እናውቅም ወይም ሕጉን ለመታዘዝ አልተስማማንም ሊሉ አይችሉም። ይህ ከሌሎች አሕዛብ ይልቅ ኃጢአተኛ ያደርጋቸዋል። እነርሱ ያደረጉት ኃጢአት ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ማድረግ እንዳልነበረባቸው ያውቃሉ።

ሚልክያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚቀጣበትን የወደፊት ቀን ይጠቁመናል። ምንም እንኳ ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ ተመልሰው ቢገነቡም ወደፊት እንደገና ስለ መፍረሱ የተጠቀሰ ነገር የለም። በብሉይ ኪዳን መጨረሻ አካባቢ ላይ የተገኘው ይህ ክፍል የመጥምቁ ዮሐንስንና የጌታችን የኢየሱስን መገለጥ አሻግር ይመለከታል። ስለዚህም ካልተስተካከለው ጠባያቸውና ከገቡት ቃል ኪዳን የተነሣ ከአምላካቸው ጋር ለማይቀረው ግንኙነት ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

# ሐጌ

## ማብራሪያ

በ520 ዓ.ዓ. ገደማ እግዚአብሔር ሁለት ነቢያትን ሐጌን እና ዘካርያስን አስነሥቷል። የሐጌ የተለየ ሥራ ሕዝቡ ለ16 ዓመታት ያልተመለከቱትን ቤተ መቅደስ መልሰው እንዲገነቡ ማድረግ ነበር። ባለመታዘዛቸው ምክንያት ማለትም የራሳቸውን ሥራ ከእግዚአብሔር ሥራ በማስቀደማቸው ምክንያት አልባረካቸውም፣ ሐጌ 1፡1-11 አንብቡ።

እግዚአብሔር መልዕክተኞችን በሚልክበት ጊዜ ተቀባይ ሕዝብ ያዘጋጃል። አንዳንድ ጊዜ ሁሉ አይቀበሉም ወይም ምናልባት ብዙዎቹ አይቀበሉም። በ520 ዓ.ዓ. አካባቢ ሕዝቡ ያዳምጣሉ፤ ደግሞም ለመታዘዝ ዝግጁ ነበሩ፣ 1፡12-15 አንብቡ። በጥቂት ወራት ውስጥ ቤተ መቅደሱ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያበቁት ሥራዎች የበለጠውን ክፍል አጠናቅቀዋል። በእርግጥ ሁሉንም ነገር አልሠሩም ነበር። ነገር ግን ቢያንስ ፈርሶ ከነበረው ብዙውን ገንብተዋል።

አንዳንድ ሰዎች ደስተኛ አልነበሩም። 586 ዓ.ዓ. የፈረሰውን የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ያስቡ ነበር፣ ዕዝራ 3፡12 ተመልከቱ። አሁን በተሠራው ቤተ መቅደስ አልተደሰቱም፤ ሆኖም የፈረሰውን መልሶ እንደሚያድስላቸው እግዚአብሔር ተስፋ ገብቶላቸዋል፣2፡1-5፤ 2፡6-9 አንብቡ።

በምዕ.2፡10-14 የሚገርኩ ተከታታይ ጥያቄዎችና መልሶች እናገኛለን። ቅዱስ የሆነው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር በመለየት ቅዱስ ሆኗል። ነገር ግን አንድ ቅዱስ ነገር ሌላ ነገር በሚነካበት ጊዜ ያ ነገር የተቀደሰ አይሆንም። አንድ ርኩስ ነገር ደግሞ ንጹሕ የሆነውን ሌላ ነገር በሚነካበት ጊዜ ያ ነገር ይረከሳል። የዚህ ምሳሌ ትርጉም በ2፡14 ላይ ተሰጥቷል።

አልታዘዘም ሲሉ እግዚአብሔር ቀጥቷቸዋል፣ 1፡4-7። አሁን ታዛዦች ስለሆኑ እግዚአብሔር ይባርካቸዋል፣ 2፡15-19። የእግዚአብሔርን ትዕዛዞች መታዘዝ ዘወትር በረከት ያስገኛል።

እግዚአብሔር ዘወትር ለመሪዎች የተለዩ ዕቅዶች አሉት፣ 2:20-23 አንብቡ። የዚህ ሕዝብ መሪ መሆን ለዘሩባቤል ከባድ እንደነበር እናውቃለን። እግዚአብሔር የተለየ ተስፋ የሰጠው ለዚህ ነው።

# ሚልክያስ

## ማብራሪያ

በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ለተመረጠው ሕዝብ ለእስራኤል የተለየ ሥፍራ ነበረው። ደግሞም አሁንም አለው፣ 1:1-5 አንብቡ። ለያዕቆብና ለኤሳው የተጠቀሱትን ምቹ ሁኔታዎች በምናወዳድርበት ጊዜ ይህ ሥፍራ ግልፅ ይሆናል። እግዚአብሔር ከተለየው ሕዝብ መካከል ሌላ የተመረጠ ቡድን ማለት ካህናትን እንዲያገለግሉት መርጧል፣ 1:6-14 አንብቡ። ሆኖም ሚልክያስ ባገለገለበት ዘመን ካህናት ለእግዚአብሔር ታማኞች አልነበሩም።

እግዚአብሔርን በማገልገል ፈንታ ራሳቸውን ማገልገል መርጠዋል። በቃል ኪዳኑ ውስጥ ያለውን ስምምነት አልጠበቁም፣ 2:1-9 አንብቡ። ካህናቱ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ ፈንታ አራቁት።

ካህናት ብቻ ሳይሆኑ ሰዎች ጭምር ታማኝ አልነበሩም። እግዚአብሔር ቃሉን ሰጥቷቸው ነበር፣ ነገር ግን ቢያነቡትም እንኳ በተግባር ላይ አያውሉትም ነበር፣ 2:10-16 አንብቡ። በአፋቸው አንድ ነገር ይናገራሉ! የሚያደርጉት ግን የተለየ ነገር ነው።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ተስፋዎችን አዝሏል። በተጨማሪም ፍርዶችን ይዟል። ሕዝቡ ሥርዓትን በማክበራቸው ስለተመኩ ለእግዚአብሔር መልስ መስጠት እንደሚገባቸው የዘነጉ ይመስላል። እግዚአብሔር ራሱ ሊጠይቃቸው እንደሚገለፅ ሚልክያስ ያሳስባቸዋል፣ 2:17-3:5 አንብቡ።

ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለራሳቸው ይወስዱ ነበር፣ 3:6-12 አንብቡ። ከዚህ የተነሣ ለሥራቸው የእግዚአብሔርን በረከት አይቀበሉም ነበር። ንሥሐ እንዲገቡና ለእግዚአብሔር የሚገባውን እንዲሰጡ ነቢዩ ያሳስባቸዋል። ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርና እርሱን ለማገልገል ያላቸውን ፍላጎት አጥተዋል፣ 3:13-18 አንብቡ። ሆኖም እግዚአብሔር ይህ ሕዝብ ወደ እርሱ እንዲመለስ ይጠራው ነበር። ምንም እንኳ ልባቸው ቢጠጥርም አሁንም ጌታ ምሕረቱን ያሰፋላቸው ነበር።

አንድ ቀን ፍርድ ከተፍ ይላል፣ 4:1-6። ይህ ትንቢት በከፊል በመጥምቁ ዮሐንስ እንደተፈፀመ ከአዲስ ኪዳን ተረድተናል። በተጨማሪም ከዚህ ባሻገር የመጨረሻውን የፍርድ ቀን ያመለክታል። ይህ ቀን ጌታን ለሚወዱትና ለሚያገለግሉት የበረከትና የሽልማት ቀን ይሆናል፣ 4:2-3።

# ሐጌ

## የተለዩ ነጥቦች

ቤተ መቅደሱ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የተለየ ሥፍራ አለው። እውነተኛውን አምላክ የማያውቁት ሰዎች እስከዛሬ ድረስ በኮረብቶችና በተራሮች መስዋዕት ያቀርባሉ። ይህንን ነገር ለመከላከል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ልዩ ማምለኪያ ሥፍራ ለምሳሌ እንደ ምስክር ድንኳንና ቤተ መቅደስ የመሳሰሉትን ሰጥቷቸዋል። ቤተ መቅደሱ በ586 ዓ.ዓ. ፈርሶ ስለነበር ሕዝቡ መልሰው እንዲገነቡት አዟቸዋል። በአግባብ ቢጠቀሙበት በጣም ጠቃሚ ነበር።

ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን መልሰው ለመገንባት እንዲችሉ የሚያነቃቃቸው ነቢይ ያስፈልጋቸው ነበር። በዚያ ወቅት እግዚአብሔር ሁለት ነቢያት ሐጌንና ዘካሪያስን ልኮላቸዋል። ሐጌ እግዚአብሔር አዟቸው የነበረውን ሥራ እንዲያጠናቅቁ አበረታትቷቸዋል። በተጨማሪ ስለ ወደፊት ተስፋዎች ነግሯቸዋል። በሐጌ ዘመን እግዚአብሔር ሰዎችን ጠርቶ እንደተጠቀመባቸው ዛሬም ይጠቀማል።

ሐጌ ቤተ መቅደስ ተሳላሚዎች ለምን የእግዚአብሔርን በረከት እንደማይቀበሉ አሳስቧቸዋል። በተጨማሪ ሕዝቡ ወዲያው ተነሥተው መገንባት እንዲጀምሩ አበረታትቷቸዋል። እነርሱም አዳመጡት፥ ታዘዙትም። ምንም እንኳ የከተማይቱን ግንብ እንደገና ገንብተው ባይጨርሱም የቤተ መቅደሱን ግንብ አጠናቅቀዋል። ሐጌ አሁንም እግዚአብሔር ለእነርሱ ምን ማድረግ እንደፈለገ ነገራቸው። አዲሱ ቤተ መቅደስ ከበፊቱ ይልቅ ያማረ መሆን ይኖርበታል፥ 2፡1-9፤ ሥራቸው ይባረካል፥ 2፡15-19፤ መሲሁ ከዘሩባቤል ዘር ይወጣል፥ 2፡20-23።

# ሚልክያስ

## የተለዩ ነጥቦች

ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማገልገል ተሰላችተው ነበር። ደስተኞች ሆነው አይሠሩም ወይም ፈቃደኝነት አልነበራቸውም። ነገር ግን እግዚአብሔር ያቀደላቸውን አሳብ አልለወጠም ነበር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ማን እንደሆነና ምን ማድረግ እንደሚፈልግ የሚነግሩን ስንት ማስረጃዎች ታገኛላችሁ? እግዚአብሔርን በዓይናችን አይተነው አናውቅም። ይሁን እንጂ ሲናገር ሰምተነዋል፥ ሲያደርግም አይተነዋል። እርሱ ማን እንደሆነ ራሱ ስለነገረን እናውቀዋለን። ሚልክያስ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮች ያስተምረናል።

እግዚአብሔርን ለማገልገል ስለሚጠቀሙባቸው ሐጌ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን መልሰው እንዲገነቡ አበረታታቸው። የአምላኪው ልብ ንፁህ ካልሆነ ሥርዓቶች ሁሉ ምንም የማይጠቅሙ ሽፋኖች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። በሚልክያስ ዘመን ሆኖ የነበረውም ሁኔታ ይህንን ይመስላል። ሕዝቡ ይጾሙና መሥዋዕትም ይሠዉ ነበር። ነገር ግን የሥርዓታቸው ጥንስስ የእግዚአብሔር ፍቅር ባለመሆኑ ድርጊታቸው በሙሉ ከንቱ ልፋት ነበረ።

ራሳቸውን የሚወዱ ሰዎች የወደፊቱን በፍፁም አያስቡም! እነዚህ ሰዎች ለራሳቸው ብቻ ማከበት ይፈልጋሉ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ወደፊት ስለሚፈፀሙ ነገሮች የሚጠቁሙን ስንት ጥቅሶች እናገኛለን? መልካም ሰዎች ማለት እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንዲመራላቸው የፈቀዱለትና ራሳቸውን የሚወዱ ሰዎች ከመኖራቸው የተነሣ የወደፊቱ ሁኔታ ፍርድንና በረከትን ያቀፋል። እግዚአብሔር ሲጠይቃቸው መልስ ለመስጠት ዝግጁ እንዲሆኑ ነቢዩ ሚልክያስ ሕዝቡን ያሳስብ ነበር።

# ሐጌ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

አሁን በኢየሩሳሌም ምንም ቤተ መቅደስ የለም። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የአማኝ አካልና በአንድነት የሚሠራ የአማኞች ኅብረት ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን በገለፀበት መንገድ ዛሬም ራሱን ይገልጻል። የእግዚአብሔርን ሰዎች የሚያረካቸው ወንጌልን መስማት ብቻ ሳይሆን በአማኞች ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን ኃይል መመልከት ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ህልውና ያረጋግጥላቸዋል።

እግዚአብሔር ሐጌን ለተለየ ተግባር በጠራበት ተመሳሳይ መንገድ ዛሬም ሰዎችን ለልዩ ሥራ ይጠራቸዋል። እነርሱም ከርሱ የተቀበሉትን አደራ ማከናወን አለባቸው። እግዚአብሔር አስቀድሞ አዳምን በስሙ ጠርቶታል። እንዲሁም በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ዮሐንስን በስሙ ጠራው። እግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ ያዘጋጀልን ሥራ ይኖረው ይሆን? በሚጠራን ጊዜ እንደ ሳሙኤል እና ኢሳይያስ እንመልስለታለን? ወይስ እንደ አዳምና ዮናስ ለመደበቅ እንሞክራለን?

አዲስ ኪዳን በተስፋዎች የተሞላ ነው። እነዚህ በሙሉ ለአማኞች ተሰጥተዋል። በጣም ጥቂት ሰዎች የሚወርሱት ለምንድነው? የእግዚአብሔር መንገድ አልተለወጠም። የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ለማግኘት ቃሉን መስማት ይኖርብናል። እውነት ነው ብለን መቀበል አለብን። ለኛ የተሰጡ ናቸው ብለን ከተረከብናቸው በኋላ አድርጉ የሚለንን ማድረግ ይኖርብናል! በኢየሩሳሌም የነበሩት ሰዎች ለ16 ዓመታት ምንም በረከት አልተቀበሉም፤ ምክንያቱም ምን ማድረግ እንዳለባቸው አውቀው ምንም አላደረጉም።

# ሚልክያስ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

እግዚአብሔር በፍጹም ሊለወጥ አይችልም። በብሉይ ኪዳን ባለንበትም ዘመን ለአማኞች ጠቃሚ የሆነበት ምክንያት ይህ ነው። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ይነግረናል። የእግዚአብሔር ቤተሰቦች እርሱ ያደረገላቸውንና የሚያደርግላቸውን ማሰላሰል ትተው እነርሱ ያደረጉለትን በሚያስቡበት ወቅት እርሱን ከማፍቀር ይልቅ ራሳቸውን መውደድ ይጀምራሉ።

ጳውሎስ በዕብ.1፡1-2 ላይ ምን ይላል? በተጨማሪ 1 ዮሐ.1፡1-3 ተመልከቱ። እግዚአብሔር በንግግር ብቻ አላቆመም፤ ነገር ግን ራሱን ለእኛ ለመግለፅ ሰው ሆኗል።

እግዚአብሔርን እንድናመሰግንና እንድናገለግል የሚያደርገን ማንኛውም ሥራ ጠቃሚ ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ለተከታዮቹ ሁለት ዋና ዋና መታሰቢያዎች ማለት ጥምቀትን እና የጌታን ራት ሰጥቷቸዋል። እነዚህም የክርስቶስን ሞትና ለአማኞች የሚሰጠውን አዲስ ሕይወት እንድናስተውል ይረዱናል። እነዚህን ሥርዓቶች የምንፈጽማቸው እግዚአብሔርን ለማስደሰት ብለን ከሆነ ለእኛ ያላቸውን ትርጉም ያጣሉ። እኛን ከመርዳት ይልቅ አይናችንን ከእግዚአብሔር አንሥተን ወደ ሌላ እንድንመለከት ያደርጋሉ።

ኢየሱስ በማቴ.24፤ በማር.13ና በሉቃስ 21 ውስጥ ስለ ወደፊቱ ሁኔታ አስተምሯል። ጳውሎስ በ1 ቆር. 15 እና በ1 ተሰ.4-5 ተመሳሳይ ትምህርት አቅርቧል።

የዮሐንስ ራዕይ ደግሞ ስለ ወደፊቱ ሁኔታ በሰፊው ይነግረናል። የወደፊቱን ሁኔታ እየተመለከትን ካልኖርንና ይህንንም ነገር በአዕምሮአችን አስቀምጠን ካላገለገልን አቅጣጫችንን እንስታለን። እግዚአብሔር በሰጠን ስጦታዎች ምን እንደሠራንባቸው አንድ ቀን ለሚጠይቀን ጥያቄ መልስ መስጠት እንዳለብን ዘንግተናል። በዚያን ጊዜ እርሱ የሚቀበላቸው ልጁን አምነው የተቀበሉትን ብቻ ነው፣ እንደየአገልግሎታቸው የሚገባቸውን ይሰጣቸዋል።

# የክለሳ ጥያቄዎች

1. ፈርኦን ኒካኡ አሶርን መርዳት የፈለገው ለምንድነው?
2. ኢሳይያስ የተነበየው ስለ ማን ነበር?
3. በ536 ዓ.ዓ. የአይሁድ መሪ የነበረው ማን ነበር?
4. ኤር.25፡11፤ 29፡10 የሚናገረው ስለ ምንድነው?
5. ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰው መቼ ነበር?
6. ዕዝራ 1-6 የሚናገረው ስለ የትኛው ዘመን ነው?
7. በ444 የተመለሱት ሰዎች መሪ ማን ነበር?
8. ከተበታተኑት አይሁዶች ብዙዎቹ የተጓዙት ወደ የትኛው ከተማ ነው?
9. በ520 ዓ.ዓ. የፋርስ ንጉሥ ማን ነበር?
10. በ520 ዓ.ዓ. ይናገሩ የነበሩት ሁለት ነቢያት ማንና ማን ናቸው?
11. ከ536-520 ዓ.ዓ. ምን ያህል የግንባታ ሥራ ተካሄደ?
12. ሐጌ ሕዝቡን ያበረታታቸው የነበረው ምን እንዲሠሩ ነበር?
13. ሐጌ በ2፡20-23 የሚናገረው ማንን ነው?
14. እግዚአብሔር ከኤሳው ይልቅ ማንን መረጠ?
15. ሕዝቡ መታዘዝ የሚገባው ለምንድነው?
16. ለእግዚአብሔር የሚገባውን ሳያስረክቡ ለራሳቸው የወሰዱት ምንድነው?
17. 4፡1-6 የሚናገረው ስለ ምንድነው?
18. ባቢሎን ቤተ መቅደሱን ያፈረሰችው መቼ ነበር?
19. እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሰለቹት በማን ዘመን ነበር?

20. ዛሬ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምንድነው?
21. ተስፋን ለመጎናጸፍ አስፈላጊው ነገር ምንድነው?
22. ስለ ወደፊቱ ሁኔታ የሚናገሩ ሶስት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
23. በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉን ሁለት ሥርዓቶች የትኞቹ ናቸው?
24. ብሉይ ኪዳን ጠቃሚ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
25. በሐጌና በሚልክያስ መካከል ምን ያህል የዘመን ርቀት አለ?

# ክፍል አራት

## መግቢያ

በክፍል አንድ ውስጥ ለእስራኤል የተናገሩት ሶስት ነቢያት አሞፅ፣ ሆሴዕ እና ኢዮኤልን ተመልክተናል። የእስራኤል ዋና ከተማ ሰማርያ በ722 ዓ.ዓ. በአሶራውያን እንደተያዘች እናውቃለን። ስለዚህ እነዚህ ነቢያት የተናገሩት ከዚህ ጊዜ በፊት ነበር። በተጨማሪ ደግሞ የታወቁት ሁለት ነቢያት ኤልያስና ኤልሳዕ ከዚህ ጊዜ በፊት በእስራኤል ተናግረዋል። አሞፅ፣ ሆሴዕና ኢዮኤል ትምህርታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ ያሰፈሩ ናቸው። ሆኖም እግዚአብሔር እስራኤልን ለመናገር ሌሎች ነቢያትን ደግሞ እንደተጠቀመባቸው ማስታወስ ይኖርብናል። ኢሳይያስና ሚክያስም ለእስራኤል የሚናገሩት ነገር አላቸው።

በክፍል ሁለት ለይሁዳ የተናገሩትን ነቢያት አጥንተናል። ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው ሚክያስ ሲሆን እርሱም በኢዮአታም፣ በአካዝ እና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ተናግሯል። ከ70 ዓመታት ያህል በኋላ ሶፎንያስ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ለይሁዳ ሰብኳል። ዕንባቆም ልክ ኢየሩሳሌም ከመፍረሰዋ በፊት ምናልባት በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት ተናግሯል። እግዚአብሔር ይሁዳን ለመናገር ሌሎች ነቢያትን ደግሞ ተጠቅሟል። በሚክያስ ዘመን ኢሳይያስ ሰብኳል። ሶፎንያስና ኤርምያስ ጓደኞሞች ነበሩ። ዕንባቆም ሕዝቡን በኢየሩሳሌም በሚያስተምርበት ወቅት ሕዝቅኤል በባቢሎን ነበር።

ክፍል ሶስት የሚናገረው እግዚአብሔር ከምርኮ በኋላ ስለተጠቀመባቸው ሶስት ነቢያት ነው። ከእነዚህ ሶስት መጻሕፍት ጋር ዕዝራን፣ ነህምያንና አስቴርን ማንበብ ያስፈልገናል። ሐጌና ዘካርያስ የተናገሩት በተመሳሳይ ዘመን ነው። ሚልክያስ የተናገረው ምናልባት ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሳይሆን አይቀርም። የዘካርያስ ጥቂት ክፍሎች ለምሳሌ ከምዕ.9-14 ያሉት እስከዚያ ጊዜ ድረስ በፋርስ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነገር ይኖረው ይሆናል።

በክፍል አራት እግዚአብሔር አሕዛብን ለመናገር የተጠቀመባቸውን ሶስት የአይሁድ ነቢያት እናጠናለን። እነዚህ ሶስቱ በአንድ ላይ የቀረቡበት ምክንያት ይህ ነው። የተናገሩባቸው ዘመናት በጣም የተራራቁ ናቸው፤ ነገር ግን አንዱ ለኤዶም ሲናገር ሁለቱ ደግሞ ለአሶር ተናግረዋል። ሙሴ ለግብፅ መስካሪ እንደነበረ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ደግሞ በባቢሎን በመኖራቸውና በመስበካቸው እነርሱም ለባቢሎን እንደመስካሪ ሳይቆጠሩ አልቀሩም።

እግዚአብሔር አንድ የተለየ ሕዝብ ማለት አይሁድን የመረጠው ለምንድነው? ለእነርሱ ጥቅም ሳይሆን እነርሱን በመጠቀም ለተቀሩት የዓለም ክፍሎች መልዕክቱን ለማድረስ ነበር። «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» የሚለው ትእዛዝ በአዲስ ኪዳን ብቻ የሚገኝ አይደለም።

ረጃጅም መጻሕፍት የጻፉት ሶስቱ ነቢያት የእስራኤል እና የይሁዳ ጎረቤቶች ስለነበሩት ባዕድ መንግሥታት አጫጭር ክፍል በጽሑፋቸው ውስጥ አክለዋል። በዚህ አጋጣሚ እነዚህን

ምዕራፎች ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው፥ ኢሳ.13-23፤ ኤር. 46-50ና ሕዝቅኤል 25-32። እያንዳንዳቸው ስለ እነዚህ ሕዝቦች የሚናገሩትን አወዳድሩ። ከእስራኤል እና ከይሁዳ ጋር ቃል ኪዳን የገባው እግዚአብሔር የእነርሱ አምላክ ብቻ ሳይሆን የሁሉም አምላክ ነው። አሕዛብ የራሳቸው የሆኑ ጣኦታት ነበሩአቸው፥ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ፈርዶባቸዋል፤ ደግሞም በታትኗቸዋል።

# ትምህርት አሥር

## አብድዩ ዮናስና ናሆም

## አብድዩ

### ታሪካዊ አቀማመጥ

በመጽሐፉ ውስጥ አብድዩ መቼ እንደሰበከ የሚጠቁም እርግጠኛ ሐሳብ አናገኝም። ይሁን እንጂ ሁለት ነጥቦች ግልጽ ናቸው:-

1. አብድዩ የኤሳው ትውልድ ስለሆነው ስለ ኤዶም ሰብኳል። ከ586 ዓ.ዓ. በፊት እነዚህ ሰዎች አልፎ አልፎ ይሁዳን ቢወጉዋትም በአይሁዶች ላይ ያደረሱት ጥቃት በ586 ዓ.ዓ. እንዳደረሱት ዓይነት አልነበረም።
2. በዚህ ጊዜ ኤዶም የኢየሩሳሌምን አይሁድ ለመደምሰስና ለማጥፋት ከሌላ ኃይል ጋር ተባብራለች።

እነዚህ ሁለት ነጥቦች አብድዩ የሰበከው ባቢሎን ከኢየሩሳሌም በስተቀር የይሁዳን ከተሞች በሙሉ አሸንፋ በነበረበት ወቅት በ586 ዓ.ዓ. ገደማ ነው ለማለት የሚያስችሉን መረጃዎች ናቸው። ግብጻውያን በባቢሎን ተሸንፈው ነበር። ስለዚህ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ እና ምሥራቅ በሚገኘው በረሃ ይኖሩ የነበሩት ኤዶማውያን ኢየሩሳሌምን ለመዝረፍ ከባቢሎናውያን ጋር ተባብረው ነበር። ኢየሩሳሌምን የቀጣት በእርግጥም እግዚአብሔር ነበር፤ ነገር ግን ኤዶም ጥፋተኛ ነበረች።

## ዮናስ

### ታሪካዊ አቀማመጥ

ጋትሔፌር በመባል የምትጠራው ዮናስ ይኖርባት የነበረችው ከተማ ከገሊላ ባሕር በስተ ምዕራብ 4 ሰዓቶች የምታስኬድ ስትሆን በጥምት በገሊላ ባሕርና በቀርሜሎስ ተራራ መካከል ጥግሽ መንገድ ላይ ነበረች።

የእስራኤል 14ኛ ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ከ783-743 ዓ.ዓ. ለ40 ዓመታት በሰማርያ ነግሷል። እርሱ ምንም ጠማማ ንጉሥ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ነቢዩ ዮናስን በመላክ አሶር የወሰደችውን በሰሜን የሚገኘውን ምድር በሙሉና ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በስተ ምሥራቅ ያሉትንም መንደሮች ከአሶራውያን ነጥቆ ወደ ግዛቱ ሥር ሊመልሳቸው እንደሚችል ተስፋ ሰጥቶታል፥ 2ኛ ነገ. 14፡23-29።

በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት ከ783-743 ዓ.ዓ. በትክክል ባልታወቀ ጊዜ እግዚአብሔር ዮናስን ወደ አሶር ዋና ከተማ ወደ ነነዌ ልኮታል። ይህ ድርጊት የተፈጸመው የአሶራውያን ግዛት በባቢሎን ሳይደመሰስ ከ150 ዓመታት በፊት መሆን አለበት። የነቢይ ዮናስ ስም በ2ኛ ነገ.14፡25ና በወንጌሎች ውስጥ ተጠቅሷል።

# ናሆም

## ታሪካዊ አቀማመጥ

ናሆም ለአሶራውያን ከተማ ለነነዌ የተናገረ መሆኑ ከመጽሐፉ ይዘት ግልፅ ሆኖ ይታያል። ነገር ግን ናሆም መቼ እንደተናገረ የሚጠቅስ ነገር በመጽሐፉ ውስጥ የለም። ሆኖም መቼ እንደተነበየ የሚነግሩን ሐሳቦች ከመጽሐፉ ይዘት ማግኘት እንችላለን።

መልእክቱ ስለ ፍርድ ብቻ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ የተስፋ ቃል ወይም በረከት በፍጹም አይገኝም። ዮናስ በነነዌ ከተማ ከሰበኩ 150 ዓመታት ማለፋቸውን አትርሱ። ከዮናስ ዘመን 20 ዓመታት በኋላ የትውልድ አገሩ በአሶራውያን ትሸነፋለች፤ በተለይ ኢሳ. 9፡1 ተመልከቱ። የናሆም መልእክት የአሶራውያን የመጨረሻው ጊዜ እንደተቃረበ ያመለክተናል።

ነነዌ በ612 ዓ.ዓ. በባቢሎናውያን እንደተደመሰሰች እናውቃለን። ናሆም የተናገረው ከዚህ ጊዜ በፊት መሆን አለበት፤ በናሆም 3፡20 የተጠቀመው ፍርድ በ663 ዓ.ዓ. የተፈጸመ መሆኑን የዓለም ታሪክ ያረጋግጥልናል። ስለዚህ ናሆም ትንቢት የተነበየው በ663ና በ612 ዓ.ዓ. መካከል ነው።

# አብድዩ

## የነቢዩ ሸክም

አብድዩ የሚናገራቸው ሁለት አበይት ነገሮች አሉ፡- አንዱ ለኤዶማውያን ሲሆን ሌላው ለኢየሩሳሌም ሰዎች ነው።

1. ኤሳውና ያዕቆብ ወንድማማች ነበሩ። ስለዚህ ኤዶማውያን ከአይሁዶች ጋር ዘመዶች ነበሩ። ከዚህ የተነሣ ኤዶማውያን ኢየሩሳሌምን መዝረፋቸው ከባድ ወንጀል ነበር። ከባቢሎናውያን ጋር ሲወዳደሩ ኤዶማውያን በቁጥር በጣም ያነሱ ነበሩ፥ ስለዚህ ኢየሩሳሌምን ለመከላከል አልቻሉም። ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱ ዘመዶቻቸውን በመዝረፋቸው ኃጢአተኞች ነበሩ።

2. እግዚአብሔር ምንም እንኳ ከሕዝቦችዋ ኃጢአት የተነሣ የኢየሩሳሌምን መፍረስ ቢፈቅድም ያፈረሱዋትን ደግሞ ይቀጣቸዋል። እግዚአብሔር ከፋታቸውን ለእርሱ ዓላማ ተጠቀመበት እንጂ የእነርሱን ጠባይ ደገፈታል ማለት አይደለም። አይሁድን ጨርሶ ትቷቸዋል ማለትም አይደለም። በምድያም ምድረ በዳ ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች ከደቡብ ወደ ሰሜን ሲዘምቱ ኤዶማውያንን ወደ ይሁዳ የገፉአቸው ሲሆን በመጨረሻም ኤዶማውያን ከአይሁዶች በመቀላቀል ሕልውናቸውን አጥተዋል። የነቢይ አብድዩ ትንቢት ታሪካዊ ፍጻሜውን ያገኘው በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር።

# ዮናስ

## የነቢዩ ሸክም

የዮናስ መጽሐፍ ከሚያስተምረን ብዙ ትምህርቶች መካከል ሶስቱን መርጠን እንመለከታቸዋለን፦

1. መጽሐፉ እግዚአብሔር አንድ ግለሰብን መርጦ ሊጠቀምበት እንደሚችል ያሳየናል፥ 2ኛ ነገ.14፡23-29 ደግማችሁ አንብቡ። ዮናስ የኖረው የእስራኤል መንግሥት ሰፊና ባለጠጋ በሆነበት ዘመን ነበር። በብዙ አቅጣጫዎች የእርሱ ጠባይ መጥፎ ነበር፥ ነገር ግን እግዚአብሔር አልተወውም። እንዲያውም ፍቅሩንና ትዕግሥቱን አሳየው።
2. ዮናስ አይሁድን የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው። እነርሱ ጎረቤቶቻቸውን ይዘልፉና ይጠሉ ነበር። በእውነት አሶራውያን ጨካኞችና ርሕራሔ የሌላቸው ሰዎች ነበሩ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የዮናስን የትውልድ አገር ገሊላን ሊያጠፉአት ዘምተውባታል። የሆነ ሆኖ እግዚአብሔር ገሊላዊ ነቢይ በመላክ ለእነርሱ ያለውን ፍቅርና ቸርነት ያሳያቸዋል።
3. የነነዌ ሕዝብ ንሥሐ ለአይሁድ ተግሳፅ ነበር። እግዚአብሔር ፍቅሩን ለእስራኤል ሲያሳይ ሕዝቡ ለነቢያት መልስ አልሰጠም ነበር፥ ሆሴዕ 1፡1 አንብቡ። ሆሴዕ እስራኤላውያን ንስሐ እንዲገቡ ይማፀናቸው የነበረው በዚህ ዘመን ነበር። ነነዌ ንስሐ ስትገባ ሰማርያ ግን አልገባችም።

# ናሆም

## የነቢዩ ሸክም

2ኛ ነገ.23፡29 አሳዛኝ ታሪክ ይነግረናል። አሶራውያን ከዕለት ወደ ዕለት እየደከሙ ሲመጡ ባቢሎናውያን እየበረቱ መጡ። የግብፅ ንጉሥ ወይም ፈርኦን ኒካኡ አሶር መድከምዋን ስለተረዳና እርሱም በመጨረሻ ላይ ሊያሸንፋት እንደሚችል ስላወቀ እንዲሁም ደግሞ የባቢሎን እድገት ስላሳሰበው ከአሶር ጋር ተባብሮ ባቢሎንን ለመቅጨት ዘምቶ ነበር። ለንጉሥ ኢዮስያስ የባቢሎን አደገኛነት አልተከሰተለትም፤ ነገር ግን አሶርን ይጠላት ስለነበር ባቢሎን እንድትደመስሳት በጉጉት ይጠባበቅ ነበር። የግብፅን ንጉሥ ኒካኡን ማገድ የፈለገው ለዚህ ነበር። ይኸውም በ609 ዓ.ዓ. ነበር። ናሆም ሶስት ጥያቄዎችን ይመልስልናል።

1. ነነዌን በ612 ማን ደመሰሳት? ባቢሎን ሳትሆን እግዚአብሔር ነው።
2. ነነዌ ለምን ተደመሰሰች? ኃጢአት የታየበት ቦታ ሁሉ ስለሚፈረድበት ነው። ባቢሎን ብርታት ያገኘችው ከየት ነው? ከጣኦቶችዋ ሳይሆን በዚያ ወቅት ባቢሎንን ተጠቅሞ በነነዌ ላይ ያወጣውን ዕቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ይፈልግ ከነበረው ከእስራኤል አምላክ ነበር።

# አብድዩ

## ማብራሪያ

መጽሐፉ አጭር ቢሆንም እንኳ በውስጡ አራት ትምህርቶች እናገኛለን። እያንዳንዳቸውን በአጭሩ እንመልከት።

የኤዶም ዋና ከተማ ፔትራ የተገነባችው ከጨው ባሕር በስተደቡብና ምሥራቅ በሚገኙት አለቶች ላይ ነበር። በ2 ሳሙ. 5 ላይ እንደተጠቀሰው እንደ ኢያቡሳውያን ከተማ የማትደፈር ናት ብለው ያስቡ ነበር፥ ቁ.1-9።

እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ለመፍረድ በባቢሎናውያን እንጂ በኤዶማውያን ለመጠቀም ባለማቀዱ ኤዶማውያን እጥፍ ድርብ ኃጢአት ሠርተዋል፥ ቁ.10-14። ምንም እንኳ እነርሱ ከተመረጡት ዘር ባይሆኑና እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ባይገባም እንደሚፈርድባቸው ተናግሯል። ቢያውቁትም ባያውቁትም አምላካቸው ነው። ይህ ትንቢት ተፈጽሟል። አሁን ኤዶም ተብሎ የሚጠራ ሕዝብ በጭራሽ የለም።

እግዚአብሔር ራሱን ለዓለም አሳውቋል። ነገር ግን ለዚህ መለኮታዊ መገለጥ ያሳዩት አለመታዘዝ ጠቅላላው ሕዝብ የራሳቸውን ጣኦታት እንዲያበጁ አድርጓቸዋል፥ ሮሜ 1። ሆኖም እግዚአብሔር በመላው ዓለም ላይ በመፍረድ ከእነዚህ ጣኦታት በላይ ታላቅ መሆኑን ይገልጣል። በሕዝቅኤል 25-32 ላይ የተጠቀሱት የትኞቹ ሕዝቦች ናቸው? ስንቶቻቸውስ ፍርዳቸውን ተቀብለው ከነጭራሹ ጠፍተዋል?

ንጉሥ ሄሮድስ ኤዶማዊ ነበር። ኤዶማውያን ወደ ሰሜን ተገፍተው ጨርሰው እስከጠፉበት ጊዜ ድረስ ቀስ በቀስ ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ተደባልቀው ነበር። በቁ.17-21 ያለው ትንቢት ባልታሰበ መንገድ ይሁን እንጂ ተፈጽሟል።

# ዮናስ

## ማብራሪያ

ዮናስ እግዚአብሔር ለተለየ ተግባር እንደጠራው ቢያውቅም እንደ አሥሩ የእስራኤል ነገዶች አልታዘዘለትም። እንደ አዳም ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ሞክሯል። እግዚአብሔር ለማይታዘዙት ያለውን ፍቅር ከዚህ ልምምዱ መማር ነበረበት። እግዚአብሔር ዮናስን ባልታሰበ መንገድ አድኖታል። የዮናስን ታሪክ መሠረት አድርገን ሰው ምንም ቢያጠፋ

እግዚአብሔር በተአምራዊ መንገድ ከጥፋቱ ውጤት ያድነዋል እንድንል የሚያደፋፍረን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም።

ዮናስ በጭንቀቱ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ተጠግቷል። ይህ ትምህርት በከንቱ አልተሰጠም። ዮናስ ስለ እግዚአብሔር ሰፊ ትምህርት እንደተማረ ምዕ.2 ያሳየናል። በእርግጥ ዮናስ በባሕር ውስጥ በነበረበት ወቅት ይህንን መዝሙር አልጻፈውም። እግዚአብሔር የዮናስን ጸሎት መልሶለታል፤ ነገር ግን የነነዌ ሰዎች ንሥሐ ገብተው በጸለዩበት ወቅት እግዚአብሔር ሰምቶ ስለመለሰላቸው ተቆጥቶ ነበር።

በምዕ.3 ዮናስ ተመልሶ ወደ ነነዌ የመጓዝን ታሪክ እናገኛለን። እግዚአብሔር ዮናስን እንዲረዳው አሳን አዘጋጅቶ እንደነበረ እንዲሁ የነነዌን ከተማ ለመልእክቱ አዘጋጅቷታል። በምዕ. 3፡4 ላይ እንደምንመለከተው ፍርዱ የማይሻር መስሎ ቢታይም በእርግጥ እውነቱ አልነበረም። ሕዝቡ ንሥሐ ገባ፤ ከዚያም እግዚአብሔር ምሕረቱን አሳያቸው።

ምዕ.4 የተጨመረው ለምንድነው? የእግዚአብሔር መልእክተኛ ራሱ በጌታ ተአምራዊ ሥራ ሳይለወጥ? መቅረቱን ለማሳየት ነው። በኢየሱስ ምሳሌ ውስጥ የምናገኘውን ይቅርታ የማያደርገውን ባለ ዕዳ ይመስል ነበር። ምንም እንኳ ዮናስ ልቡ ጠማር ቢሆንም እግዚአብሔር እስከዚህ ጊዜ ድረስ ለእርሱ ሩህሩህና ቸር ነበር።

# ናሆም

## ማብራሪያ

ናሆምና ሶፎንያስ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መካከል እጅግም የተወደዱ አይደሉም። በየመጽሐፉ ውስጥ 3 ምዕራፎች አሉ፤ ነገር ግን ሁለት ዋና ዋና ሐሳቦች ብቻ አሉት።

ምዕ.1፡2-14 በአሶር ዋና ከተማ በነነዌ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ያሳያል። ሰማርያ በ722 ዓ.ዓ. ከወደቀች ከ150 ዓመት በፊት ከዘንበሪ ዘመን ማለት ከ885-874 ዓ.ዓ. አሶር ዕለት በዕለት ብርቱ መንግሥት እየሆነች በመምጣት ላይ ነበረች። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለመቅጣት አሶራውያንን እንደተጠቀመባቸው እርግጠኛ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር እንደ ሕዝቡ ተቀብሏቸዋል? እግዚአብሔር በልባቸው ያኖረውን ሕግ ለሰጣሱ አሶራውያንን ሊቀጣቸው ነው። በትንቢተ ናሆም የእግዚአብሔር ቁጣ በሥዕላዊ አገላለፅ ቀርቧል።

እግዚአብሔር እንዲያደርግ የወሰነውን አጠናቅቋል። እግዚአብሔር ነነዌን በዮናስ ዘመን እንደሚፈርድባት ተናግሮ ነበር፤ ነገር ግን አልፈረደባትም። ምክንያቱም ሕዝቡ ንሥሐ ገብቷል። ፍርድ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ የማምለጥ ዕድል አለ። ናሆም ከተማይቱ ገና ድሮ እንደተደመሰሰች አድርጎ ያቀርባታል፣ ነገር ግን አልተደመሰሰችም ነበር። ነነዌ በባቢሎን ጦር ተሸንፋ የተደመሰሰችው በ612 ዓ.ዓ. መሆኑን ከዓለም ታሪክ እንረዳለን። ከተማይቱ በአጠቃላይ ተደምስሳ ነበር። የነበረችበትን ሥፍራ ማንም እስከማያውቀው ድረስ የምድረ በዳ ነፋስ የብዙ ሜትር አሸዋ ከምርባታል። ከቅርብ ዓመታት ሥፍራ ተፈልጎ ሲገኝ የጥንቲቱ ከተማ ንብረቶችዋና እጅግ ብዙ ጽሑፎች ተገኝተዋል።

# አብድዩ

## የተለዩ ነጥቦች

አብድዩ ለአይሁዶች እና ለኤዶማውያን ለሁለቱም ከእግዚአብሔር ማምለጥ እንደማይቻል አሳሰቧቸዋል። ኤርምያስ ለ40 ዓመታት በኢየሩሳሌም ሆኖ የባቢሎን ከተማ እንደሚፈርስ ያሳሰብ ነበር። ኤር. 52 የእርሱ ትንቢቶች ዕውነት መሆናቸውን ያረጋግጣል። አብድዩ ይህንን አጭር ትንቢት ለአይሁዶች ወይም ለኤዶማውያን ጽፎላቸዋል? እኛ አናውቅም። እግዚአብሔር ኤዶማውያንን ፈርዶባቸዋል። በተጨማሪም በመጨረሻ መንግሥታቸው ጨርሶ ጠፍቷል። ኤዶማውያን ዋና ከተማቸው ጴጥራ የማትደፈር መስሏቸው ነበር። እርሷን ያበጃት እግዚአብሔር መሆኑን ዘንግተው ነበር።

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለመቅጣት ባቢሎናውያንን መርጦ ጊዜያዊ መሣሪያ አድርጓቸዋል። ኤዶማውያን በማጥፋቱ ተግባር ላይ ተባባሪ ነበሩ። በሌሎች ኃጢአት ስለተሳተፉ ተፈርዶባቸው ነበር። የኢየሩሳሌም ሰዎች ጥፋት የኤዶማውያንን ስሕተት ቅን አያደርገውም። ወንድሞቻቸው ምንም ያህል ክፉዎች ቢሆኑም እንኳ ኤዶማውያን በጭራሽ ሊወጉአቸው አይገባም ነበር። እግዚአብሔር የእነርሱን ዕርዳታ አልፈለገም። ባቢሎናውያንም የእነርሱን ዕርዳታ አይፈልጉም ነበር።

# ዮናስ

## የተለዩ ነጥቦች

ከዘንበሪ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ አሶር እስራኤልን ትወጋት ነበር። አሁን እግዚአብሔር የአሶር ሕዝቦች ንሥሐ እንዲገቡ ለመጥራት ወደ ዋና ከተማቸው ወደ ነነዌ መልዕክተኛ ይልካል። የዮናስን አለመደሰት ምክንያት ለመገመት አያዳግትም። አሶራውያን ደግሞ ዮናስ እነርሱን በመዋጋት ፈንታ የንሥሐ መልዕክት ይዞላቸው በመምጣቱ ሳይገረሙ አልቀረም። አሶራውያን ከዚህ አደናቃፊ ፍርድ የማምለጥ ዕድል እንዲያገኙ የእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ ነበር።

መጽሐፉ በብዙ መንገዶች የእግዚአብሔርን ምሕረት ያሳየናል። ይህ የንሥሐ ጥሪ የተገለጠለት ታዛዥ ላልሆነና ደግሞም ለነነዌ ከተማ ነዋሪዎች ምንም ርህራሄ ላልነበረው ነቢይ ነበር። ሁኔታው የተገለፀው የባዕድ ከተማ ለነበረችው ለነነዌ ነበር። ሕዝቡ የተሰጠውን ምሕረት ከመቀበሉ የተነሣ ፍርዱ ለሌላ ጊዜ ተላልፎ ነበር። ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚገልጡ ሌሎች ሃሳቦች ሰብስቡ።

# ናሆም

## የተለዩ ነጥቦች

ከየትም ይምጡ ግን እግዚአብሔር ክፋትንና ኃጢአትን ይጠላል። ናሆም በአጭር ትንቢቱ ውስጥ ይህንን ሐሳብ ግልፅ አድርጎታል። ጨካኞቹ አሶራውያን ከ150 ዓመታት በላይ ከአገር ወደ አገር በመዘዋወር ዓለምን ሁሉ በመዝመት እንዲወጉ እግዚአብሔር ፈቅዶላቸው ነበር። እግዚአብሔር ክፋታቸውን ያውቃል። ስለዚህ ንሥሐ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታዎች ፈጥሮላቸዋል። ናሆም የአረመኔ ሕዝቦች ክፋት ሳይፈረድበት እንደማይቀር ያሳስበናል።

የእግዚአብሔር ውሳኔ እርግጠኛ ከመሆኑ የተነሣ ወደፊት የሚፈፀመው ነገር እንደተፈፀመ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። ናሆም የተናገረው ከ612 ዓ.ዓ. የነነዌ መፍረስ ቀደም ብሎ ነበር፤ ነገር ግን ብዙ ነገር አስቀድሞ የተፈፀመ ይመስላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእንደዚህ ዓይነት ትንቢት ብዙ ምሳሌዎች እናገኛለን። የባቢሎን ጦር አሶራውያንን ድል ሲመታ በአማልክታችን ኃይል ነው ብሎ ሳያስብ አልቀረም። ናሆም ነነዌን ያፈርሳት እግዚአብሔር እንደሆነ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ለምን እንዳደረገውና ገና ወደፊትም በነነዌ የሚያደርገውንም ነገር በሙሉ ለናሆም ነግሮት ነበር።

# አብድዩ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 5፡10 ላይ በቆሮንቶስ ለሚገኙት ክርስቲያኖች ሲጽፍ ሁላችን እንዴት መመላለስ እንደሚገባንና ለእግዚአብሔር መልስ መስጠት እንዳለብን ያሳስባቸዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስን ከአጠገባቸው ስላራቁት እንደፈለጉ መኖር የሚችሉ ይመስላቸዋል። ሴዴቅያስ በተለያዩ ወቅቶች ኤርምያስን ለመግደል ሞክሯል፤ ነገር ግን ይህ ድርጊት እግዚአብሔር ለእርሱና ለኢየሩሳሌም ያስተላለፈውን መልዕክት አልለወጠውም። አንዳንድ ክርስቲያኖች ልክ እንደ ኤዶም ቅጥራችን የማይደፈር ነው በማለት በእግዚአብሔር ላይ መተማመናቸውን ይተዋሉ።

በኤዶም ላይ ለምን ፍርድ እንደተፈረደባት አስታውሱ! በባቢሎን ኃጢአት ስለተባበረች ነው። ጳውሎስ በ1 ቆሮ.15፡33-34 ክርስቲያኖች ከዚህ እንዲጠበቁ ያሳስባቸዋል። ኃጢአት የሚጠነስሰውን እና በተጠነሰሰውም ኃጢአት የሚሳተፈው እኩል ጥፋት አልሠሩም የሚል የተሳሳተ ሐሳብ ሊኖረን ይችል ይሆናል። ኃጢአቱን የጠነሰሰው ማንም ይሁን ግን ከኃጢአቱ መገለል እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያስጠነቅቀናል። ብዙዎቹ ያደርጉታል የሚል ምክንያት እንፈጥር ይሆናል። ይህ በጌታ ዘንድ ምክንያት አይሆንም። የሰውን ብዛት ወይም የሰውን ፊት ሳንመለከት ለጌታ ቃል መታዘዝ አለብን።

# ዮናስ

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

ዮናስን ወደ ነነዌ የሰደደው እግዚአብሔር ነበር። ጳውሎስና በርናባስን ወደ ቆጵሮስና በዚያው ወደ እስያ የላካቸው እግዚአብሔር ነበር። ሌሎች ብዙ ምሳሌዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልናወጣ እንችላለን። እግዚአብሔር ቋንቋቸውና ባሕላቸው የተለየ ወደሆኑ ሰዎች ሄደው መልካሙን የምሥራች እንዲሰብኩላቸው ዛሬም ሰዎችን መጥራቱን አላቋረጠም። እያንዳንዱ ክርስቲያን ለዘመናዊቷ ነነዌ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለማድረስ የጌታችንን ትዕዛዝና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመታዘዝ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል።

ለማይታዘዘውና ውለታቢስ ለሆነው መላውን የአይሁድን ብሔር ለሚወክለው ለዮናስ የእግዚአብሔር ምሕረት ተገልጾለት ነበር። ምናልባት በኋላ ዮናስ እንደ ሆሴዕ መላውን ሕዝብ ለመገሠፅ የተጠቀመው የራሱን ሕይወት ነው። በተጨማሪም የእግዚአብሔር ምሕረት ለጨካኞችና ምሕረት ላልነበራቸው አረመኔ ሕዝቦች ተገልጦላቸው ነበር። እነርሱ ለንሥሐ ዝግጁ ነበሩ፥ እኛስ ነን?

# ናሆም

## ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

ስንሰብክና ስናስተምር በእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት ላይ ማትኮር ይኖርብናል። ሆኖም ከዚህ ጋር በማያያዝ እግዚአብሔር ማንኛውንም ዓይነት ክፋት እንደሚጠላ በግልጥ ማሳየት ያስፈልገናል። በዕብራውያን ውስጥ ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚነድ እሳት ብሎ ይጠራዋል፥ ዕብ. 12፡29። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ልክ እንደ እግዚአብሔር ክፋትን መጥላት ይኖርበታል። በ1 ቆሮ. 13 ጳውሎስ ፍቅር ምን እንደሚመስል ያሳየናል። ፍቅር መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ይወዳል። ነገር ግን መጥፎ የሆነውን ነገር ሁሉ ይጠላል። ይህንን ትምህርት ለመማር ጊዜአችንን እንስጥ!

እኛ እንደምንፈርደው እግዚአብሔር ቸኩሎ የሚፈርድ ስላልሆነ አንዳንድ ጊዜ ሁሉን ነገር የረሳ ይመስለናል። አንዳንዱ እግዚአብሔር ክፉ የሚሠሩትን ለምን ይረዳቸዋል በማለት እንደ ዕንባቆም ግራ ይገባናል። የእግዚአብሔር ፍርድ የማይቀር ነገር ነው። ክፋት እስከ መጨረሻ ድረስ አይዘልቅም። በራዕይ 18-19 ውስጥ ዮሐንስ የባቢሎንን ማለት እግዚአብሔርን የሚቃወመው ኃይል አጠቃላይ ውድቀት ይናገራል። ውድቀቷ የተረጋገጠ በመሆኑ የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን ነቢያት እንደተፈፀመ በመቁጠር ስለዚህ ነገር የሚናገሩት በኃላፊ ጊዜ ግሥ ነው።

# ጥያቄዎች

1. ለእስራኤል የተናገሩት ሶስት ነቢያት እነማን ናቸው?
2. ሰማርያን ማንና መቼ ያዛት?
3. ከዚህ ዘመን በፊት ለእስራኤል የተናገሩት ነቢያት የትኞቹ ናቸው?
4. ለእስራኤል የጻፉ ሁለት ሌሎች ነቢያት ማንና ማን ናቸው?
5. በሚኪያስ ዘመን የመሩት ሶስት ነገሥታት እነማን ነበሩ?
6. በሚክያስና በሶፎንያስ መካከል ያለው የዘመን ርቀት ምን ያህል ነው?
7. ሶፎንያስ ይናገር የነበረው በማን ዘመን ነበር?
8. ዕንባቆም የተናገረው በማን ዘመን ነበር?
9. ለይሁዳ የተናገሩት ሶስት ነቢያት የትኞቹ ናቸው?
10. የሚክያስ ጓደኛ የነበረው ነቢይ ማን ነበር?
11. ዕንባቆም በኢየሩሳሌም በነበረበት ወቅት በባቢሎን ይሰብክ የነበረው ነቢይ ማን ነበር?
12. ከምርኮ በኋላ የነበረውን ሁኔታ የሚነግሩን ሶስት መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው?
13. ከምርኮ በኋላ በአንድ ወቅት የኖሩና የሰበኩ ነቢያት ማንና ማን ናቸው?
14. ምናልባት ዘካርያስ 9-14 የተጻፈው ለእነማን ነበረ?
15. ለአሕዛብ የተናገሩ ሶስት ነቢያት እነማን ናቸው?
16. ለአሶር የተናገሩት ሁለት ነቢያትስ?
17. በባቢሎን ይመሰክሩ የነበሩት ሁለት ነቢያት ማንና ማን ናቸው?
18. እግዚአብሔር አይሁዶችን ለምን መረጠ?
19. የኢሳ.13-23፤ ኤር.46-50ና ሕዝ.25-32 አቢይ ትምህርት ምንድነው?
20. እግዚአብሔር የማን አምላክ ነው?
21. አብድዩ የጻፈው መቼ ነው?
22. ስለ አብድዩ ግልፅ የሆኑ ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?
23. የኤዶም ቅድመ አያት ማን ነበር?
24. አብድዩ የተናገረው በግምት መቼ ነበር?
25. ጌትሔፌር የምትገኘው የት ነበር?
26. ከ783-743 ዓ.ዓ. ድረስ ንጉሥ የነበረው ማን ነበር?
27. የዳግማዊ ኢዮርብዓምን ታሪክ የምናገኘው የት ነው?
28. የአሶር ታላቅ ከተማ ማን ነበረች?
29. ከዳግማዊ ኢዮርብዓም ሞት 20 ዓመታት በኋላ ሰማርያ ምን ተፈፀመባት?
30. ባቢሎን ነነዌን የደመሰሰችው መቼ ነበር?
31. አሶር ኖህ አሞንን የደመሰሰችው መቼ ነበር?
32. ምናልባት ናሆም የጻፈው በ612 ዓ.ዓ. አካባቢ ሳይሆን አይቀርም ብለን የምንገምትበት ምክንያት ምንድነው?
33. የኤዶም ወንጀል በጣም ከባድ ሆኖ የተቆጠረው በምን ምክንያት ነው?
34. ኤዶም ምን ይደርስባታል?
35. የግብፅ ንጉሥ ኒካኡ ኢዮስያስን የት ገደለው?
36. የኤዶም ዋና ከተማ ማን ነበረች?

37. ንጉሥ ሄሮድስ የየትኛው ሕዝብ መሪ ነበር?
38. እግዚአብሔር ነነዌን በሚመለከት ስለ ንሥሐ የተናገረውን ቃል ለምን ቀየረው?
39. ዘንበሪ ኢየሩሳሌምን ይመራ የነበረው መቼ ነበር?
40. ነነዌ ከፈረሰች በኋላ ምን ሆነች?

# መልሶች

# ክፍል አንድ

## ትምህርት አንድ /ሆሴ.1-7/

1. የሰበኩና በጽሑፍ ያሰፈሩ ናቸው።
2. ከ875-800 ዓ.ዓ. ነበር።
3. 1ኛ ነገ.18-2ኛ ነገ.2 ውስጥ ነው።
4. ሆሴዕ፣ አሞፅና ኢዮኤል ናቸው።
5. በ1 ነገሥት 12 ውስጥ ነው።
6. መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊውን ሁኔታ ያስገነዝበናል።
7. ሰማርያ ነበረች
8. ሰማርያ ወደቀች።
9. በ800 ዓ.ዓ. አካባቢ ነው።
10. ከ800-722 ዓ.ዓ. ነበር።
11. 2ኛ ነገ.14፡23-29 ውስጥ ነው።
12. 2ኛ ነገ.15-16 ውስጥ ነው።
13. የጋብቻን ውል ይመስላል።
14. ዘመኑ መልካም እንደነበረ ነው
15. ምዕ. 17 ነው።
16. የሆሴዕን የግል ሕይወት ታሪክ ነው።
17. ሚስቱ እስራኤልን ስለምትመስል ነው።
18. 40 ዓመታት ነገሠ።
19. 21 ዓመታት ይሆናል።
20. ዝሙት በእስራኤል እንዴት እንደነበር ነው።
21. በምዕ.6-7 ውስጥ ነው።
22. ሆሴዕን ካገባች በኋላ ነው።
23. ጥቂት ታማኝ ሰዎች ነበሩ።
24. አዝያን ነበር፣ ኢሳ.6፡1 ተመልከቱ።
25. ማቴ.26፡26-30 ነው።
26. የተለወጠ ሕይወት ነው።
27. እግዚአብሔር ያለው ዓይነት መሆን አለበት።

## ትምህርት ሁለት /ሆሴ.8-14/

1. 1ኛ ነገ.16፡21-28 ውስጥ ነው።
2. ዘንበሪ ነው።
3. አሞፅ፣ ሆሴዕና ኢዮኤል ናቸው።
4. በ740 ዓ.ዓ. ነው።
5. የሰሜን እስራኤልን በአሶር መያዝ ነው።
6. በ743 ዓ.ዓ. ነው።
7. የኤልያስና የኤልሳዕ ታሪክ ነው።
8. ዘፍ.15፡1-21ና ዘፀ.20 ናቸው።
9. ሕጎች ናቸው።
10. ዘሌ.26፡1-46 ውስጥ ነው።
11. ዳንኤልና ሕዝቅኤል ናቸው።
12. ከግብፅና ከአሶራውያን ጋር ነው።
13. ሁብታምና ታላቅ እንድትሆን ረዳት።
14. ስለ ሰማርያ ነው።
15. የከነዓናውያንን ነው።
16. ፍቅርን በሚመለከት ነው።
17. አድራጊው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።
18. ዕብራውያን 12።
19. እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሚሠራ መሆኑን ያሳየናል።
20. ማንኛውም እግዚአብሔር እንዲቆጣጠረው የማንፈቅድለት ነገር ሁሉ ነው።

## ትምህርት ሦስት /ኢዮኤል/

1. ነቢያት፣ ነገሥታትና ካህናት ናቸው።
2. የመንግሥት መከፈል።
3. ቀዳማዊ ኢዮርብዓም ነበር።
4. በቤቴልና በዳን ነው።
5. የባዕድ ሕዝብ ዕድገት ስለሚናገሩ ነው።
6. ናሆምና ዮናስ ነበሩ።
7. 110 ዓመታት ነው።
8. መቼ እንደተጻፈ አናውቅም።
9. በ743 ዓ.ዓ. ነው።
10. በዘንበሪ ዘመን ነበር።
11. ከአሞጽና ከሆሴዕ ጋር ተያይዞ ስለሚገኝ ነው።
12. ምዕራፍ 17 ነው።
13. የመሸነፋቸውን ምክንያት ነው።

14. ከእሶር በመጡ ሰዎች ተተካች።
15. እሶር ናት።
16. ሥዕላዊ።
17. የኢዮ.2፡28-32ን ፍጻሜ ያሳየናል።
18. አዝያን ነበር።
19. በበረከቶች ነው።

# ትምህርት አራት /አሞፅ/

1. ከ800-700 ዓ.ዓ. የሚገኙት ዓመታት።
2. ለ40 ዓመታት ከ783-743 ዓ.ዓ. ነው።
3. 6 ነገሥታት ነግሠዋል።
4. 2ኛ ነገ.15-16 ውስጥ ነው።
5. ስልምናሶር ነበር፥ 2ኛ ነገ.17፡5-6።
6. ሳርጎን ነበር።
7. ሰናክሬም ነበር።
8. አስናፈር።
9. ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ 12 ኪሎ ሜትር ርቃ ነው።
10. በ740 ዓ.ዓ. ነበር፥ ኢሳ.6፡1።
11. በ2ኛ ነገ.14፡23-29 ውስጥ ነው።
12. ሀብትና የግዛት መስፋፋት ናቸው።
13. የናስ ነበር።
14. ኤልያስና ኤልሳዕ ናቸው።
15. ሁለቱም በቤቴል ስለነበሩት ነቢያት ይናገሩ ስለነበር ነው።
16. አዝያን ነበር።
17. እስራኤል ከእግዚአብሔር ርቃ እንደነበር ነው።
18. በ586 ዓ.ዓ. ነበር።
19. ዘንበሪ ነበር።
20. የእስራኤላውያን ኃጢአት ነው።
21. 5 ራዕዮች አሉ።
22. ወደ ፍርድ ነው።
23. ስለ ነቢያት ጥሪ የሚናገሩት ነገር ነው።

# ክፍል ሁለት

## ትምህርት አምስት /ሚክያስ/

1. ሚክያስ ሶፎንያስና ዕንባቆም ናቸው።
2. ኢሳይያስና ኤርምያስ ናቸው።
3. ከ931-586 ዓ.ዓ. ነበር።
4. ሰሎሞን ሞተ።
5. የሚጽፉ ነቢያት አልነበሩም።
6. ኢሳይያስ ነበር።
7. በ700 ዓ.ዓ. ገደማ ነው።
8. በ620 ዓ.ዓ. ገደማ ነው።
9. ነቢያት አልነበሩም።
10. በ586 ዓ.ዓ. አቅራቢያ ነበር።
11. ኢዮስያስ ሞተ።
12. የአሶር መንግሥት ነው።
13. የባቢሎን መንግሥት ነው።
14. በ740 ዓ.ዓ. ነው፤ ኢሳ.6፡1።
15. ኢዮአታምና አካዝ ናቸው።
16. በ2ኛ ዜና 26 ውስጥ ነው።
17. ከአሶር ጋር ነው።
18. ምዕ.29-31 ናቸው።
19. ኢዮአታም፥ አካዝና ሕዝቅያስ ነበሩ።
20. የሕዝቡን ኃጢአት ስለሚገልፅ ነው።
21. ስለ ወደፊት ሁኔታ ነው።
22. የነበረው ቃል ኪዳን ነው።
23. ከሰማርያ ጋር ነው።
24. ኢዮአታም ብዙዎች ሀብታም እንዲሆኑ ረድቷቸው ነበር።
25. ምዕ.2፡1-4 ያሉት ቁጥሮች ናቸው።
26. ዕዝ.1-6 ያሉት ምዕራፎች ናቸው።
27. ከኢሳ.36-39 ወይም 2ኛ ነገ.17 ጋር ነው።
28. እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላደረገላቸው ሕዝብ ነው።
29. የጸሎት ነው።
30. እግዚአብሔር ራሱ ነው።
31. እግዚአብሔር በሥራ ላይ እንዳለ ስለሚያሳይ ነው።
32. የትንቢቶች ፍጻሜ ነው።

## ትምህርት ስድስት /ሶፎንያስና ዕንባቆም/

1. ሶፎንያስ ነበር።
2. ከ606 ዓ.ዓ. በኋላ ነበር።
3. ለ70 ዓመታት ማለት ከ606-536 ዓ.ዓ. ነው።
4. በ586 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር።
5. ምናሴና አሞፅ ናቸው።
6. በ609 ዓ.ዓ. በመጊዶ ነበር።
7. ምንም ነቢያት አለመኖራቸው ነው።
8. ከ640-609 ዓ.ዓ. ነበር።
9. በ2ኛ ነገ.21-22 ውስጥ ነበር።
10. በ622 ዓ.ዓ. ነበር።
11. እግዚአብሔር ክፉን እንዴት ይጠቀምበታል? የሚል ነበር።
12. የእግዚአብሔር ትዕግሥት ማለቁ ነበር።
13. ምናልባት በኋላ ነበር።
14. በ586 ዓ.ዓ. ነበር።
15. ለኢየሩሳሌም ከተማ ነበር።
16. የደስታ መዝሙር ነው።
17. በ606ና በ597 ዓ.ዓ. ነበር።
18. ቂሮስ ባቢሎንን ሲደመስሳት ነበር።
19. የዕንባቆም ጸሎት ነው።
20. በዓል ነበር።
21. ኤርምያስ ነበር።
22. 140 ዓመታት ናቸው።
23. በመናገር ገለፀ።
24. መልስ በማግኘቱ ነው።
25. ሁለቱም በምስጋና ስለሚደመደሙ ነው።

# ክፍል ሦስት

## ትምህርት ሰባት /ዘካ.1-8/

1. ሐጌ፣ ሶፎንያስና ሚልክያስ ናቸው።
2. 2ኛ ነገ.25፤ 2ዜና 36ና ኤር.52 ናቸው።
3. ኤርምያስ ነው።
4. መዝ.135 ነው።
5. ዳንኤልና ሕዝቅኤል ናቸው።

6. ወደ ይሁዳ የሚመለሱትን ማበረታታት ነበር።
7. ከ538-333 ዓ.ዓ. ነበር።
8. መጽሐፈ አስቴር ነው።
9. ዘሩባቤል ነበር።
10. ስለ 536-520 ዓ.ዓ. ነው።
11. ነህምያ ነው።
12. ዘካርያስ ነበር።
13. ቤቶቻቸውን ይገነቡ ነበር፤ ሐጌ 1 ተመልከቱ።
14. የፋርስ መንግሥት ነበር።
15. ካምቤስስ ነበር።
16. በዳርዮስ ዘመነ መንግሥት።
17. በኢየሩሳሌም ለነበሩት ነበር።
18. ዳን.9፡1-3 ነው።
19. ስለ አዲስ ቤተ መቅደስ ነው።
20. ዕዝራ 2-6ና ሐጌ 1-2 ናቸው።
21. ማበረታታት ነው።
22. 8 ራዕዮች አሉ።
23. ለዘሩባቤልና ለኢያሱ ነበር።
24. በምኩራብ ተተካ።
25. በፋርስ መንግሥት ነበር።
26. የይሁዳ ጠላቶች ናቸው።
27. የኢያሱ ነው።
28. ስለ ኢያሱና ዘሩባቤል ነው።
29. ምድሪቱ ናት።
30. ስምንተኛው ራዕይ ነው፤ 6፡1-8።
31. መልሰው ከመገንባት ይልቅ አሁንም ባለፈው ነገር ያዙ ነበር።
32. የኢፊሶን መልዕክት ነው።
33. አማኞች በሙሉ ናቸው።

# ትምህርት ስምንት /ዘካ.9-14/

1. ዘካርያስ ነበር።
2. ዘሩባቤል ነበር።
3. ኢያሱ ነበር።
4. ከ586-536 ዓ.ዓ. ለ50 ዓመታት ነበር።
5. በ606 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር።
6. በ520 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር።
7. በዕዝራ 1-6 ውስጥ ነው።
8. 8 ራዕዮች ይገኛሉ።
9. በኢየሩሳሌም ስለሚገኙት ሕዝብ ነው።

10. በፋርስ ይኖሩ ለነበሩት ነው።
11. ረጋ በሉ የሚል ነው።
12. ተስፋ ስለቆረጡ ነበር።
13. በ536 ዓ.ዓ. ነበር።
14. ከ400 ዓመታት በላይ ይሆናል።
15. 100 ዓመታት ያህል ይሆናል።
16. ታሪካዊ፥ ትንቢታዊና ተግባራዊ ናቸው።
17. በ520 ዓ.ዓ. ገደማ በሐጌና በዘካርያስ ዘመን ነበር።
18. በ444 ዓ.ዓ. ገደማ በነህምያ ዘመን ነው።
19. ከምርኮ በኋላ ስለነበረው ሁኔታ ነው።
20. መልሶ የመገንባቱ ችግሮች ነው።
21. በ514 ዓ.ዓ. ነበር፥ ዕዝ.6፡15።
22. እርነት ማግኘት ነው።
23. ምዕ.12 ነው።
24. ታማኞች በሚሆኑበት ወቅት ነው።
25. ሮሜ 5-6ና ገላ.3 ናቸው።
26. በማንኛውም ከእርሱ በራቁበት ወቅት ነው፥ ምዕ.10።
27. ስለ መንጻት ነው።
28. ሁሉም ነገር ይገባዋል።
29. ቆራጥ ምስክርነት እንዲሰጡ ያጠነክራቸዋል።
30. ምዕራፍ 11 ነው።

# ትምህርት ዘጠኝ /ሐጌና ሚልክያስ/

1. ባቢሎንን ድል ለማድረግ ነው።
2. ስለ ኢዮስያስ ነበር።
3. ዘሩባቤል ነበር።
4. ስለ 70ዎቹ ዓመታት ምርኮ ነው።
5. በ457 ዓ.ዓ. ነበር።
6. ስለ 536-520 ዓ.ዓ. ነው።
7. ነህምያ ነበር።
8. ወደ እስክንድሪያ ነው።
9. ዳርዮስ ነበር።
10. ሐጌና ዘካርያስ ናቸው።
11. ምንም የግንባታ ሥራ አልተካሄደም።
12. መልሰው እንዲገነቡ ነበር።
13. ዘሩባቤልን ነው።
14. ያዕቆብን መረጠ።
15. ኪዳል ኪዳኑ የተነሣ ነው።
16. አሥራት ነበር።

17. ስለ ኤልያስ ነው።
18. በ586 ዓ.ዓ. ነበር።
19. በሚልክያስ ዘመን ነበር።
20. የአማኞች ናቸው።
21. መታዘዝ ነው።
22. ማቴ.25፤ ማር.13፤ ሉቃስ 21።
23. ጥምቀትና የጌታ እራት።
24. እግዚአብሔር ስለማይለወጥ ነው።
25. ከ520-444 ዓ.ዓ. 84 ዓመታት ያህል ነው።

# ክፍል አራት

## ትምህርት አሥር /አብድዩ፥ ዮናስና ናሆም/

1. ሆሴዕ፥ አሞፅና ኢዮኤል ናቸው።
2. አሶር፤ በ722 ዓ.ዓ. ነበር፥ 2ኛ ነገ.17 ተመልከቱ።
3. ኤልያስና ኤልሳዕ ናቸው።
4. ኢሳይያስና ሚክያስ ናቸው።
5. ኢዮአታም፥ አካዝና ሕዝቅያስ ነበሩ።
6. 70 ዓመታት ያህል ነበር።
7. በኢዮስያስ ዘመን መንግሥት ነበር፥ 2ኛ ነገ.21-22።
8. ምናልባት በሶፎንያስ ዘመን ነበር።
9. ሚክያስ፥ ሶፎንያስና ዕንባቆም ናቸው።
10. ኢሳይያስ ነው።
11. ሕዝቅኤል ነበር።
12. ዕዝራ፥ ነህምያና አስቴር ናቸው።
13. ሐጌና ዘካርያስ ናቸው።
14. በፋርስ ለቀሩት አይሁዳውያን ነው።
15. አብድዩ፥ ዮናስና ናሆም ናቸው።
16. ዮናስና ናሆም ናቸው።
17. ሕዝቅኤልና ዳንኤል ናቸው።
18. ምስክርነት እንዲሰጡ ነበር።
19. ባዕድ ሕዝብ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ነው።
20. የዓለም ሁሉ አምላክ ነው፤ የዓለም ሁሉ ገዥ ነው።
21. በትክክል እርግጠኞች መሆን አንችልም።
22. ስለ ኤዶም ተናገሯል፤ ኢየሩሳሌም በጦርነት ላይ ነበረች።
23. ኤሳው ነበር።
24. በ586 ዓ.ዓ. ነው።

25. በገሊላ ባሕርና በቀርሜሎስ ተራራ መካከል ላይ ነበር።
26. ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነበር።
27. በ2ኛ ነገ.14፡23-29 ላይ ነው።
28. ክፉ ነበረች።
29. በአሶራውያን ተደመሰሰች፥ 2ኛ ነገ.17።
30. በ606 ዓ.ዓ. ነበር።
31. በ663 ዓ.ዓ. ነበር።
32. የሚናገረው ስለ ፍርድ ብቻ ስለሆነ ነው።
33. ይሁዳ ወንድሙ ስለሆነ ነው።
34. እግዚአብሔር ይፈርድባታል።
35. በመጌዶ ነበር።
36. ጴጥራ።
37. የኢዶም መሪ ነበር።
38. ክፉ ንሥሐ ስለገባች ነው።
39. ከ885-874 ዓ.ዓ. ነበር።
40. በአሸዋ ሥር ተቀብራ ነበር።